«‹ወደጦርነት ላለመግባትና ችግሮችን በሰላም ለመፍታት በመንግሥትበኩል እየተደረገ ያለውን ጥረት አደንቃለሁ››

- ወይዘሮ ሶፊያ አሰፋ



ገጽ 6

የከተማ ግብርና ስኬታማነት ማሳያው

- ዶክተር ጋሻው

ገጽ 13


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 007 መስከረም 7 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# በ2015 ስንዴን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የተያዘውን ግብ ለማሳካት ተቃርበናል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በጀመርነው አዲስ ዓመት ስንዴን ለውጭ ሀገር ገበያ ለማቅረብ ወደያዝነው ግብ ተቃርበናል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ የፌደራል እና የክልል ከፍተኛ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን የዱግዳና ቦራ ወረዳዎችን የስንዴ ኩታ ገጠም እርሻን ጎብኝተዋል።

ከጉብኝቱ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንደገለጹት፤ በያዝነው አዲሱ ዓመት ስንዴን ለውጭ ሀገር ገበያ ለማቅረብ የተያዘው ግብ እጅግ ተስፋ የሚሰጥ ደረጃ ላይ ይገኛል።

ለኢትዮጵያውያን በዚህ ልክ መስራታችን ብሄራዊ ክብራችን እና የሀገር ሉአላዊነታችንን ከማስከበር ጋር በቀጥታ የተገናኘ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የመንግስትም ዋነኛ ትኩረት ከዚህ በፊት የነበረውን መራብ አሁን የተፈጥሮ ሀብታችን፣ ያለንን ጉልበት በአግባቡ በመጠቀም ስንዴን ከመብላት አልፈን ወደመላክ መቀየር ነው ብለዋል።


በ2015 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፦-ገባቦ ገብሬ

ዶክተር አስራት አጸደወይን

## የኢትዮጵያም ሆነ የቀጣናው ሰላም በዘላቂነት የሚረጋገጠው አሸባሪው ትህነግ ሲጠፋ ብቻ ነው


ገጽ 4


# በዘንድሮ የትምህርት ዘመን አዲሱ ስርዓተ ትምህርት በከፊል ተግባራዊ ይሆናል

## - በመጪው ሰኞ በመላ አገሪቱ ትምህርት ይጀመራል

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አዲስ አበባ፡- አዲሱ ሀገራዊ ስርዓተ ትምህርት በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ሙሉ ለሙሉ ፤ ከ9 እስከ 10ኛ ክፍል ደግሞ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የሙከራ ትግበራ የሚደረግ መሆኑን ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ:: መስከረም ዘጠኝ ቀን በሀገር አቀፍ ደረጃ ትምህርት እንደሚጀመርም ተጠቁሟል::

በትምህርት ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርቶች ስርዓተ ትምህርት ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ ዛፉ አብርሃ በሥርዓተ ትምህርት አተገባበሩና ትምህርት ስለሚጀመርበት ሁኔታ ላይ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ላለፉት አምስት ዓመታት ሲጠና የቆየው አዲሱ ሀገራዊ ስርዓተ ትምህርት በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ተግባራዊ ይደረጋል። ይህ ስርዓተ ትምህርት ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ሙሉ የሚተገበር ሲሆን ከ9ኛ እስከ 10ኛ ክፍል ደግሞ የሙከራ ትግበራ ይደረጋል። 11ኛና 12ኛ ክፍል የነባሩ ስርዓተ ትምህርት እስከ 2016 ዓ.ም ድረስ የሚቀጥል ይሆናል::

ስርዓተ ትምህርቱ በዚህ ዓመት ሙሉ እና የሙከራ


በዘንድሮ የትምህርት ዘመን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




“አሸባሪው ትህነግ ሕፃናትን ለጦርነት በማሰለፍ ትውልድን እያጠፋ ነው“

- አቶ ሀይለ ገብረሚካኤል


ገጽ 4

















# የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ የታክስ ማሻሻያ ተግባራዊ ተደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን እና አስመጪዎችን የሚያበረታታ እንዲሁም ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ የታክስ ማሻሻያ ተግባራዊ መደረጉን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በዚህም የታክስ ማሻሻያ ከውጭ የሚገቡም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኤሌክትሪክ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣ የቤት አውቶሞቢሎች እና የዕቃ መጫኛ ተሽከርካሪዎች ላይ ዝቅተኛ የጉምሩክ ታሪፍ የሚጣልባቸው ሲሆን ከተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ከኤክሳይዝ ታክስ እና ከሱር ታክስ ነፃ እንደሚደረጉም ታውቋል።

የታክስ ማሻሻያው ዓላማ በአገራችን በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የተሽከርካሪዎች ቁጥር በፖሊሲ ማዕቀፍ ከአካባቢ ደህንነት ጋር የሚስማማ ለማድረግ፣ በኅብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል፣ በአየር ንብረትና በብዝሃ ህይወት ላይ ተጽእኖ የማያሳርፍ እና ታዳሽ የኃይል ምንጮችን በአግባቡ የሚጠቀም የመጓጓዣ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ሲሆን፤ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ እንዲቀርቡ ለማስቻልም መሆኑ ተጠቅሷል።

በታክስ ማሻሻያው መሰረት የኤሌክትሪክ የቤት አውቶሞቢሎችን በተመለከተም ሙሉ በሙሉ ተበትነው ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው የሚገጣጠሙ አውቶሞቢሎች ከጉምሩክ ቀረጥ፣ ከኤክሳይዝ ታክስ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከሱር ታክስ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ መደረጉም ተገልጿል።

በከፊል ተበትነው ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው የሚገጣጠሙ የኤሌክትሪክ የቤት አውቶሞቢሎችን በተመለከተም አምስት በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ ብቻ የሚጣልባቸው ሲሆን ከኤክሳይዝ ታክስ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከሱር ታክስ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ ተደርጓል።




ሙሉ ለሙሉ ተገጣጥመው ያለቀላቸው የኤሌክትሪክ አውቶሞቢሎች ወደ ሀገር ሲገቡ ደግሞ 15 በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ ብቻ የሚጣልባቸው ሲሆን ከኤክሳይዝ ታክስ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከሱር ታክስ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ መወሰኑን ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# መንግስት ላይ ጫና ለመፍጠር ከሚሰሩ ተቋማት ጀርባ የተለያዩ አገራት ፖለቲካዊ ፍሳጎት አለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓትን በመደገፍ መንግስት ላይ ጫና ለመፍጠር ከሚሰሩ ተቋማት ጀርባ የተለያዩ አገራት ፖለቲካዊ ፍላጎት መኖሩን ዓለም አቀፍ የሰላምና ደህንነት ተመራማሪ ብሌን ማሞ ተናገሩ። መንግስት በአሸባሪው ሕወሓትና ተላላኪዎቹ ላይ እርምጃ በመውሰድ የአገር ሉዓላዊነትን የማስከበር ህጋዊ ኃላፊነት እንዳለበትም ተናግረዋል።

ዓለም አቀፍ የደህንነት ጉዳዮች ተመራማሪዋ ከኢዜአ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደተናገሩት፤ መንግስት ከኃይል ርምጃ ይልቅ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት በተደጋጋሚ ሞክሯል።

ሆኖም አሸባሪው ሕወሓት ለሰላም ቦታ እንደሌለውና ለውይይት እንደማይቀመጥ ከአንድም ሶስት ጊዜ ጦርነት በመክፈት በተጨባጭ አሳይቷል ነው ያሉት። በዚህም በርካታ ንጹሃን ዜጎችን ከመጨፍጨፉ ባሻገር የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚጻረሩና የማዕከላዊ መንግስትን የኃይል የበላይነት የሚፈታተኑ የኃይል ርምጃዎች ላይ መሳተፉን ጠቅሰዋል።

ለአብነት የሽብር ቡድኑ ራሱን እንደ አንድ ሀገር መንግስት የመቁጠር፣ ራሱን የቻለ መከላከያ ሰራዊት ያለው የማስመሰልና የውጭ ግንኙነት ቢሮ ከፍቶ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር የመገናኘት ተግባራት ውስጥ መሳተፉን አንስተዋል።

የቡድኑ የ50 ዓመታት ታሪክ የኢትዮጵያን ጡት ነካሽነትና ባንዳነት እንደሚያሳይ ያነሱት ተመራማሪዋ፤ በተለይ ከምዕራባውያን ጋር የቅጥረኝነት ጉዞው አለመቋጨቱን ገልጸዋል።


**የሰላምና ደህንነት ተመራማሪ ብሌን ማሞ**

ኢትዮጵያን ለማዳከም ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን በመጥቀስ፤ የአሸባሪው ሕወሓት ጋላቢዎች ትልቁ የሴራ መዳረሻ ኢትዮጵያን በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ መክተት መሆኑን ተናግረዋል። በተለይም የራሳቸውን ጥቅምና ፍላጎት ለማሟላት ሲሉ የተረጋጋና ልማት ላይ ያተኮረ መንግስት እንዲኖራት ፈጽሞ እንደማይፈልጉ በታሪክ መመዝገቡንና አሁንም መቀጠሉን አብራርተዋል።

አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ግለሰቦችም የመንግስትን በጎ ጥረቶች ወደ ጎን በመተው የሽብር ቡድኑን እኩይ ተግባራት በተዘዋዋሪ ሲደግፉ ይስተዋላል ብለዋል።

ሕወሓትን ከሽብር ቡድንነት ይልቅ የአንድ ሀገር ወይም ክልል ህጋዊና ቅቡልነት ያለው አስተዳዳሪ አስመስሎ የማቅረብና ከፌደራል መንግስቱ ጋር እኩል የማቅረብ ዝንባሌዎች መኖራቸውንም ጠቅሰዋል።

ከአዝማሚያዎቹ ጀርባ የብዙ ኃይሎች ሴራና ፖለቲካዊ ግብ መኖሩን ጠቁመው፤መንግስት አሁን የጀመረውን የሰላም አማራጭ አጠናክሮ በመቀጠል በዲፕሎማሲው መስክ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሀገራት ላይ ጫና የመፍጠር ስልታዊ ስራ ይጠብቀዋል ብለዋል።

ከሰላም አማራጩ ጎን ለጎን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚያስከብሩ፣ ህጋዊ ማዕከላዊ መንግስትነቱን የሚያረጋግጡና፣ የኃይል የበላይነቱን የሚያስመሰክሩ ርምጃዎች መውሰዱን እንዲቀጥልም መጠየቃቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

በተለይም አሸባሪው ሕወሓት ተገድዶ ወደ ሰላም ጠረጴዛ እንዲመጣ ካልሆነም የጋላቢዎቹን ተልዕኮ ለማሳካት ኢትዮጵያን የማወክ ተግባሩ እንዲያከትም የማድረጉን ስራ መንግስት አጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም አመልክተዋል።



# አሸባሪው ሕወሓት

## የፈጸመው የነዳጅ ዝርፊያ የሰብአዊ ድጋፍ ስራውን አክብዶብናል

- ዴቪድ ቤስሊ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት መቀሌ በሚገኘው የዓለም ምግብ ፕሮግራም መጋዘን ውስጥ የፈጸመው የነዳጅ ዝርፊያ የድርጅቱን ስራ እንዳከበደበት ዋና ዳይሬክተሩ ዴቪድ ቤስሊ ገለጹ።

በተመድ የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ አምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ በትዊተር ገጻቸው ባሰፈሩት ፅሁፍ ዋና ዳይሬክተሩ በፀጥታው ምክር ቤት ስብሰባ ላይ አማፂው ቡድን የፈጸመው ዝርፊያ ድርጅቱ በትግራይ በሚያከናውነው ስራ ላይ ትልቅ እንቅፋት እንደፈጠረ መግለጻቸውን ጠቅሰዋል።

አያይዘውም ድርጅቱ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ለሚያከናውነው የሰብአዊ ድጋፍ ነዳጅ፣ ድጋፍ እና ተንቀሳቅሶ መስራት እንፈልጋለን ማለታቸውን አስታውቀዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ባለፈው ነሐሴ ወር መቀሌ በሚገኘው የዓለም ምግብ ፕሮግራም ድርጅት ግቢ ውስጥ በመግባት 570 ሺህ ሊትር ነዳጅ መዝረፉ ይታወሳል።

ይህን ተከትሎም የዓለም ምግብ ፕሮግራም ሰብአዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ተዘዋውሮ ድጋፍ ለማድረግ መቸገሩን በተደጋጋሚ ሲገልጽ ቆይቷል። አሸባሪው ሕወሓት መቀሌ ከሚገኘው የዓለም ምግብ ድርጅት መጋዘን 12 ቦቴ ነዳጅ መዝረፉን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ቃል አቀባይ ስቴፈን ዱጃሪክ ይፋ ማድረጋቸው ይታወሳል።

ቃል አቀባዩ ባለፈው ነሀሴ ወር መጨረሻ ላይ የአሸባሪው የሕወሓት ቡድን በሀይል መቀሌ ወደሚገኘው የድርጅቱ መጋዘን በመግባት 12 የነዳጅ ቦቴዎችን በአጠቃላይ 570 ሺህ ሊትር ነዳጅ መዝረፉን አስታውቀዋል። በስፍራው የነበሩ የተመድ ሰራተኞችም የሽብር ቡድኑን ዝርፊያ ማስቆም እንዳልቻሉም ነው ያመለከቱት።

ቃል አቀባዩ በሕወሓት የተዘረፈው ነዳጅ በክልሉ የሰብዓዊ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ምግብ ለማቅረብ እና ማዳበሪያን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ የሰብዓዊ እርዳታዎችን ለማድረስ ይውል እንደነበር ጠቁመዋል።

የሕወሓት ዝርፊያ የድርጅቱን የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦት ስራውን እንደሚጎዳም መናገራቸው ይታወሳል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ማናቸውንም የሰብዓዊ እርዳታ ቁሳቁሶች ላይ የሚፈፀም ዝርፊያን እንደሚያወግዝም አስታውቋል። ይህን ተከትሎም ዓለም አቀፍ ተቋማትና አገራት የአሸባሪውን ሕወሓት እኩይ ድርጊት በወቅቱ ማውገዛቸው የሚታወስ ነው።

# የቢጫ ወባ ክትባት የምስክር ወረቀት በጥቁር ገበያ እየተሸጠ ነው

- ተገልጋዮች

# ድርጊቱን ለመከላከል ከፖሊስ፣ ደህንነትና ከሆስፒታሉ ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው

-የማኅበረሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

**ሙሳ ሙሐመድ**


አዲስ አበባ፡- በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ግቢ ውስጥ የሚሰጠው የቢጫ ወባ ክትባት ከሆስፒ፤ታሉ ውጪ በህገ-ወጥ መንገድ በጥቁር ገበያ እየተሸጠ መሆኑን ተገልጋዮች ተናገሩ። የማኅበረሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በበኩሉ ችግሩ መኖሩን አምኖ ለመከላከል ከፖሊስ፣ ደህንነትና ሆስፒታሉ ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው።

ከተገልጋዮቹ መካከል አቶ አብርሃም ጫኔ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሆስፒታሉ እንደልብ የማይገኘውና ለአለምአቀፍ ተጓዦች የሚሰጠው የቢጫ ወባ ክትባት የምስክር ወረቀት በህገ-ወጥ መንገድ እየታተመ በሆስፒታሉ ዙሪያ በጥቁር ገበያ እየተሸጠ ነው።

"ክትባት ለመውሰድ ወደ ሆስፒታሉ ስንሔድ ገና ከማዕከሉ በር በእድሜ ከ60 ዓመት በላይ ለሆኑ ነው የምንሰጠው ይባላል፣ ከዚህ በታች ለሆነና አንገበጋቢ ሆኖ ስንጠይቅ የአቅርቦት እጥረት ስላለብን አይሰጥም ይሉናል፤ እጥረቱ በሆስፒታሉ ተደጋጋሚ ይከሰታል" ያሉት አቶ አብርሃም፣ ከዚያ በተጨማሪ ለህክምና ወደ ውጭ ልትወጡ ካልሆነ በስተቀር ማግኘት አትችሉም ብለው ይመልሱልናል ብለዋል።

ከተቋሙ አግልግሎቱን አጥተን ከግቢው ሳንወጣ ዞረው ከበር በተኮለኮሉት ደላሎች በኩል ሰርተፊኬቱን በህገ-ወጥ እንድንገዛ እንጠየቃለን፤ ከመርሃ-ግብራችን ላለመስተጓጎልም በዙሪያው ካሉት ደላሎች በዋጋ ተደራድረን በራሳችንና በሀገር ላይ ያለውን ችግር እያወቅንም ቢሆን እንድንገዛ እንገደዳለንም ብለዋል።

የክትባት አገልግሎት በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት በቁጥር የበዙ ሆስፒታሎች ተመርጦ በጥቁር አንበሳ




የሚሰጥ መሆኑ ነው አቶ አብርሃም የገለጹት፣ ክትባቱን ለህዝብ ሳይሆን ለህገ-ወጥ ሰዎች የገንዘብ ፍላጎት መሙያ ያደረገውም ይህ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በህዝብ ስም የተከፈቱት ክትባት ማዕከሎችም ክትባቱን ፈልገው የሚመጡትን ዜጎች እያገኙት አይደለም፣ የጉዞ ዓላማቸው እንዳይሰናከል በማሰብ ብቻ በኪስ ገንዘባቸው በሆስፒታሉ ዙሪያ ከተኮለኮሉት ደላሎችና ሱቆች በማቅናት በመደራደር ገዝተው ይሄዳሉ ብለዋል። ይህ ለዜጎች የተከፈተውን አገልግሎቱን የማግኘት



መብትን ይገድባል፣ በውጭ ከተኮለከሉት ደላሎች ጋርም ትስስር ያለው አካሔድ መኖሩን ይጠቁማል፤ የመንግስትን የተለየ ክትትልም ይሻል ሲሉ ተናግረዋል።

ለትምህርትና የተለያዩ ጉዳዮች ከሀገር የሚወጡና ክትባቱን የሚፈልጉት በህገ-ወጥ መንገድ ከሆስፒታሉ አካባቢ ካሉት ደላሎችና ሱቆች እንዲገዙ ይገደዳሉ ያሉት ደግሞ በስነ-ጽሁፍ መድረክ ለመካፈል ወደ ደቡብ አፍሪካ ለማቅናት ቢፈልግም ክትባቱን ማግኘት ያልቻለው አቶ አዲሱ ከበደ ተናግሯል።

በእድሜ ገደቡ አገልግሎቱን ማግኘት አትችልም ተብያለሁ፣ በብዙ ጊዜ ጥረት ያገኘሁትን የስነ-ጽሁፍ መርሃ-ግብር እንዳያመልጠኝ በማሰብ ብቻ በህገ-ወጥ መንገድ ከሚሸጡት ደላሎች ገዝቼ ለመጠቀም ተገድጃለሁ ሲል መግዛቱንና ለሚፈልገው መርሃ -ግብር መብቃቱን አቶ አዲሱ ገልጿል። በአገልግሎቱ ህጉን በሚጥሱና የህዝብ ንብረትን ለግል በሚያውሉት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ሁለቱም ግለሰቦች ጠይቀዋል።

በማህበረሰብ ጤና ኢንስቲቱዩት የዓለም አቀፍ ተጓዦች ማዕከል ዳይሬክተር አቶ ዮሐንስ ዱጋሳ እንደተናገሩት፤ ክትባቱ በጥቁር አንበሳ ብቻ ሳይሆን ቅዱስ ጳውሎስን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በሚገኙ ሆስፒታሎች ይሰጣል። የሚሰጠውም የዓለም የጤና ድርጅት ያስቀመጣቸውን መስፈርቶችን ላሟሉ ነው።

ድርጅቱ ዜጎች የክትባት ካርድ ሳይይዙ እንዳይገቡባቸው ወዳደረጋቸው ሀገራት ለሚሄዱና ክትባቱን ለመውሰድ አስፈላጊውን መስፈርት ላሟሉ ሁሉ ይሰጣል።

የእድሜ ገደቡ የክትባቱ እጥረት በሚኖርበት ወቅት አስፈላጊ ለሆኑት ብቻ ለማዳረስ ሲባል ተጥሎ የነበረ ነው። አሁን ላይ ዓለም አቀፍ ተጓዦች የሆኑና የመውሰድ ፍላጎቱ ላላቸው ለሁሉም ዜጎች እየተሰጠ ነው። ወደ ፊትም የአቅርቦት እጥረት እስካለገጠመን ድረስ ይሰጣል ብለዋል።

በጥቁር አንበሳ አካባቢ ህገ-ወጡ የክትባት ካርድ የሚሸጥበት ሁኔታ መኖሩን የገለጹት አቶ ዮሐንስ፤ ለመከላከል ከፖሊስ፣ ደህንነቶችና ከሆስፒታሉ ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው። እስካሁንም በወንጀሉ ተጠርጠረው የተያዙና ለህግ የቀረቡ መኖራቸውን ጠቁመው፤ ወደፊትም አገልግሎቱን ለማዘመን እየተሰራ ነው። ህገ-ወጡን አካል በህግ የመጠየቁ ተግባርም ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በህገ-ወጥ መንገድ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለመግታት የሁሉም አካላትን ርብርብ ይጠይቃል ያሉት አቶ ዮሐንስ፣ የሚዲያ ተቋማት ሂደቱ በግለሰቦችና ሀገር ላይ የከፋ ተጽዕኖ እንዳለው በማወቅ የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

# በያዝነው ዓመት ለ12 ሚሊዮን ሰዎች የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ ይካሔዳል

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በያዝነው የ2015 ዓ.ም ለ12 ሚሊዮን ዜጎች የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ እንደሚካሔድ የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ዮዳሔ አርያስላሴ ትናንት በተካሄደው የብሔራዊ መታወቂያ ቀን መድረክ ላይ ተገኝተው እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ በያዝነው የ2015 ዓ.ም ብቻ ለ12 ሚሊዮን ሰዎች የብሔራዊ መታወቂያ ምዝገባ አገልግሎት ይካሔዳል።


አቶ ዮዳሔ እንዳሉት፤ በቀጣይ ሶስት ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ የብሔራዊ መታወቂያ አገልግሎትን ሙሉ በሙሉ በመላው ኢትዮጵያ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ ነው።

በኢትዮጵያ አገልግሎቱ ከተጀመረ 12 ዓመታትን ያስቆጠረ መሆኑን የገለጹት አቶ ዮዳሔ፤ እስካሁንም አንድ ሚሊዮን ሰዎችን ብቻ ተጠቃሚ በማድረግ ውስንነት የነበረበት መሆኑን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ኢንጅነር መላኩ እዘዘው እንደተናገሩት፣ የዲጂታል መታወቂያን ለንግዱና ለግሉ ዘርፍ ማስተዋወቅ ዘርፉ በመታወቂያ ስርዓት ትግበራ ላይ የሚኖረውን አስተዋፅኦ ከፍ ያደርገዋል።

በቀጣይም አገልግሎቱ በመላ ሀገሪቱና ለሁሉም ተገልጋይ በንግድ ስርዓቱ ላይ ፍትሃዊነት እና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

በመታወቂያ አገልግሎት ሳቢያ የሚደርስ የሳይበር ጥቃትን በመከላከል ትክክለኛውን አገልግሎት ለተገቢው




አካል እንዲደርስ ያደርጋልም ሲሉ ኢንጅነር መላኩ ተናግረዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ኃላፊ እና የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር አቶ ተፈሪ ፍቅሬ ሁሉም ሰው መታወቅ ስለሚገባው የመታወቂያ ቀን እያከበርን ነው ብለዋል።

የመታወቂያ ቀንን የምናከብረው እያንዳንዱ የማንነት መለያ አድርጎ መታወቂያን ከመጠቀም ባሻገር በሁሉም ዘርፍ ለምናበረክተው ሀገራዊ ፋይዳና ለምናገኘው አገልግሎት ግዴታችንን ለመወጣት ያስችለናል፣ መብቶቻችንን ለመጠየቅም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ተፈሪ ገለጻ፣ አገልግሎቱ የሀብት ብክነትን ይቀርፋል፣ በየአካባቢው በተለያዩ አሰራሮች ላይ የሚደርሱትን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ይከላከላል፣ የነዋሪዎችን ሰላምና ደህንነትም ያረጋግጣል።

በሌላ በኩልም በቀበሌ መታወቂያ አሰጣጥና አገልግሎት ላይ የሚታዩ ዘርፈ ብዙ ክፍተቶችን ያስቀራል፣ የፖሊሲ ቀረጻና ትግበራን ለማቃለል ይጠቅማል ሲሉም ጠቁመዋል።

ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ዳይሬክተር ዶክተር አብዮት ባዩ የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባው እንደሌሎቹ የመታወቂያና የፓስፖርት ምዝገባዎች በእድሜ ገደብ የሌለውና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ተናግረዋል።

አመራሮቹም የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ በአዲስ መልኩ መጀመሩን በጋራ አብስረው፤ የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ አካሂደዋል።

ጉምሩክ ኮሚሽን
CUSTOMS COMMISSION

# ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የግል መገልገያ እቃዎች መመሪያ ተሻሻለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የግል መገልገያ እቃዎች ወደ ሀገር የሚገቡበትን ሁኔታ የሚወስነው በስራ ላይ ያለው መመሪያ ለህገወጥ ንግድ በር የከፈተና የአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ተፅዕኖ የፈጠረ በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 923/14 መተካቱን የጉምሩክ ኮሚሽን አስታወቀ።

ቀድሞ በነበረው መመሪያ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው በመንገደኞች እንዲገቡ የተፈቀዱ 102 አይነት እቃዎች ወደ 16 አይነት ዝቅ እንዲሉ ተደርጓል።

ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ቢያንስ ለ12 ወራት ሲገለገሉባቸው የነበሩትን የግል መገልገያ እቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት እንደሚችሉ ተገልጿል።

የግል መገልገያ እቃ በስጦታ የተላከለት ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የሌለው ከሆነ ከቀረጥና ታክስ በተጨማሪ 30 በመቶ የገቢ ግብር እንደሚከፍል በመመሪያው ተመላክቷል።

በአንድ ዓመት ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ ስጦታ መቀበል እንደማይቻልም ነው የተገለጸው። መመሪያው ከነሐሴ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ተደርጓል።

# አገልግሎቱ የሀገር ውስጥ መድኃኒት አቅራቢዎችን አቅም ለማሳደግ እየሰራ ነው

## • ሁለተኛው ዓለም አቀፍ የመድኃኒት አቅራቢዎች ኮንፈረንስ ተካሂዷል

**አብዱረዛቅ መሐመድ**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የመድኃኒት አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የሚስተዋለውን የአቅርቦት ሂደት መጓተት ለመቅረፍና የሀገር ውስጥ አቅራቢዎች አቅም ለማጎልበት እየሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ገለጸ።

የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አብዱልቃድር ገልገሎ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የመድኃኒት ፍላጎት ቢኖርም የአቅራቢዎች ቁጥር ውስን በመሆኑ በአቅርቦት ሰንሰለቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሲፈጥር ቆይቷል።

"አገልግሎቱ 85 በመቶ የሚሆነውን የሕክምና ግብዓት ከውጪ ነው የሚያስገባው" ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የሕክምና ግብዓቶች አቅርቦት ረጅም ጊዜ የሚወስድና በርካታ ባለድርሻ አካላትን ያካተተ መሆኑ ለአቅርቦት መጓተት ምክንያት ሆኗል ብለዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በዓለም አቀፍ ደረጃ የግብዓት አቅርቦት ሰንሰለቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱ ለአቅርቦት ሰንሰለቱ መጓተት ሌላኛው ምክንያት መሆኑንም አስረድተዋል።

በሀገር ውስጥ አቅራቢዎች የሚሸፈነው 15 በመቶ የሚሆነው ብቻ መሆኑን ጠቅሰው፤ የሀገር ውስጥ አቅራቢዎች አቅም ማሳደግ ሀገሪቷ ጊዜና የውጭ ምንዛሪን ለመቆጠብ እንዲሁም የአቅርቦት ሂደቱን ለማሳጠር እንደሚረዳትም አብራርተዋል።

በሀገሪቱ በትግበራ ላይ ያለው የግዢ መመሪያ የሕክምና ግብዓቶችን ባህሪ ከግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆኑና ልዩ ትኩረት እንደሚሻ የተናገሩት ዶክተር አብዱልቃድር፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ አገልግሎቱ ለመንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን ጥያቄ ማቅረቡንም ገልጸዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ የሕክምና ግብዓቶች ግዢ ሌሎች ቁሳቁሶች በሚመሩበት የግዢ መመሪያ መመራት የለበትም፣ ኤጀንሲው የመድኃኒትን ባህሪ፣ አንገብጋቢነትና አጭር የመጠቀሚያ ጊዜ ታሳቢ ያደረገ የግዢ መመሪያ እንዲዘጋጅ እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

በተያያዘ ዜና፣ የሀገሪቱ የመድኃኒት አቅርቦት ሰንሰለትን ማሻሻል ላይ ትኩረቱን ያደረገው ሁለተኛው ዓለም አቀፍ የመድኃኒት አቅራቢዎች ኮንፈረንስ በትናንትናው እለት በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት አዘጋጅነት የተካሄደው ይህ ኮንፈረንስ ከዓለም አቀፍ መድኃኒት አቅራቢዎች ጋር ያለውን የገበያ ትስስር በማጠናከር በሀገሪቱ የመድኃኒት አቅርቦት ሰንሰለቱን ማሻሻል፣ በዘርፉ የሚስተዋሉ ማነቆዎችን በመፍታት የመድኃኒት አምራቾችና አቅራቢዎች ወደ ኢትዮጵያ መሳብ እንዲሁም የምዝገባ ሂደቱን ሊያቀላጥፉ የሚችሉ ማሻሻያዎችን በተመለከተ ግንዛቤ ለመፍጠር ያለመ መሆኑ ተገልጿል።

የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አብዱልቃድር ገልገሎ በመክፈቻ ንግግራቸው እንደገለጹት፤ የመድኃኒት አቅርቦት ሰንሰለቱ ውስብስብና ከፍተኛ መቀናጀት የሚጠይቅ በመሆኑ እንዲህ አይነት መድረኮች ከፍተኛ ፋይዳ ይኖራቸዋል።

በዘርፉ ከፍተኛ የግብዓት ፍላጎት አለ ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ አብዛኞቹ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ የተመዘገበ አቅራቢ ባለመኖሩ በመድኃኒት አቅርቦት ላይ ችግር ፈጥሮ እንደቆየም አብራርተዋል።

በኢትዮጵያ ከፍተኛ የመድኃኒት ፍላጎት ቢኖርም የአቅራቢዎች ቁጥር ውስን መሆኑን የገለጹት ዶክተር አብዱልቃድር፤ ለአብነትም በአገልግሎቱ የግዥ መዘርዝር ከተካተቱ 1020 የመድኃኒት አይነቶች መካከል በ970 መድኃኒት አይነቶች በተደረገው ጥናት 257 መድኃኒቶች ምንም አይነት የተመዘገበ አቅራቢዎች የላቸውም ብለዋል።

በተጨማሪም በዳሰሳ ጥናቱ መሰረት 231 የመድሃኒት አይነቶች አንድ አቅራቢ ብቻ ያላቸው መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል። ይህም በአቅርቦቱና በፍላጎቱ መካከል አለመጣጣም እንዲከሰት ማድረጉን ጠቁመዋል።

በጉባዔው የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰን ወክለው ንግግር ያደረጉት የአርማወር ሐንሰን ምርምር ተቋም ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ በበኩላቸው፤ የጤና አገልግሎትን ለማሻሻል የመድኃኒትና ሕክምና መሳሪያ አቅራቢዎች ሚና ወሳኝ መሆኑን አስረድተዋል።

መንግሥት በአምራች ዘርፍ ትኩረት ከሰጣቸው አንዱ የመድኃኒት ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ አኳያ የግሉ ሴክተር በዘርፉ እንዲሰማራ ጥሪ አቅርበዋል።

በኮንፈረንሱ የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎትና የጤና ሚኒስትር ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ ጥሪ የተደረገላቸው አምባሳደሮች እንዲሁም ከ103 በላይ የሚሆኑ የዓለም መድኃኒት አቅራቢዎች በአካልና በቨርቹዋል ተሳታፊ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።

# "አሸባሪው ትህነግ ሕፃናትን ለጦርነት በማሰለፍ ትውልድን እያጠፋ ነው"

- አቶ ሀይለ ገብረሚካኤል

**መአርግ ገ/እግዚአብሔር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ትህነግ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ህጻናትን በውትድርና እየመለመለ ለጦርነት በማሰለፍ የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት እየሰራ ነው ሲሉ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሁለት የብልፅግና ፓርቲ አመራር አቶ ሀይለ ገብረሚካኤል ገለጹ።

አቶ ሀይለ ገብረሚካኤል ከኢፕድ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለፁት፤ ታዳጊ ህጻናትን ወደ ጦርነት ማስገባትና አደንዛዥ እጾችን መጠቀም በህግ የተከለከለና በአለም አቀፍ ህግም ወንጀል ነው።

እንደ አቶ ሀይለ ገለጻ፣ አሸባሪው ትህነግ ግን ከዓለም አቀፉ ህግ በተፃራሪ ህፃናትን ለጦርነት እያሰለፈ ትግራይን ያለ ትውልድ ለማስቀረትና የፌደራል መንግስት ህጻናትን እየገደለ ነው በማለት የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት እየሰራ ነው።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ሕጻናትን አደንዛዥ እጽ ተጠቅመው ህሊናቸውን ስተው ወደ ጦርነት እየገቡ እንዲያልቁ በማድረግ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት እና የውጭ ድጋፍ በማግኘት የስልጣን ዘመኑን በጦርነት ለማራዘም ብቻ ስለሚያስብ ነው ብለዋል።

በዚህ ጦርነት የትግራይ ህዝብ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ገብቷል፤ የተረፈውም ተፈናቅሎ የከፋ ኑሮ እየመራ ነው፤ ህዝቡ ከዚህ በላይ ዋጋ ላለመክፈል ሲል ቡድኑን ከስልጣን ለማውረድ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለበት።

የትግራይ ህዝብ በዚህ በአሸባሪው ቡድን ምክንያት ለዘላለም እየተሰቃየ ሊኖር አይገባም ያሉት አቶ ሀይለ፤ ሰላም በመንፈግ የተቀረውን ህዝብ ለማጥፋት ሶስተኛውን ጦርነት ጀምረዋል፤ ህዝቡ ከዘላለማዊ ጦርነት፣ ረሃብ፣ ስቃይ እና ባርነት ታግሎ ነጻ መውጣት አለበት ብለዋል።

የሽብር ቡድኑ አመራሮች "የፌደራል መንግስት ህጻናትን እየገደለ ነው" በማለት የመንግስትን ስም ለማጥፋት በህዝብ ውስጥ ሆኖ እየተኮሱ እንዲመታ እያደረጉ ነው ያሉት አቶ ሀይለ፤ የትግራይ ህዝብ "እንድናልቅ እያደረጋችሁን ነው፤ በእናንተ ምክንያት ሰላም ማጣት የለብንም፣ ሰላም ስጡን" ብሎ ሊታገላቸው ይገባል ብለዋል።

# የኢትዮጵያም ሆነ የቀጣናው ሰላም በዘላቂነት የሚረጋገጠው አሸባሪው ትህነግ ሲጠፋ ብቻ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያም ሆነ የቀጣናው ሰላም በዘላቂነት የሚረጋገጠው አሸባሪው የትህነግ ቡድን ሲጠፋ ብቻ መሆኑን የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ተናገሩ። የትግራይ ህዝብ አሸባሪውን ትህነግ ቢታገልና ቢያጠፋ ከሌላው ህዝብ የበለጠ ተጠቃሚ እንደሚሆንም ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንቱ ዶክተር አስራት አጸደወይን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ የሽብር ቡድኑ ጥቅምት 24 ቀን 2013 በሰሜን እዝ ላይ ክህደት በመፈጸም፣ በአማራና በአፋር ህዝብ ላይ ታሪክ ይቅር የማይለው ስህተት የፈጸመ ሲሆን ፤ከሰሞኑ የጀመረው ጦርነት ሶስተኛ ወረራ ደግሞ ሌላኛው የቀጠለ ስህተቱ ነው።

ይህ ተግባሩ መቼም ቢሆን ለሰላም ፍላጎት የሌለው፣ የማይሰለጥን ቡድን መሆኑን ያሳየ ነው ያሉት ዶክተር አስራት፤ ሕወሓት የሰላማዊ ድርድሩን ወደጎን በመተው ለሶስተኛ ጊዜ ወደጦርነት መግባቱ ከስህተቱ የማይማር ድርጅት መሆኑን በተግባር ያሳያል ብለዋል።

ዶክተር አስራት እንደተናሩት፤ ሕወሓት ከስህተቱ ባለመማሩ በርካታ ዜጎች ህይወታቸውን እንዲያጡ፣ የትግራይ እህቶቻችን፣ እናቶቻችን፣ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን የችግሩ ገፈት ቀማሽ እንዲሆኑ አድርጓል። ከሰራቸው ሁለት ስህተቶች ሳይማር ሶስተኛ ስህተት ለመፈጸም መነሳቱ በሰላም መኖር የማይችል ድርጅት መሆኑን በግልጽ ያሳየ ነው።

የሚያሳዝነው የትግራይ ህዝብ ይህን አስከፊና አረመኔ የሆነ ድርጅት ማውገዝ አለመቻሉ ነው። ትግራይ ውስጥ ያሉት ታፍነውና ተገደው እንደሆነ ይታወቃል። አንዳንድ የትግራይ ወገኖቻችን እኩይ ተግባሩን እያጋለጡ በግልጽ የሚታገሉ አሉ። ይሁን እንጂ ከዚህም በላይ ሊወገዝ የሚገባው ነው። ነገር ግን ከትግራይ ውጪ በአገር ውስጥ ያሉና በውጭ አገር ያሉት የትግራይ ወንድሞቻችን የሽብር ቡድኑን እኩይ ተግባር ሊያወግዙትና በቃ ሊሉት ይገባል ነው ያሉት ዶክተር አስራት።

እንደ ዶክተር አስራት ገለጻ፤ የኢትዮጵያም ብሎም የቀጣናው ችግር በዘላቂነት ሊቀረፍ የሚችለው ትህነግ የተባለ የሽብር ቡድን ሲጠፋ ብቻ እንደሆነ ባለፉት ሶስት ተከታታይ ጥፋቶች ማየት ይቻላል። ይህን ጥፋት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያወግዘው ይገባል። ከምንምና ከማንም በላይ ትግራውያን ሕወሓት ሲጠፋ ተጠቃሚ ይሆናሉ እንጂ የሚጎዱበት ነገር የለም።

ሕወሓት በቀሰቀሰው ጦርነት የትግራይ ወንድሞቻችን የችግሩ ገፈት ቀማሽ ሆነዋል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ በጣም የሚያሳዝነው ከዚህ ጨካኝና አስከፊ የሆነ ድርጅት ለመላቀቅ አለመታገላቸው ነው። ሁሉም ትግራውያን ሊያወግዙትና በቃ ሊሉት ይገባል። ከተጋረጠባቸው መከራ ሊድኑ የሚችሉት የሽብር ቡድኑ ሲጠፋ ነው። ለዚህም ጥፋቶቹ ምስክር ናቸው። ከምንምና ከየትኛውም ህዝብ በላይ ተጠቃሚው የትግራይ ህዝብ ነው ብለዋል።

# በ2015 ስንዴን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በአካባቢው ከዚህ ቀደም በስንዴ ምርት ብዙም የሚታወቅ እንዳልነበረ የተገለጸ ሲሆን፤ ግብርናውም በተበጣጠሰ መንገድ ሲከናወን እንደነበረ ታውቋል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በሁለቱ ወረዳዎች ከ31 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በክላስተር ለምቷል።

በዚህ አመት ከ3ነጥብ2 ሚሊየን ሄክታር በላይ መሬት በስንዴ መልማቱን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ ያለጥርጥር በዚህ አመት ስንዴን ወደውጭ ትልካለች ብለዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ መሰደድን ወደ ሀገር ውስጥ መስራት መቀየር፣ መራቆትን ወደማልበስ መቀየር የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ እየተሰራ ነው።

በስንዴ መስክ የተሰራው ስራ በሁሉም መስኮች ውጤት እንደሚመጣ ያረጋገጠ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በርካቶች ትኩረታችንን ወደልማት እንድናደርግ ይሰራሉ ብለዋል። ሆኖም ሁላችንም በተሰማራንበት መስክ ለውጤታማነት መስራት እንዳለብን አሳስበዋል።

ወታደሩ ሀገሩን መጠበቅ፤ አርሶ አደሩ ማረስ፣ መምህሩ ማስተማር አለበት ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በየክልሉ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ግብርናውን በመደገፍ ረገድ እየሰሩ ያለውን ስራ አድንቀዋል፤

ኢትዮጵያ በበጋ ስንዴ እርሻ ስራ ዘንድሮ ከአንድ ሚሊየን ሄክታር በላይ እንደምታለማ ይጠበቃል፤ በመኸሩም በበጋውም እርሻ የሚለማው ተደምሮ ከሚያስፈልጋት የስንዴ ምርት በተጨማሪ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ከ30-40 ሚሊየን ኩንታል ስንዴ ታገኛለች ተብሎ ይጠበቃል።

በጉብኝቱ ላይ የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ እና የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳን ጨምሮ ሌሎች የፌዴራልና የክልል አመራሮች ተገኝተዋል።

# በዘንድሮ የትምህርት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ትግበራ ከተደረገበት በኋላ በ2016 ዓ.ም የሚኖሩ ችግሮችን በማስተካከል እና በማዳበር ሙሉ ለሙሉ ወደ ትግበራ የሚገባ መሆኑን ጠቁመው፤ አዲሱ ስርዓተ ትምህርት በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ባሉ የግልም ሆኑ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚተገበር መሆኑን አስታውቀዋል።

የሙከራው ትግበራ በሚኒስቴሩ ድረ ገጽ፣ በመምህራን እና በተማሪዎች እጅ ከደረሰ በኋላ ማህበረሰቡ በሚሰጠው የማሻሻያ ጥቆማ ዳብሮ በ2016 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚሆንም አስታውቀዋል።

አዲሱ ስርዓተ ትምህርት እስካሁን በስራ ላይ ያለው ስርዓተ ትምህርት ያሉበት ክፍተቶች የተስተካከለበት እና የትምህርት ጥራትን ለማምጣት የተዘጋጀ መሆኑንም ተናግረዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ መስከረም 9 ቀን 2015 ዓ.ም መደበኛ የመማር ማስተማር ስራ እንደሚጀመር የገለጹት የትምህርት ፕሮግራሞች ጥራትና ማሻሻል መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ዮሐንስ ወጋሶ፤ ለዚህም 34 ሺህ ትምህርት ቤቶች ዝግጁ መሆናቸውንና 16 ነጥብ 3 ሚሊዮን ተማሪዎች መመዝገባቸውን አመልክተዋል።

በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ምክንያት መስከረም ዘጠኝ ትምህርት የማይጀምሩ ትምህርት ቤቶች መኖራቸውንም ገልጸዋል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሄት



ፓርኪንሰን

ገጽ 8



ባለብዙ አንድምታው የመኖሪያ ቤቶች እድሳትና ግንባታ

ገጽ 14



‹‹ወደጦርነት ላለመግባትና ችግሮችን በሰላም ለመፍታት በመንግሥትበኩል እየተደረገ ያለውን ጥረት አደንቃለሁ››

- ወይዘሮ ሶፊያ አሰፋ

ገጽ 6



ባላለፈው ችግር- ነገን ለመሻገር

ገጽ 16

## በውስጥ ገጾች

ራስ ጠልነት፡- ለሰብዓዊ ፍጡር ሀፍረት የሆነ አሸባሪው ትሕነጋዊ ታህተ ሰብእ ባህሪይ

ገጽ 9

እኛው ያጠገብናቸው የመዲናችን አይነኬ ‹‹ባለሥልጣናት››

ገጽ 11

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ወደጦርነት ሳለመግባትና ችግሮችን በሰላም ለመፍታት በመንግሥት በኩል እየተደረገ ያለውን ጥረት አደንቃለሁ››

- ወይዘሮ ሶፊያ አሰፋ

ማህሌት አብዱል

የዛሬዋ የዘመን እንግዳችን በግብረ-ሰናይ እንዲሁም በአገራዊ እርቅና ሰላም ሥራቸው ለረጅም ዓመታት ሕዝብና አገራቸውን ያገለገሉ እናት ናቸው። እኚህ ሴት የበርካታ ዜጎችን ሕይወት ለመታደግና ኑሮ ለመለወጥ ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉ ቢሆኑም የልፋታቸውን ያህል ያልተዘመረላቸው ታታሪ ሰው ስለመሆናቸው የሚያውቋቸው ይመሰክሩላቸዋል። እንግዳችን ውልደታቸውም ሆነ እድገታቸው አዲስ አበባ ከተማ ቢሆንም ለጥቂት ጊዜ በድሮ አጠራር ሲዳሞ ክፍለሀገር ኖረዋል። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በቀድሞ ልዑል መኮንን ትምህርት ቤት ነው የተማሩት። ብርሃን ዛሬ ነው በተባለ ትምህርት ቤት ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማታው ክፍለ ጊዜ ገብተው እየተማሩ ጎን ለጎንም በጽሕፈት ሥራ እዚያው ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያገለግሉም ነበር። ሆኖም በወቅቱ ትዳር ይዘው ስለነበረ ባለቤታቸው ለሥራ ሲንጋፖር በመመደባቸው ትምህርታቸውን አቋርጠው ከባለቤታቸው ጋር ለመሄድ ተገደዱ።

በሄዱበት አገርም በሕፃናት አስተዳደግ ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎችን የወሰዱት እኚሁ ሴት በአሜሪካም በኢንትሪየር ዲዛይን የትምህርት መስክ ተምረውም ነበር። ሆኖም ሁለተኛ ልጃቸውን ወልደው ስለነበር ብዙም ሳይገፉበት ሙሉ ትኩረታቸውን ልጆቻቸውን ወደ ማሳደግ አዞሩ። ይህም ቢሆን ጎን ለጎን ራሳቸውን በእውቀት ለማበልፀግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር። በተለይም ሴቶችን የማማከር የተፈጥሮ ፀጋቸውን እያጎለበቱ በመምጣት የተጎዱ እናቶችን በሃሳብና በተለያዩ ነገሮች በመደገፍ የበኩላቸውን ሚናም ተጫውተዋል። በባለቤታቸው የሥራ ፀባይ ምክንያት የተለያዩ አገራትን የመጎብኘት ዕድሉን ያገኙት እኚህ ሴት በውጭ አገራት በቆዩባቸው 38 ዓመታት በተለይ በስደት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በመደገፍና በችግራቸው ሁሉ ቀድሞ በመድረስ የበጎ አድራጎት ሥራ ያከናውኑም ነበር። በዋናነትም የወያኔ አገሪቷን መቆጣጠር ተከትሎ አገራቸውንና ሕዝባቸውን ጥለው ወደ ኬንያ የተሰደዱ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት በመታደግና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ረገድ ያበረከቱት አስተዋፅ ተጠቃሽ ነው።

ወደአገራቸው ከተመለሱ በኋላም በደማቸው ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ያለባቸው በርካታ ሴቶች የሕክምና፣ የሥነ-ልቦና የስልጠና ድጋፍ እንዲያገኙ አድርገዋል። ከዚህም በተጨማሪ ራሳቸውን እንዲችሉ የሙያ ስልጠና በመስጠትና በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ የመኖር ተስፋቸውን ያለመለሙ አገር ወዳድ ሴት ስለመሆናው በሥራቸው አስመስክረዋል። ከዚህም ባሻገር በወህኒ ቤት ያሉ ሴት ታራሚዎችና የጎዳና ተዳዳሪዎች ላይ ፕሮጀክት በመቅረፅና ሌሎች ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር እገዛ እንዲያገኙ አድርገዋል። ካለፈው ሁለት ዓመታት ወዲህ ደግሞ ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ በአሸባሪው ሕወሓት ቡድን የተደፈሩ 100 ሴቶች ከደረሰባቸው የሥነ-ልቦና እና የአካል ጉዳት እንዲወጡ ያበረከቱት አስተዋፅኦ በብዙዎች ዘንድ ትልቅ አክብሮትን አስችሯቸዋል። እነዚህና ሌሎች በርካታ የበጎአድራጎት ሥራቸውን በሚመለከት የቤዛ ኮምዩኒቲ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን መሥራች የሆኑትን ወይዘሮ ሶፊያ አሰፋን አነጋግረናቸው እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።



ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሴ

**አዲስ ዘመን፡- እርሶና ባለቤትዎ ኬንያ በምትኖሩበት ጊዜ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ሕይወት በመታደግ ከፍተኛ ሥራ ማከናወናችሁ ይነገራል። እስቲ ስለዚህ ሥራችሁ ያስታውሱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**ወይዘሮ ሶፊያ፡-** እንደምታስታውሽው የደርግ ሥርዓት እንዳበቃ በርካታ ሕዝብ ወደ ኬንያና ወደ ሌሎች አገራት ተሰዶ ነበር። በተለይ ወደ ኬንያ የፈለሱ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከ20 ሺ በላይ የሚልቅ ነበር። በናይሮቢ መጠለያ ጣቢያ ከሰፈሩት ውጪ ቲካ በተባለ በረሃ ላይ የወደቀውና የሞተው፣ የአውሬ እራት የሆነው ከፍተኛ ቁጥር ያለው ነበር። ከእነዚህም መካከል የደርግ ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ ጀነራሎች፣ ኮሎኔሎች፣ ሚኒስትሮች ነበሩ። የኬንያ መንግሥትም ሆነ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተቀብላቸው እንጂ እርዳታ አልነበራቸውም። በነገራችን ላይ መጠለያ ጣቢያ የገቡት የታወቁ የደርግ ባስልጣናት ሲሆኑ ሜዳ ላይ ደግሞ ዝም ብሎ የፈሰሱ በርካቶች ነበሩ። ናይሮቢ ከተማ ጎዳና ላይ ወድቆ በረሃብ የሞተም አለ። በየመንገዱ ስንሄድ የተጎሳቆሉ ኢትዮጵያውያንን ስንመለከት ልባችን ክፉኛ ይሰበር ነበር። በኋላ ይህንን እያየን ዝም ማለት ስላልቻልን በአቅማችን ለመርዳት ተነሳን። የኬንያ መንግሥትን አስፈቅደን ናይሮቢ ባለ መጠለያ ጣቢያ ላይ ቦታ ተሰጥቶን ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን የሥነልቦና እና መንፈሳዊ ትምህርት እንሰጣቸው ነበር። ከትምህርቱ ጎን ለጎን ቤተ-መጽሐፍት ገንብተን የሚያነቡበትና ከተስፋ መቁረጥ ወጥተው አዕምሮቸውን የሚያበለፅጉበት ሁኔታን አመቻችተንላቸው ነበር። ይህም በተለይ ያሳለፉትን መጥፎ ታሪክ እንዲረሱ አድርጓቸዋል የሚል እምነት አለኝ።

ከዚህ በተጨማሪ በቲካ ካምፕ ውስጥ በበዓላት ጊዜ ደግሰን እናበላቸው ነበር። ናይሮቢ ከተማ ውስጥ ያሉት ደግሞ በጣም ብዙ ስለነበሩ በቀን እስከ 100 ሰው ድረስ በነፃ እናበላ ነበር። ዲቱር ወይም መመለስ በሚል መርሃግብራችን ደግሞ ወደ አውሮፓ ከሚሄዱት በተጨማሪ ወደ አገራቸው መመለስ ለሚፈልጉ ስደተኞች የተለያዩ ስልጠናዎች በመስጠት ሲመለሱ የራሳቸውን ሥራ የሚሠሩበትን ምቹ ሁኔታ ፈጥረንላቸው ነበር። እውነቱን ለመናገር ይሄ ፕሮግራም ባይዘጋጅ ኖሮ ብዙዎች ይሞቱ ነበር። በየቀኑ መቶ ሰው ማብላት ማለት ቀላል አይደለም። በነገራችን ላይ ከየትኛውም ድርጅት ድጋፍ ሳናገኝ በራሳችን ገቢ ነበር ይህንን ሁሉ ሰው እንመግብ የነበረው።

**አዲስ ዘመን፡- ወደ አገርዎ ከተመለሱ በኋላስ የበጎ አድራጎት ሥራ የጀመሩበት አጋጣሚ ምን ነበር?**

**ወይዘሮ ሶፊያ፡-** በመሠረቱ ይህ ለሰዎች ችግር ቀድሞ የመድረስና መርዳት ከልጅነት ጀምሮ ያደገብኝ ባህሪ እንደሆነ ነው የምረዳው። ሆኖም በተለይ እኔና ባለቤቴ ለ25 ዓመታት ኬንያ ናይሮቢ ከቆየን በኋላ የፈጣሪ ምሪትን ተቀብለን ነው ወደ አገራችን ለመመለስ የወሰነው። በተለይም «አገር በፅድቅ ይወረሳል፤ ፅድቅ ደግሞ አገርን ከፍ ከፍ ታደርጋለች» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልን መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያን መለወጥ አለብን ብለን ነው የተመለስነው። ልክ የዛሬ 17 ዓመት እንደመጣንም እንጦጦ ኪዳነ ምህረት አካባቢ ወደ አራት ሺ የሚሆኑ ሰዎች ላስቲክና ዛፍ ስር ወድቀው ተመለከትን፤ አንዳንዶቹም ልጆች አላቸው፤ በርካታ ወጣት ሴቶችና በዕድሜ የጠኑም ነበሩ። ሁሉም ሰዎች ታዲያ ኤች አይቪ እንዳለባቸው ሲያውቁ ብቻ ነው ለፀበል ብለው የመጡት። የሚበሉትም ሆነ የሚለብሱት አልነበራውም። የነበረውን አሳዛኝ ሁኔታ ስናይ በጣም ደነገጥን። ከዚያ ከኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን ጋር በመተባበር ማሰልጠኛ ቦታ ሰጥተውን በመጀመሪያ ስለኤች. አይ.ቪ. ማስተማር ጀመርን። በተለይም ራሳቸውን ከጠበቁ መኖር እንደሚችሉ፤ ከእነሱ ቀድሞ በሌላ በሽታ የተያዘ የሚሞትበት ዕድል ስለመኖሩ የሥነ-ልቦና ትምህርት ስንሰጥ ነበር።

እርግጥ እንደጀመርን ከፍተኛ ችግር አጋጥሞን ነበር፤ በተለይ ቄሶቹ ስለመድኃኒት እንድናስተምር የማይፈልጉ መሆናቸው ፈተና ሆኖብን ነበር። ምክንያቱም በዚያ ጊዜ መድኃኒቱ ብዙ አልታወቀም ነበር። በሂደት ግን በጥቂቱ መድኃቱን እየጀመሩ መጡ። ትምህርቱንም እየወሰዱ በሥነ ልቦናም እየታነፁ ትንሽ መጠናከር ጀመሩ። ከዚሁ ጎን ለጎን የሙያ ስልጠና እንዲሰጣቸው ተደረገ። በተለይም ከቡና ፍሬ ልዩ የሆነ ጌጣጌጥ ሥራ ስልጠና ወስደው እየሠሩ በመሸጥ ራሳቸውን ይደጉሙ ነበር። በባዛርና ውጭ አገር እስከመላክ የደረሱበት ሁኔታም ነበር። በኋላ ግን ሥራውን የጀመርነው በበጎ አድራጎት ድርጅት መልኩ ስለነበር የበጎ አድራጎት ድርጅት ደግሞ ገቢ በሚያመጡ ሥራዎች ላይ መሥራት አይችሉም ተባለና ተከለከልን።

በዚህ ምክንያት ድርጅቱን በቦርድ ይመሩ የነበሩ አንድ ግለሰብ ሥራውን ተረክበው ለብቻቸው ማካሄዱን ቀጠሉበት። ያም ቢሆን በርካታ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ሥራውን ገፍተውበት በግላቸው ሱቅ ከፍተው የቀጠሉ አሉ። በሽመና፤ ጡብ እና በተለያዩ ሙያ ነክ ሥራዎች ተሰማርተው የሚገኙትም ጥቂት አይደሉም። ከዚህ ባሻገር ተደራጅተው እንዲሠሩ የቁጠባ ማህበርም እንዲያቋቁሙ ድጋፍ አድርገንላቸዋል። አሁን በሚሊዮን የሚቆጠር ካፒታል ባለቤት ሆነዋል። ከእነሱ አልፎ ልጆቻቸውን እናስተምራለን፤ የተለያዩ ድጋፎችም እናደርግላቸዋለን። አሁን ላይ ኮሌጅ የደረሱት ልጆች ደግሞ ለሌሎቹ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት ያግዙናል።

ከዚህ በተጨማሪ ጋይንት የሚባል አካባቢ ሥነ-ምህዳሩና ተፈጥሮው እህል ለማብቀል በጣም አስቸጋሪና ድንጋያማ መሬት ያለ በመሆኑ ሕዝቡ በከፍተኛ ድህነት ውስጥ እንደሚኖር መረጃው ደረሰን። በተደጋጋሚ ረሃብ ስለሚያጠቃቸውም በሴፍትኔት ነው የሚኖሩት። የአካባቢው ነዋሪ ራሳቸውን በምግብ የሚችሉባቸውን በርካታ ፕሮጀክቶችን ነድፈን ወደ ሥራ ገባን። ከእነዚህም መካከል 100 የሚሆኑ የአካባቢው ሴቶች ባላቸው አነስተኛ መሬት ማረስና ምርታማ መሆን እንዲችሉ የሚያደርግ ስልጠና ከውጭ ባለሙያ በማምጣት አሰልጥነናቸዋል። በቤታቸው ማዳበሪያ በማዘጋጀት ነዋሪዎቹ ከጓሯቸው ጀምሮ አትክልትና ፍራፍሬ አምርተው ውጤታማ ሆነዋል። ከዚሁ ጎን ለጎን የፈትል ሥራ በስፋት እንዲሠሩ ምቹ ሁኔታ ፈጥረንላቸዋል። ልጆቻቸውም ትምህርት ቤት እንዲማሩ ተደረገ። ከኅብረተሰቡ ጋርም በጠንካራ ትብብር ነው የምንሠራው። መንግሥትም ይህንን ሥራ እንድናሰፋው ጠይቆናል። በተጨማሪም የተለያዩ ሙያዎችን በማሰልጠን ሥራ እንዲፈጥሩ አድርገናል። የተለያዩ የዕደ-ጥበብ ውጤቶችና ሌሎች ምርቶች ባዛር በማዘጋጀት እንዲሸጡ አመቻችተንላቸዋል።

በሌላ በኩል ሱርማ ማህበረሰብ ላይ የምንሠራው ሌላ ፕሮጀክት አለን። እነዚህ ማህበረሰቦች እንደሚታወቀው ከዘመናዊ አኗኗር ዘይቤም ሆነ ከልማት ወደኋላ የቀረ ከሚባሉ ኢትዮጵያውያን መካከል ዋነኞቹ ናቸው። አሁንም ድረስ ራቁት ሆነው የሚንቀሳቀሱ፤ በማደንና እርስ በርስ በመገዳደል የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው። በተከታታይ ጊዜ ኋላቀር የሆነውን የመገዳደል ባህላቸውን ጎጂነት ግንዛቤ እናስጨብጣለን፤ በትራኮማና በሌሎች የጤና ችግሮች እየተሰቃዩ ያሉ ነዋሪዎችንም የህክምና ቡድን ይዘን በመሄድ ህክምና እንዲያገኙ እናደርጋለን፤ አልባሳትና የተለያዩ ቁሳቁሶችንም እዚህ ያለውን ማህበረሰብ በማስተባበር ድጋፍ እናደርግላቸዋለን።

**አዲስ ዘመን፡- በወህኒ ቤቶችም የተለያዩ ሥራዎች እንደምትሠሩ ሰምተናል። እስቲ ስለዚህ ሥራችሁ በጥቂቱ ያጫውቱን?**

**ወይዘሮ ሶፊያ፡-** በወህኒ ቤቶች በዋናነት የምንሠራው የግብረ-ገብ ግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው የሥነ-ልቦና ትምህርት ነው የምንሰጠው። ይህም ታራሚዎቹ ትክክለኛ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡና ከእስር ሲወጡ ከማህበረሰቡ ጋር በሰላም መኖር እንዲችሉ የሚያደርግ ነው። ሴት ታራሚዎች ጋር በተለይ ዕድሉ ሲገኝ የንፅህና መጠበቂያዎችን እንሰጣቸዋለን። ይህንንም የምናደርገው ከዚህ ቀደም ሴት እስረኞች የንፅህና መጠበቂ እጥረት ስላለባቸው ብርድልብሳቸውን ቀደው እንደሚጠቀሙ ሰምቼ ልቤ ክፉኛ ስለተነካ ነው። አንድ ክረምት ላይ እንዲያውም ጨርሶ ብርድልብስ የሌላቸው ሴት እስረኞች አጋጥመውናል። ስለዚህ ለእያንዳንዱ እየታጠበ ዳግመኛ መጠቀም የሚያስችል የታሸገ የንፅህና መጠበቂያ (ሞዴስ) እናከፋፍላለን። ይህንን የንፅህና መጠበቂያ ደግሞ የሚሠሩት እኛ የምንረዳቸውና አሰልጥነን ሥራ የፈጠርንላቸው ሰዎች ናቸው። እስካሁን ገና ሁለት ወህኒ ቤቶች ላይ ብቻ ነው የሠራነው። በመጀመሪያው ዙር 60 ሴት ታራሚዎችን ፤ በሁለተኛው ደግሞ 40ዎቹን የግንዛቤ ማስበጫና ድጋፍ ነው ያደረግንላቸው።

ከዚህ በተጨማሪ ዝዋይ ላይ የጎዳና ልጆችን

### ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

በመሰብሰብ ትምህርት የምናስተምርበት መርሃ ግብር አለ። በተለይ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ጠንካራና ተከታታይ ሥራ ነው የሚሠራው። ልጆችን ብቻ ሳይሆን ኑሯቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ እናቶችንም እንረዳለን። ይህም በጣም አበረታች ለውጥ እያመጣን ካለንበት ሥራዎች መካከል የሚጠቀስ ነው። እነዚህ እናቶች ከወንዶቹ በላይ ተጎጂ በመሆናቸው ነው በዋናነት ትኩረት የምናደርገው።

እንዳልኩሽ ከሴቶች ጋር መሥራት ከጀመርን በጣም በርካታ ዓመታት አስቆጥረናል። እንደእኔ የሴቶች ጉዳይ የሚያሳስባቸውና ሴቷ ተጠቃሚ እንድትሆን ፅኑ ፍላጎት ካላቸው የተለያዩ ሰዎች ጋር በየጊዜው ዓለምአቀፍ ጉባኤ እናደርጋለን። እስካሁን በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ በስፋት ተከናውኗል። በዚያ ጉባኤ ላይ ከተለያዩ አገራት ሴት ኢትዮጵያውያን ተሰባስበን ሴት በአገር እድገት ያላትን ዋጋ ለሁሉም ማሳወቅና በተግባርም ማረጋገጥ በምንችልባቸው ጉዳዮች ላይ እንመክራለን። በተለይ ባህል የተማረችውንም ሴት ሳይቀር ተፅዕኖ የሚፈጥር እንደመሆኑ ሥርታ ማደግ፤ አገርን በብቃት መምራት እንደምትችል በተጨባጭ ለማሳየት እገዛ የምናደርግበት መድረክ ነው። ከዚህም አልፎ ጤነኛና ብቃት ያላቸውን አገር ተረካቢ ልጆችን የማፍራት ኃላፊነት በዋናነት የእኛ የእናቶች እንደመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ እንመክራለን።

በኢትዮጵያ ደግሞ «ቡና ጠጡ» የሚል መርሃ-ግብር አለን። እርግጥ የዚህ መርሃ-ግብር መነሻው የማህበረሰባችን ቡና የመጠራራት የቆየ የማህበራዊ እሴት አካል ነው። እንደሚታወቀው ደግሞ ይህ የቡና መጠጣት ሥርዓት የውይይት መድረክ የሚፈጥርና በዚህም ብዙ ችግሮቻችንን የምንፈታበት ትልቅ ባህላዊ እሴታችን ነው። እኛም ይህንን ባህላዊ የመገናኛ መድረክ በመጠቀም ሴቶች ያለባቸውን ችግር አቅርበው የመፍትሄ ሃሳብ እንዲመነጭ ይደረጋል፤ በየጊዜው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በመምከር ግንዛቤ እንፈጥራለን። ላለፉት 17 ዓመታት በየሦስትና አራት ወራት በየጊዜው እየተገናኘን ቡና እየጠጣን ነው የምንመክረው። በቅርቡ ባካሄድነው የቡና ጠጡ መርሃ-ግብር አጀንዳ አድርገን ያነሳነው በወላጆችና በአዲሱ ትውልድ መካከል የአስተሳሰብ ክፍተት ላይ ነው ።

በተለይም ከዘመን አመጣሽ መጤ ባህሎች ተጋላጭነት እንዴት መታደግ እንደምንችል እንዲሁም ልጆቻችን በምን መልኩ ልናስተምር እንደሚገባ ሰፊ ውይይት አድርገናል። በዋናት በማህበራዊ ሚዲያው አማካኝነት በእምነትም ሆነ በባህል ውግዝ የሆነው ግብረ-ሰዶማዊነት ተጋላጭ እየሆኑብን ስለሆነ እኛ በቂ እውቀት ይዘን እንዴት ልጆቻችን መታደግ እንደሚገባ በስፋት ተመካክረናል። ከዚህ ቀደም ደግሞ በባህል አልባሳት ትውልዱ በምን መልኩ ሊያዘወትር ይገባል? በሚል ርዕሰ ዙሪያ ውይይት ካደረግን በኋላ ለአንድ አራት ሴቶች ዲዛይን እንዲሠሩ ተደረገ። ትውልዱ በየዕለቱ ሊለብሳው በሚችል መልኩ በዘመናዊ መንገድ ተሠርተው ለገበያ ቀርበዋል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደማንኛው ኢትዮጵያዊ እናት ልጆችዎን በማሳደግና ለቁምነገር ለማድረስ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል፤ ግን ደግሞ ተስፋ ሳይቆርጡ ያልዎትን አቅምና ችሎታ ወገኖችን ለመርዳት ተጠቅመው ውጤታማ ሆነዋል። ለመሆኑ ይህንን ማሳካት የቻሉበት የተለየ ምስጢር ይኖር ይሆን?**

**ወይዘሮ ሶፊያ፡-** እውነት ለመናገር ስለእኔ ማንነትና እዚህ መድረስ ሳስብ ከሁሉ በላይ ፈጣሪዬን ነው ማመስገን የምፈልገው። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ከሚፈራ ቤተሰብ ስለመጣሁ እሱን በመፍራትና እንደሚገባኝ ቤተሰቤን እየመራሁ የኖርኩት። በሁለተኛ ደረጃ ለእኔ ሕይወት እንደትልቅ አርዓያ የማየውና መሠረት የጣለው ወላጅ አባቴ ነው። ምክንያቱም አባቴ ብዙ ሰዎች ያላገኙትን በፍቅርና በእውቀት ቀርፆ ነው ያሳደገኝ። ማንኛውም ነገር እንደምችልና በራሴ እንድተማመን ያበረታታኝም ነበር። ሴት በመሆኔ ተስፋ እንዳልቆርጥ ይደግፈኝ ነበር። በመሠረቱ ለእኔ ልጆቼን ማሳደግና ለቁም ነገር ማድረሱ በራሱ ከዲግሪም ሆነ ከስልጣን በላይ ነው። ልጆቼ አሁን ለደረሱበት ከፍተኛ ቦታ የእኔ መስዋዕትነት መክፈል ግድ ስለነበር ነው። እኔ በወቅቱ ራሴ ላይ ብቻ ባተኩር ኖሮ አሁን የደረሱበት ቦታ አይደርሱም ነበር።

ልክ እንደእኔ ብዙ እናቶች ጥቅማቸውንም ሆነ ፍላጎታቸውን ለቤተሰባቸው በመስጠትና በመኖር ለሌሎች መስዋዕት ሆነዋል። ያ ምንአልባት ከፍተኛ ደረጃ ከደረሰው ባለስልጣን እኩል በማህበረሰብ ዘንድ ባያስመለክተንም ያንን ከፍተኛ ባለስልጣን ያለበት ደረጃ ያደረስነው እኛ እናቶች ስለመሆናችን ሊዘነጋ አይገባም። ብዙ ጓደኞቼ ዶክተርና ሌላም ነገር መሆን ችለዋል፤ እኔም ከፈጣሪ የተሰጠኝ ልጆች በመልካም ሥነ-ምግባር የማነፅና የማሳደግ ተልዕኮ በስኬት በማጠናቀቄ በዚህ ከፍተኛ ደስታ ይሰማኛል።



**ጦርነቱ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ጎድቷል። አርሶአደሩም ምርቱን አጥቷል፤ ነጋዴው ኪሳራ ውስጥ ገብቷል፤ ንፁሃን ከየቀያቸው ተፈናቅለዋል፤ ተሰደዋል፤ ቆስለዋል፤ ሞተዋል። በተለይ የሴቶች ጉዳት እጅግ ከባድ ነው። በዚህ ጦርነት እናት ዘጠኝ ወር ተሸክማ፣ አምጣ፣ወልዳና አጥብታ ለፍታ ያሳደገቻቸውን ልጆቿን አጥታለች፤ የቤቷ መሪ የሆነው ባሏን መስዋዕት አድርጋ ብቻዋን ቀርታለች። በዚህም ዘላቂ ለሆነ የሥነ- ልቦና ጉዳት ሰለባ ሆናለች**

ማንኛዋም እናት የጎላ የገንዘብ ችግር ከሌለባት በስተቀር ልጆቿን በሞግዚት እንዲያድጉ መፍቀድ የለባትም። ምክንያቱም ራሷ ቀርፃ ያላሳደገችው ልጅ ነገር አገር ተረካቢ ትውልድ ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም። ይህ ማለት ሴት መማርና ወጥታ መሥራት የለባትም እያልኩኝ አይደለም። ሴት በጣም መማርና ራሷን ማሳደግ እንዳለባት አምናለሁ። ግን ደግሞ ከዚሁ ጎን ለጎን ወደዚህ ምድር ላመጣቻቸው ልጆች የበለጠውን ኃላፊነት ወስዳ ማሳደግ ይገባታል ባይ ነኝ። ደግሞም የትኛውም ሴት ብትሆን ልጆቿን ራሷን መስዋዕት ማድረጓ ሊቆጫት አይችልም። አሁን እኔ ለልጆቼ ያን ያህል መስዋዕትነት ከፍዬ በማሳደጌ ልጆቼ ከፍተኛ የሚባል ደረጃ ደርሰውልኛል፤ አገራቸውን የሚወዱና ወገኖቻቸውንም የሚደግፉ ናቸው። በሚሠሩት ሥራ ለበርካቶችም የሥራ ዕድል ፈጥረዋል። ስለዚህ ትምህርት ቤት ብቻ በመሄድ እውቀት አይገኝም። በየዕለት ተዕለት ኑሯችን ራሳችንን ማስተማርና ማሳደግ ይቻላል ብዬ አምናለሁ። እኔ እስካሁን ተማሪ ነኝ ብዬ ነው የማስበው። መጽሐፍት በማንበብም ሆነ በሕይወት ተሞክሮ መማር ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ባለፉት ሁለት ዓመታት ድርጅታችሁ በጦርነት የተጎዱና የተደፈሩ ሴቶችን እየረዳ መሆኑ ይታወቃል። እስኪ ስለ ሥራችሁ ያብራሩልን?**

**ወይዘሮ ሶፊያ፡-** ስለእነዚህ ሰዎች በመጀመሪያ የሰማሁት ጎንደር ጋይንት አካባቢ ሄዶ ሴቶች ያሉበትን ሁኔታ ከተመለከተ ሰው ነው። እነዚህ የተደፈሩ ሴቶች የደረሰባቸው በደል አልበቃ ብሎ በማህበረሰቡ ተገልለው በር ዘግተው በችግር መቀመጣቸውን ስሰማ ክፉኛ ልቤ አዘነ። በምን መልኩ ላግዛቸው እንደምችል አሰብኩና ዓለምአቀፉ ቤዛ ኢንተርናሽናል ማህበር አባላትን በዙም ስብሰባ ጠርቼ አማከርኳቸው። ሁላችንም ገንዘብ አዋጥንና ጋይንትና ንፋስ መውጫ ባለን ጽሕፈት ቤታችን አማካኝነት ገንዘብና «አንቺም አርበኛ ነሽ፤ አሸንፈሻል» የሚል ጽሑፍ ያለው ሜዳሊያ እንዲደርሳቸው ተደረገ። ይህንን ያደረግንበት ምክንያት እነዚህ በአሸባሪ ቡድኑ የተደፈሩ ሴቶች በጦርነት ሜዳ ላይ ከተዋጋው ወታደር እኩል ለአገራቸው ዋጋ የከፈሉ ናቸው ብለን ስለምናምን ነው።

እነሱ ላይ የደረሰው ነገር የጦርነቱ ጠባሳ ነው። ልክ ወታደር አገሩን ለማዳን ሲል አካሉን እንደሚያጣ ሁሉ እነዚህም ሴቶች በወራሪው ኃይል ጥቃት ደርሶባቸዋል። ሆኖም በጥቃቱ አልሞቱም፤ አሸንፈው ዛሬም በሕይወት መኖራቸው ትልቅ ድል እንደተቀናጁ ነው ሊቆጠር የሚገባው። የሥነልቦና ባለሙያዎችን በመላክም የተጎዳ ሥነልቦናቸው እንዲጠገንና ያለእፍረት ቀና ብለው እንዲሄዱ እገዛ አድርገንላቸዋል። ማህበረሰቡም እነዚህ ሴቶች ለአገር የከፈሉት ዋጋ መሆኑን ተገንዝቦ እነሱን እንዳያገል ተከታታይ ትምህርት ሰጥተናል። በዚህ ስልጠና ላይ 100 የሚሆኑ ሴቶች እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበን 70ዎቹ ናቸው የተሳተፉት። እኛ በነበረው አለመረጋጋት በአካል እዚያ ባንገኝም በተወካዮቻችን አማካኝነት ለእነሱ ያለንን ፍቅርና ያለንን አክብሮት የሚገልፅ ደብዳቤ ልከን እንዲነበብላቸው ተደርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ተገዳ ለሦስተኛ ዙር ስለገባችበት ጦርነት ያለዎት ምልከታ ምንድን ነው? በዚህች አገር ዘላቂ ሰላም ለማምጣትስ ምን መሠራት አለበት ብለው ያምናሉ?**

**ወይዘሮ ሶፊያ፡-** ጦርነቱ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ጎድቷል። አርሶአደሩም ምርቱን አጥቷል፤ ነጋዴው ኪሳራ ውስጥ ገብቷል፤ ንፁሃን ከየቀያቸው ተፈናቅለዋል፤ ተሰደዋል፤ ቆስለዋል፤ ሞተዋል። በተለይ የሴቶች ጉዳት እጅግ ከባድ ነው። በዚህ ጦርነት እናት ዘጠኝ ወር ተሸክማ፣ አምጣ ወልዳና አጥብታ፤ ለፍታ ያሳደገቻቸውን ልጆቿን አጥታለች፤ የቤቷ መሪ የሆነው ባሏን መስዋዕት አድርጋ ብቻዋን ቀርታለች። በዚህም ዘላቂ ለሆነ የሥነ- ልቦና ጉዳት ሰለባ ሆናለች። አርሶ እና ሸምቶ የሚያበላቸውን ባለቤታቸውን አጥተው ለረሃብና ለእንግልት ተዳርገዋል። እነዚህ ሰዎች ልባቸው በልጅ ኀዘን የተመታና በመንፈስም የጎበጡ ናቸው። እንዳልኩሽ ደግሞ ይህ ሁሉ ግፍ ደርሶባቸው ሳለ የሚረዳቸው ወገን አጠገባቸው የለም። አሁን በየከተማውና ሜዳ ላይ ወድቀው ሲለምኑ የምናያቸው ሴቶች ኢትዮጵያ ተገዳ በገባችበት ጦርነት ምክንያት ቀያቸውን ለቀው የወጡ ናቸው። በጦርነቱ ልጇንና ባሏን ማጣቷ አልበቃ ብሎ አሁንም የሚጠባ ሕፃን ይዛ በሰቆቃ እየተገረፈች ያለችው ይህችው ምስኪን እናት ናት። ከዚያ በተጨማሪ ደግሞ ተደፍራ ላላስፈላጊ እርግዝና እና በሽታ የተዳረገችውንም ማሰብ ከባድ አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት ችግሩ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ የበኩሉን ጥረት ቢያደርግም በአሸባሪው ቡድን በኩል የሰላም ፍላጎት ባለመኖሩ ለሦስተኛ ጊዜ ጦርነት ጀምሯል። ይህን የሕወሓትን እብሪት እንዴት ያዩታል ?**

**ወይዘሮ ሶፊያ፡-** እኔ ፖለቲከኛ ስላልሆንኩኝ ፖለቲካ ውስጥ መግባት አልፈልግም። ግን ደግሞ ለእዚህ ቡድን ጦርነት እንዲያቆሙ ነው ጥሪ ማስተላለፍ የምፈልገው። እንዳልሽው ወደ ጦርነት ላለመግባት ችግሮችን በሰላም ለመፍታት በመንግሥት በኩል እየተደረገ የነበረውን ጥረት ሁሉ አደንቃለሁ። ሰላም ለማስፈን ከሚደረገው እንቅስቃሴ ጎን ለጎን የተሠሩ የልማት ሥራዎችም መንግሥትን የሚያስመሰግኑ ናቸው። በተለይ በአረንጓዴ ልማትና በምግብ ራስን ለመቻል የተሠሩት ሥራዎች የሚበረታቱ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡-ቀረ የሚሉት ማስተላለፍ የሚፈልጉት ሀሳብ ካለዎት ዕድሉን ልስጥዎት?**

**ወይዘሮ ሶፊያ፡-** ከዚህ ጋር አያይዤ መናገር የምፈልገው ነገር በአገራችን በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ ስለመጣው ሌብነት ጉዳይ ነው። በግሌ በግልፅ ያጋጠመኝ ነገር ባይኖርም በዙሪያዬ ያሉ ሰዎች የሚያልፉበትን ነገር በየቀኑ አያለሁ። ከዚህ ከነበረው በበለጠ ሁኔታ ሁሉም ነገር በጉቦ ነው እየተሠራ ያለው። የትኛውም ተቋም ላይ ሄደሽ ያለጉቦ የሚገኝ አገልግሎት የለም። ይህ ደግሞ እንደሕዝብ ትልቅ የአስተሳሰብ አዘቅት ውስጥ ነው የከተተን። አሁን እኮ አይን ያወጣ ሌብነትነው በመንግሥት ባለሥልጣናትና ፈፃሚዎች ላይ የምናየው።

ለእነዚህ ጉቦ ለሚጠይቁ ሁሉ ሰዎች ማስተላለፍ የምፈልገው ነገር ከሕዝብ ጉሮሮ ነጥቆ ከመብላት አፀያፊ ተግባራቸው እንዲታቀቡ ነው። ሞኝነት ነው እንጂ ሕዝብ እያስራቡና እያስቸገሩ ለብቻ የትም መድረስ አይቻልም። ያማረሩት ሕዝብ ነገ መልሶ እነሱ ላይ መነሳቱ ስለማይቀር ከዚህ ተግባራቸው በአፋጣኝ ሊወጡና ሕዝቡን በቅንነትና በታማኝነት እንዲያገለግሉ ነው። ደግሞም ከሕዝብ አግበስብሶ በስርቆት የተወሰደ ነገር ሰላምም ሆነ በረከት የለውም። ሁልጊዜ የህሊና ወቀሳ የሚያስከትል በመሆኑ ሌባው ግለሰብ ጤና አይኖረውም። በመሠረቱ ሌብነት ለራስ ዋጋ አለመስጠት ነው። ስለዚህ ከዚህ መጥፎ ተግባር መውጣት ለራስም ህሊና ነፃነት ይሰጣል።

**አዲስ ዘመን፡- ለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ወይዘሮ ሶፊያ፡-** እኔም ሃሳቤን እንድገልፅ ዕድሉን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# ፓርኪንሰን

እፀገነት አክሊሉ

ሰዎች ሳይፈልጉ ወይም ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆነ መንገድ ሰውነታቸው እንዲንቀሳቀስ ወይም እንዲንቀጠቀጥ የሚያደርገው ህመም ፓርኪንሰን በመባል ይታወቃል። የአንጎል ውጫዊ ሥርዓት ላይ በሚከሰት መዛባት እንደሚመጣ ለሚነገረው ለዚህ ህመም የተጋለጡ ሰዎች ሚዛናቸውን መጠበቅ እንደሚያቅታቸው ጥናቶች ያሳያሉ።

የጤና ጉዳይ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ፓርኪንሰን የተሰኘው ህመም በአንጎል ላይ በሚያጋጥም መዛባት ምክንያት የሚከሰት ሲሆን ምልክቱ ከታየ በኋላ ቀስበቀስ እየባሰ የሚሄድና እየተባባሰ በሚሄድበት ጊዜም ታማሚዎቹ ለመራመድ እና ለመነጋገር የሚቸገሩበት ደረጃ ላይ የሚያደርስ ነው። ከዚህ ውጪም የህመሙ ተጠቂ የሆኑ ሰዎች ችግሩ ከደረሰባቸው በኋላ በሥነ-ልቡናም ሆነ በባህሪያቸው ላይ ካፍ ያሉ ለውጦችንም ማሳየት ይጀምራሉ።

ለምሳሌ እንቅልፍ ማጣት፣ ድብርት፣ ነገሮች የማስታወስ ወይም ደግሞ የመለየት ችግሮች ሊያጋጥሟቸው እንደሚችሉ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ። እንደ መረጃዎቹ ከሆነ ምንም እንኳን ማንኛውም ሰው ለዚህ የጤና እክል የተጋለጠ ቢሆንም አንዳንድ ጥናቶች የሚያሳዩት ከሴቶች ይልቅ ወንዶች በፓርኪንሰን በሽታ የመያዝ ዕድላቸው ሰፋ ያለ መሆኑን ነው።

ዕድሜን በተመለከተም በአብዛኛው 60 ዓመት እና ከዚያ በላይ በሆናቸው ሰዎች ላይ ህመሙ ጎልቶ ቢታይም ከ50 ዓመት ጀምሮም ሆነ ከዚያ በታች ባሉ ሰዎች ላይም ሊያጋጥም እንደሚችል መረጃዎች ያመለክታሉ።

እናም የዕድሜ ጉዳይ ሲታሰብ ብዙኃኑ በዕድሜ የገፉ ይሁኑ እንጂ ችግሩ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ ባሉት ላይ ሊከሰት እንደሚችል ማወቅ ያስፈልጋል።

ህመሙ እንዲከሰት መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም አንድ ሰው በፓርኪንሰን ህመም ተጠቅቷል ወይም ለበሽታው ተጋልጧል ለማለት ሰፋ ያለ ምርመራ እንደሚያስፈልግ የህክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ። የመንቀጥቀጥም ሆነ ሌሎቹ ምልክቶች መታየት የሚጀምሩት በብዛት በሽታው ስር ከሰደደ በኋላ ነው። እናም ታማሚዎች የግድ ሰፋ ያለ የሀኪም ምርመራ እና ተገቢው የህክምና ክትትል ማግኘት ይኖርባቸዋል።

የፓርኪንሰን በሽታ የነርቭ ሥርዓትን የሚነካ እና የአንጎል ሥራን የሚቀይር የነርቭ-ነክ በሽታ ነው። በአስደናቂው ገጽታ ምክንያት ብዙውን ጊዜ የአንጎል ክልሎችን ያበላሻል፣ በእንቅስቃሴ ላይ ከሚታዩት የበለጠ ብዙ ሁከት ያስከትላል። ስለ ፓርኪንሰን በሽታ የመጀመሪያ መግለጫ በ 1817 በሐኪሙ ጄምስ ፓርኪንሰን «አነቃቂ ሽባነት» በሚል የተገለጸ ሲሆን በኋላ ላይ የነርቭ ሐኪሙ ቻርኮት የአሁኑን የፓርኪንሰንስ በሽታ ስም ሰጠው።

### በነርቭ ሥርዓት ላይ እንዴት ተጽዕኖ ያሳድራል?

የፓርኪንሰን በሽታ የነርቭ ሥርዓትን የሚነካ የነርቭ በሽታ ነው። ይህ ዓይነቱ የነርቭ ሴሎችን (ዶፓሚን በሚባል ንጥረ ነገር ተመስሏል) ብዙ ቁጥር ያላቸው የአንጎል እንቅስቃሴዎችን ያካሂዳሉ፣ ከእነዚህም መካከል እንቅስቃሴ መቆጣጠር ጎልቶ ይታያል። ሆኖም በአዕምሯችን ውስጥ የዶፓሚን እና የዶፓሚንጂጂ ኒውሮኖች ተግባር የሞተር ሥራን በመቆጣጠር ብቻ የተገደቡ አይደሉም፣ እንደ ትውስታ፣ ትኩረት፣ እንቅልፍ፣ ቀልድ እና ህመም መከልከል ባሉ ሌሎች አሠራሮች ውስጥም ጣልቃ ይገባሉ።

ለዚያም ነው፣ የፓርኪንሰን በሽታ ዋና ዋና ምልክቶች የእንቅስቃሴ መታወክ ቢሆኑም፣ በሽታው ከእነዚህ የዶፓሚንጂጂክ ነርቮች ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ምልክቶችን ሊያመርት የሚችል እንደሆነ ነው መረጃዎች የሚያመለክቱት። በተጨማሪም የፓርኪንሰን በሽታ እንዲሁ እንደ ‹ሴፖቶኒን› ፣ ኖረፒንፈሪን ወይም አሴቲልቾሊን ያሉ ከዲፖሚን ባሻገር ሌሎች ንጥረ ነገሮችን እንደሚጎዳ ተረጋግጧል። ይህም የፓርኪንሰን በሽታ በርካታ ቁጥር ያላቸውን ችግሮች ሊያስከትል ይችላል የሚለውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የፓርኪንሰን በሽታ ሥር የሰደደ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ የፓርኪንሰንን በሽታ ለማጥፋት የሚያስችል ህክምና ባለመኖሩ እና በሽታው እየገፋ በሄደ መጠን በከፍተኛ ጥንካሬ ራሱን የሚያሳይ በመሆኑ ብዙ ሰዎች የበሽታው ሁኔታ እየታየባቸው ስለመሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ።



### የፓርኪንሰን በሽታ ምልክቶች

የዚህ በሽታ ዋና ምልክቶች ከእንቅስቃሴዎች ቅንጅት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው። በፈቃደኝነት የሚንቀሳቀሱ እንቅስቃሴዎችን መቆጣጠር በአዕምሮአችን ውስጥ የሚከናወነው በአንጎል አንጀት ውስጥ በሚገኝ ኒፓራ ውስጥ በሚገኙ dopaminergic neurons በኩል ነው። የፓርኪንሰን በሽታ በሚታይበት ጊዜ የእነዚህ ነርቮች ሥራ የሚለወጥ ሲሆን ቀስ በቀስ እየተበላሹ ይሄዳሉ በአካባቢው ላይ ያሉት ነርቮች መሞት ይጀምራሉ። ስለሆነም አንጎላችን ይህን ዓይነቱን እርምጃ ለመፈፀም የሚያስችላቸውን ስልቶች ያጣል፣ ከዚህ የተነሳ ደግሞ መቼ እና እንዴት መንቀሳቀስ እንዳለባቸው መልእክቶች በተሳሳተ መንገድ ይተላለፋሉ።

### መንቀጥቀጥ

የዚህ በሽታ ችግር ያለባቸው ሰዎች 70 በመቶው የሚሆኑት እንደ መጀመሪያው መንቀጥቀጥ ስለሚታዩ ይህ ምናልባት የፓርኪንሰን በሽታ ዋና ምልክት ሊሆን ይችላል። ይህ የፓርኪንሰንስ ምልክት በሚያርፍበት ጊዜ በመንቀጥቀጥ ይታወቃል።

መደበኛው ነገር እንደ እጆቻቸው፣ እግሮቻቸው፣ እጆቻቸው ወይም እግሮቻቸው ባሉ ጫፎች ውስጥ መታየታቸው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እንደ መንጋጋ፣ ከንፈር ወይም ፊት ባሉ የሰውነት ክፍሎች ላይ ሊታይ ይችላሉ። አንድ የተወሰነ እንቅስቃሴ ሲያከናውን ይህ መንቀጥቀጥ ብዙውን ጊዜ የሚቀንስ ሲሆን በጭንቀት ሁኔታዎች ውስጥ ሲገባ ደግሞ መንቀጥቀጡ ይጨምራል።

በሽተኛው እንቅስቃሴን የሚያካትት ሥራን ለማከናወን ብዙ ጊዜ ይወስድበታል። ለምሳሌ እንደ ቁልፍ መክፈት፣ የተለያዩ ነገሮችን መስፋት፣ መጻፍ ወይም ምግብን በመመገብ በኩል ያሉ የተወሰኑ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የማያስችል ነው።

የፓርኪንሰን በሽታ ጡንቻዎቹ ይበልጥ እንዲወጠሩ እና በትክክል ዘና ብለው እንዳይንቀሳቀሱ ያደርጋቸዋል። በዚህ መንገድ ጡንቻዎች (ብዙውን ጊዜ የአካል ክፍሎች) ይበልጥ ግትር ሆነው ይታያሉ፣ ይህ ደግሞ የእንቅስቃሴዎቻቸውን መጠን ያሳጥራል፣ የመዞር ችሎታን ይቀንሰዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሁልጊዜ በውጥረት ውስጥ መሆን ህመም እና ቁስል የመያዝ ዕድሉ ሰፊ ሲሆን ጥንካሬው የፊት ጡንቻዎችን በሚነካበት ጊዜ ገላጭነት ይቀንሳል።

የፓርኪንሰን በሽታ እየገፋ በሄደ ቁጥር ታማሚዎች ሊንጠለጠሉ ይችላሉ፣ ይህም ሚዛኑን እንዲዛባ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ይህ ለውጥ በታካሚው ላይ አለመረጋጋትን ሊፈጥር ስለሚችል ከወንበር መነሳት፣ መራመድ ወይም መታጠፍ ባሉ የተለመዱ ሁኔታዎችን ማከናወን ስለማይቻል በሽተኞች እንቅስቃሴ ለማድረግ ሲሞክሩ የመውደቅ አደጋ ያጋጥማቸዋል።

### የመርሳት በሽታ

ከ 20 እስከ 60 በመቶ የሚሆኑት የፓርኪንሰን በሽተኞች በፓርኪንሰን በሽታ ምክንያት የመርሳት በሽታ (ሲንድሮም) ያጋጥማቸዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት በሽታው የሚያመነጨው እና በአእምሮ ላይ የሚያደርሰው ከፍ ያለ ጉዳት እንዲሁም ከሰውዬው የግንዛቤ ችሎታ ጋር የተዛመዱ የአንጎል አሠራሮችን ስለሚቀይር ነው። የፓርኪንሰን በሽታ ህመምተኞች የአእምሮ አቅም ውስውን ስለሚሆን ነገሮችን መርምሮ ለመረዳት ከጤነኛው ሰው በተለየ ሁኔታ ሰፋ ያለ ጊዜን ይፈልጋሉ።

በተራቀቁ ደረጃዎች ውስጥ የእይታ-የማሰብ ጉድለቶች ይታያሉ፣ እና የማስታወስ እጥረቶች፣ በተለይም ያለፉትን ክስተቶች የመማር እና የማስታወስ ክህሎት በአብዛኞቹ ህመምተኞች ላይ የወረደ ነው የሚሆነው።

ቋንቋን በተመለከተም የፓርኪንሰን ህመምተኞች በሚናገሩበት ጊዜ አፋቸውን በጣም የመያዝ አልፎ አልፎም ቋንቋዎችን ለማውጣት እስከመቸገር የሚያደርስ ችግር ያስከትልባቸዋል፤ በዚህም ምክንያት በቃላት አጠራር ላይ ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ።

በሌላ በኩልም የፓርኪንሰን ታማሚዎች የሚኖሩበትን ቀን ፣ ሳምንት ፣ ወር ወይም ዓመት አለማስታወስ እና የቦታ፣ የመንገድ ሁኔታዎችን አለማወቅ ይከሰትባቸዋል።

### ድብርት

የፓርኪንሰን በሽታ ያለባቸው ታማሚዎች በስሜት መለዋወጥ በተደጋጋሚ ይሰቃያሉ፣ እናም ድብርት ብዙውን ጊዜ እንደ ዋና ምልክት ሆኖ ይታያል። ከ 25 እስከ 70 በመቶ የሚሆኑት የፓርኪንሰን ሕመምተኞች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ አስጨናቂ ስዕል ይታይባቸዋል። አንድ ሰው በተራበ ጊዜ ሲበላ፣ ሲጠማ ሲጠጣ ወይም በማንኛውም ሌላ አስደሳች እንቅስቃሴ ውስጥ ሲሳተፍ ዶፓሚን የተባለው ንጥረ ነገር በአንጎል ውስጥ ይወጣል፣ ይህም የደህንነትን እና እርካታን ስሜት ይፈጥራል። ሆኖም የፓርኪንሰን በሽታ በአንጎል ውስጥ የዚህን ንጥረ ነገር ስለሚቀንስ የዚህ በሽታ ህመምተኞች ከፍተኛ የመንፈስ ጭንቀት የመያዝ አዝማሚያ ይታይባቸዋል። በፓርኪንሰን በሽታ ምክንያት የሚከሰት የመንፈስ ጭንቀት በከፍተኛ ደረጃ ከፍተኛ ለሆነ ተስፋ መቁረጥ እና በቋሚነት ብስጭት እና በጭንቀት ውስጥ ያስገባል። ሆኖም፣ የጥፋተኝነት ሀሳቦች፣ እራስን ነቀፋ እና ዝቅተኛ በራስ የመተማመን ስሜቶች በጣም ጥቂት ናቸው፣ ብዙውን ጊዜ በሌሎች የመንፈስ ጭንቀት ዓይነቶች በጣም የተለመዱ ምልክቶች ናቸው። እንደዚሁም በፓርኪንሰን በሽታ የመንፈስ ጭንቀት ምልክቶች ሰውዬው ለነገሮች እምብዛም ተነሳሽነት እንደሌለው፣ እንቅስቃሴዎቻቸውን የበለጠ እንዲዘገዩ እና ትኩረታቸውን አለመሰብሰብ፣ የዘገየ አስተሳሰብ እና የማስታወስ እክል እንዲባባስ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

### የእንቅልፍ መዛባት

የእንቅልፍ መዛባት በፓርኪንሰን በሽታ ዓይነተኛ ችግር ነው። እንቅልፍ ማጣት እና የእንቅልፍ መቆራረጥ ብዙውን ጊዜ ሌሊት ላይ በተደጋጋሚ መንቃቶች ይታያሉ። በፓርኪንሰን በሽታ ውስጥ ሌላኛው ተደጋጋሚ ችግር የቀን እንቅልፍ ነው ፣ በዚህ የቀን እንቅልፍ ውስጥ ደግሞ አልፎ አልፎም ቢሆን ግልፅ ህልሞችና የሌሊት ድምፆች ሊሰሙ ይችላሉ። በአሁኑ ጊዜ የፓርኪንሰን በሽታ መንስኤ ምን እንደሆነ አይታወቅም፣ ግን እንደ አብዛኛዎቹ የነርቭ በሽታዎች ፣ የእሱ ገጽታ በጄኔቲክ እና አካባቢያዊ ምክንያቶች ጥምር እንደሆነ በመወሰን የተወሰነ መግባባት አለ።

### እርጅና

ዕድሜ ለፓርኪንሰን በሽታ አደገኛ አጋላጭ መንስኤ መሆኑ ተረጋግጧል። ከ 60 ዓመት ዕድሜ በኋላ በበሽታው የመሰቃየት ዕድሉ በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል።

### ፆታ

ጥናቶች እንደሚያመለክተቱት ወንዶች ከሴቶች በበለጠ በፓርኪንሰን በሽታ የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።

### የፓርኪንሰን በሽታ ሕክምና

ለፓርኪንሰን በሽታ ምንም ዓይነት ፈውስ የለውም፣ ግን በግልጽ በሚከተሉት ጣልቃ ገብነቶች አማካይነት በትክክል በሕክምና ባለሙያ ቁጥጥር ስር ሊያውለው ይችላል።

ፓርኪንሰን ግን የአዕምሮ ሕመም ነው። በዓለም ህመም መሆኑ ከታወቀ ከ200 ዓመት በላይ የሆነው ቢሆንም በኢትዮጵያ ግን ምን ያህል ህመምተኞች እንዳሉ እንኳ የሚያሳይ መረጃ የለም። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በሽታው የሚያጠቃው ከ65 ዓመት በላይ የሆናቸውን አረጋውያን ቢባልም አሁን አሁን ወጣቶችም በበሽታው ሲያዙ እየተስተዋለ ነው።

ፓርኪንሰን በአገራችን እምብዛም አይታወቅ እንጂ «የፓርኪንሰን ፔሸንትስ ሰፖርት ኦርጋናይዜሽን -ኢትዮጵያ» የሚባል ማህበር ተቋቁሞ የተለያየ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን በመስጠት እንዲሁም በበሽታው የተጠቁ ሰዎችን አቅም በፈቀደ መጠን ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ይበል የሚያሰኝ ሥራ እየሠራም ይገኛል።

የማህበሩ መስራችና የፓርኪንሰን ህመም ተጋላጭ የሆኑት ወይዘሮ ክብራ ከበደ ስለበሽታው ይህንን ይላሉ ፤ «ፓርኪንሰን የጤና ችግር ብቻ አይደለም። የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግርም ነው ፤ በሽታው አካል ጉዳተኛ ያደርጋል ፣ አካል ጉዳተኛ መሆን ማለት ደግሞ እንደቀድሞው መሥራት አያስችልም በዚህ ምክንያት ገቢ ይቆማል፤ ቤተሰብ ችግር ላይ ይወድቃል ፤ አካል ጉዳተኛ በመሆኑ በራሱ መንቀሳቀስ ስለማይችል ምንጊዜም ድጋፍ የሚያደርግለት ሰው የግድ ያስፈልገዋል። ሚስት (ባል)፣ እህት(ወንድም) ወይም ሌላ ዘመድ ዕለታዊ ሥራቸውን ትተው በሽተኛውን ሲንከባከቡ ገቢ ይቀንሳል፣ ቤተሰብ ለችግር ይዳረጋል ይላሉ። ማኅበራዊ የሚሆነው ደግሞ ኅብረተሰቡ ስለበሽታው ስለማያውቅ፣ ከአጋንንት፣ ከሰይጣን፣ ከድመት መግደል … ጋር ስለሚያያይዘው ተገቢውን እንክብካቤ አይሰጥም እንዲያውም ያገላል ፣ በማለት የችግሩን አሳሳቢነት አስረድተዋል። ማኅበሩ ሲመሠረት ምንም አልነበረውም፤ ዛሬም አንዳንድ ግለሰቦችና ድርጅቶች ከሚያደርጉለት ጥቂት ድጎማ በስተቀር የሚተዳደርበት በጀት የለውም። ስለዚህ ከፍተኛ የመድኃኒት አቅርቦትና የዋጋ ውድነት ችግር አለበት። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም፣ በሽታውን እንደአዕምሮ ሕመም ከመቀበል በስተቀር ህሙማኑን የሚጠቅም ይህ ነው የሚባል ነገር እየሠራ እንዳልሆነ ይናገራሉ።

በክልሎች ምን ያህል የበሽታው ተጠቂዎች እንዳሉ ጥናት ስላልተደረገ አይታወቅም። በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ የማኅበሩን መመስረት የሰሙ ሄደው የተመዘገቡ 500 በሽተኞች አሉ። ማኅበሩም ከእነዚህ ውስጥ ላሰባሰባቸው 350 ለሚሆኑት ውስን ድጋፍ ያደርጋል። ሆኖም አሁንም ቢሆን፣ ኅብረተሰቡ ፓርኪንሰን በሽታ መሆኑን ካለመገንዘብ ከኋላቀር ባዕድ አምልኮ ጋር ስለሚያያይዛቸው ወጥተው ያልተመዘገቡ በርካቶች እንደሚኖሩ ተገልጿል።

# ነፃ ሃሳብ

## ራስ ጠልነት፡- ለሰብዓዊ ፍጡር ሀፍረት የሆነ አሸባሪው ትሕነጋዊ ታህተ ሰብእ ባህሪይ (የግል የጥናት ውጤት)

ይበል ካሳ

በግሌ ስለ አሸባሪው ትሕነግ እኩይነት፣ ክፋትና ሸር፣ ሰላም ጠልነት፣ ያለጦርነት መኖር አለመቻል፣ ውሸት፣ አስመሳይነት...መስማትም መናገርና መጻፍም ሰልችቶኛል። ምክንያቱም እንኳንስ እዚሁ አብረነው የኖርነው ዓለም ላይም ቢሆን ይህን የማያውቅ አለ ብዬ አላስብምና። አሁን ማወቅ የምፈልገው ከዚህ በላይ ነው፤ ስለተሠራበት መሠረቱና ስለሆነው እሱነቱ፣ ስላደረገውና ስለኖረው ታሪኩና ድርጊቱ፣ ስለጸባዩና ግብሩ ሳይሆን ለዚህ ሁሉ መሆኑና ማንነቱ መንስኤ የሆነውን እውነተኛውን የፍጥረቱን ልክ ማወቅ ነው የምፈልገው። ይህም ዛሬ ብቻ ሳይሆን ነፍስ ካወቁበትና ስለትሕነግ ካወቅኩበት ጊዜ ጀምሮ ዕድሜ ልኬን ስፈልገው የኖርኩት እውነት ነው። እናም የትሕነግን ትሕነግ መሆኑን ሳይሆን «ለምኑን» (ማለትም ከትሕነግ ትሕነግን ሆኖ የመፈጠር ጀርባ) ያለውን ምስጢር ለማወቅ ለዘመናት ስደክም ኖሬያለሁ። አቅሜ የፈቀደውን ያህልም ጉዳዩን ለመመርመርና ለማጥናት ሞክሬያለሁ። በዛሬው ጽሑፌ በምርምሬ የደረስኩበትን ግኝትና የጥናቴን ውጤት ላካፍላችሁ ወደድኩ።

**የጥናቱ መነሻ**

ሰው ከምድር ፍጥረታት ሁሉ ልቆ የተፈጠረ ታላቅ ፍጡር ነው ብዬ አስባለሁ። ሰው ሆኖ መፈጠርም ከፍጥረታት ሁሉ በላይ የሆነ ታላቅ ክብርን የሚያቀዳጅ የታላቁ ፈጣሪ ልዩ ስጦታ መሆኑንም አምናለሁ። የሰውን አፈጣጠር በተመለከተ በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊው ጎራ የፈለቁና የሚታመንባቸው እሳቤዎች የሚያረጋግጡልንም ይህንኑ እውነታ ነው። መንፈሳዊው ወይም ሥነ ፍጥረታዊው ዕይታ እንደሚያስረዳው ፈጣሪ ይህን ዓለምና በውስጡ የሚኖረውን ፍጥረት በፈጠረበት ወቅት በታላቁ መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ሌላውን ፍጥረት ሁሉ «ይሁን» እያለ በቃሉ ብቻ የፈጠራቸው ሲሆን ሰውን ግን በቅዱስ እጁ «ኑ ሰውን እንደ አምሳላችን እና እንደ አርዓያችን እንፍጠር» በማለት ከአራት ባህርያተ ሥጋና ከሦስት ባህርያተ ነፍስ በአጠቃላይ ከሰባት ባህርያት አዋህዶ በቅዱስ እጆቹ አበጅቶታል። በግዕዝ «ሰብዕ» የሚለው ቃልም ይህንኑ የሚያመለክት ሲሆን ትርጓሜውም ሰባት ባህርያት ያሉት ማለት እንደሆነ ሊቃውንት ያስረዳሉ።

ከዚህም በአሻገር እግዚአብሔር ሌሎችን ፍጥረታት በሙሉ ሥራው ይታወቅበትና ይደነቅበት ዘንድ ለአንክሮና ለተዘክሮ የፈጠራቸው ሲሆን ሰውን ግን «ስሙን ለመቀደስ፣ ክብሩን ለመውረስ ፈጠረው» ይላል። ይህም ለሰው ልጅ ምን ያህል ክብር እንደተሰጠው የሚያሳይ ነው። በተለይም «ክብሩን ለመውረስ» የሚለው ቃል ሰው በአግባቡ ተፈጥሮውን አውቆ ከተንቀሳቀሰ ከምድራውያን ፍጥረታት በልጦ መገኘት ብቻ ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር የመሆን ዕድል እንዳለውም ያሳያል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ሰው የተፈጠረው ከእርሱ ውጪ ያሉ በምድር ላይ የሚኖሩ ሌሎች ፍጥረታትን ሁሉ ይገዛ ዘንድ ታላቅነትን ብቻ ሳይሆን አለቅነትንም ጭምር ይዞ ሁሉን በሚችለው ፈጣሪ የዚህች ምድር ታላቅ ፍጡር ሆኖ መፈጠሩንም በመንፈሳዊው የሥነ ፍጥረት እሳቤ ዘንድ ዋነኛ ማጣቀሻ ሆኖ የሚያገለግለው መጽሐፍ ቅዱስ በማያሻማ ቋንቋ በግልጽ መዝግቦት ይገኛል።

ስለሰው ልጅ አፈጣጠርና አመጣጥ የሚያትተው የሳይንሱ ክፍልም ቢሆን አጠቃላይ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሕይወት ከሌላቸው ቁስ አካላት መገኘታቸውንና የሰው ልጅም ከጦጣ መሰል ፍጡር መምጣቱን ይናገራል። ይሁን እንጂ በዝግመተ ለውጥ አማካኝነት በርካታ ችግሮችን እያሸነፈ የመጣና በሂደት ተፈጥሮን በቁጥጥሩ ስር ማድረግ የቻለ ከፈጣሪው በታች ማንኛውንም ነገር ለማድረግ የሚችል ኃያል ፍጡር መሆኑን ይመሰክራል። ሰውን የምድራችን ታላቁ ፍጡር እንዲሆን ያስቻለውና ለዚህ ክብር ያበቃው ደግሞ ክፉና በጎን፣ ስህተትና ትክክልን፣ እውነትና ሃሰትን፣ ልማትና ጥፋትን፣ ሞትና ሕይወትን የተሻለውን አመዛዝኖ እንዲመርጥበት ከፍጥረት ሁሉ ተዳልቶ ለእርሱ ብቻ ተዳልቶ በተሰጠው «አዕምሮ» በተባለ ውድ የፈጣሪ ስጦታ መሆኑንም ጠንቅቄ እረዳለሁ። እናም ምንም እንኳን የሰው ልጅ እንደ እንስሳ ስጋዊ ጠባይ ቢኖረውም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ በመሆኑ አምላካዊም፣ መለኮታዊም የመሆንን ዕድል በማግኘቱ እንደፈጣሪው መልካምና ርህሩህ ፍጡር ነውም ብዬ አምናሁ።

ይሁን እንጂ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ለማድረግ ይቅርና ለማሰብ የሚዘግንኑ፣ ሰው ሆኖ መፈጠርን የሚያስጠሉ እጅግ የሚከብዱ የከፋትና የጭካኔ ድርጊቶችን በሰው ልጆች ላይ ሲፈጽም የኖረው ትሕነግ የሚባለው የሰው ጉድ ስለሰው ልጅ አፈጣጠርና ማንነት ካለኝ አስተሳሰብና እምነት በተቃራኒው ቆሞ መመልከቴ ዕድሜዬን ሙሉ «ለምን?» የሚል ጥያቄን በአዕምሮዬ ውስጥ ሲያመላልስብኝ ኖሯል። ሁኔታውን በአጽንኦት እንድመረምረውና በጉዳዩ ላይ የራሴን ጥናት እንዳደርግ ያስገደደኝም ከሰው ልጅ ተፈጥሮ በተቃራኒ የቆመው ይኸው የአሸባሪው ትሕነግ ድርጊትና ማንነት ነው።

**የጥናቱ አሁናዊ ዳራ**

በሊቢያ የሜዲትራኒያን ባህር ዳርቻ አይ.ኤስ. አይ.ኤስ በተባለ ወንጀለኛ የሽብር ቡድን በኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን ላይ ከተፈጸመው እጅግ ዘግናኝ አረመኔያዊ ድርጊት የባሰ ጭካኔ በሚለው ቃል ብቻ ሊገለጽ የማይችል ዓለማችን አይታው የማታውቀው ሌላ ዓይነት ጭካኔ እዚሁ በራሳችን ታህተ ሰብዕ ጨካኞች በትሕነግና በትሕነጋውያን አማካኝነት በተደጋጋሚ ተፈጽሟል። አሸባሪው ትሕነግ በማይካድራ የዕለት ጉርሳቸውን፣ የዓመት ልብሳቸውን ለማሟላት ቀያቸውን ጥለው ለጉልበት ሥራ የሄዱ፣ ቀን በሃሩር ሌሊት በቁር ያለእረፍት ላባቸውን እያፈሰሱ የነበሩ፣ እጅጉን በሥራ የደከሙ ምስኪን የቀን ሠራተኞችን ፍጹም አሰቃቂ በሆነ መንገድ በአካፋና በዶማ ቀጥቅጦ ገድሏቸዋል። ሞቼልሃለሁ፣ ተሰውቼልሃለሁ እያለ በሃሰት በስሙ የሚነግድበትን በተግባር ግን ዕድሜ ልኩን ሲገድለውና ለጥቅሙ ሲሰዋው ለኖረው ትሕነግ «ሕዝቤ» ለሚለው የትግራይ ሕዝብ ሕይወታቸውን ሰጥተው ሃያ ዓመታትን ከጠላት ሲጠብቁት የኖሩትን፣ ከማትበቃ ደመወዛቸው እየቀነሱ ትምህርት ቤትና ጤና ጣቢያ የገነቡለትን፣ ሃያ ዓመት አብረውት የበሉትን የጠጡትን ጋሻ መከታ ወንድሞቹን በተኙበት አርዷል።

በአፋር በጋሊኮማ መንቀሳቀስ የማይችሉ በሰው የሚወጡ የሚገቡ አረጋውያን እናቶችንና አባቶችን እና ሕፃናትን በከባድ መሣሪያ በጅምላ ጨፍጭፏል። በሰሜን ወሎ አጋምሳ የተባለች ወረዳን ነዋሪዎቿን በጅምላ ጨፍጭፎ፣ ምድሯን ሳይቀር አቃጥሎ ሙሉ በሙሉ አውድሟል። ሽንፈቱንና ውርደቱን ለመደበቅ በሚል በጦርነት የሞቱበትን የራሱን አመራሮች ሳይቀር ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ አንገታቸውን ቆርጦ ደብቋል። ትሕነጋውያን ጦርነት ምን እንደሆነ ምኑንም የማያውቁ፣ አውቀውም የማይሸሹ፣ ሸሽተውም የማይደበቁ፣ የማይናገሩ፣ የማያስቡ፣ የማይማከሩ «ነፍሰ እግዚአብሔር» የሚባሉ የቤት እንስሳትንም ገድለዋል፣ አቃጥለዋል። ስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ደግሞ እጅግ አሰቃቂ በሆነ፣ እስካሁን ታይቶ በማይታወቅ መንገድ የሰውን ልጅ አሰቃይተዋል፣ ገርፈዋል፣ ሰውን ከእባብና ከጊንጥ፣ ከአንበሳና ከጅብ ጋር አንድ ላይ አስረዋል፣ የሰውን ልጅ ከእነ ነፍሱ ቀብረዋል፣ የወንድ ልጅን ብልት አኮላሽተዋል፣ በሴት ልጅ ብልት እንጨት...።

በአጠቃላይ ትሕነግ ቅድስት አገር በምትባለው በኢትዮጵያ ላይ ይቅርና ምንም ዓይነት ሃይማኖት የሚባል ነገር በሌለበት በየትኛውም የዓለም ክፍል ላይ እንኳን ሊፈጸሙ የማይችሉ፤ ታይተው ተሰምተው የማይታወቁ እንኳንስ ለሰው ልጅ ለፍጡር ሁሉ እንግዳ የሆኑ፣ ብዙ፣ ብዙ ተዘርዝረው የማያልቁ አሳፋሪ ርኩሰቶችንና አሰቃቂ ጉዶችን በሰው ልጆች ላይ ፈጽሟል።

**የጥናቱ ዘዴ**

በዚህ ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው ዘዴ እስካሁን ድረስ የተነበቡ የትሕነግ ማንነት ታሪኮችን በቅርብ ጊዜ ከቀሰቀሰው ወረራና ጦርነት ጋር በማገናዘብ ጥልቅ የማሰብና የማብሰልሰል ዘዴን በመጠቀም የትሕነግን ሁለንተናዊ ማንነት መመርመር ነው።

**ትንተና**

የራስን ችግር ለመፍታትና የተሻለ ሰው ሆኖ ለመገኘት ማሰብና መፍጨርጨር ለሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ተፈጥሯዊ ባህሪይው ነው። መነሻና መድረሻውም ሕይወትን ማፍቀርና ማሳመር ነው። እናም ይኸው ንጹህ የማደግና የመሻሻል ፍላጎት የወለደው ንጹህ የፍቅር የኃይል ሚዛናዊ በመሆኑ ሂደቱ አንድና ቀጥተኛ ግቡም አንድነትና ስምምነት ነው። መሠረቱ ለሕይወት ያለ ንጹህ ፍቅር ነውና፤ ሕይወት ደግሞ የእያንዳንዱም የሁሉም፣ አንድም ብዙም፣ ግለሰብም ኅብረተሰብም፣ ራስም ሌላም፣(የራስም የሌላውም፣ የሁሉም)፤ ናትና። ሰው ራሱ አንድነትም ብዙነትም ነውና፣ ሰው የሚለው ቃል ራሱ የአንድም የሁሉም ስያሜ ነውና፣ አንዱም ሰው፣ አጠቃላይ የሰው ዝርያ(ስፒሽየስ)ም የሚጠራው «ሰው» ተብሎ ነውና።

ለምሳሌ «አንተ ሰው»፣ «ያ ሰው» በሚሉት አገላለጾች ውስጥ ያለው ሰው አንድ ወይም ነጠላ ሲሆን «የሰው ልጅ»፣ «በምድር ላይ የሚኖር ሁሉም ሰው ሊያውቀው የሚገባ ጥብቅ ጉዳይ»፣ «ሰው ለተባለ ፍጡር ሁሉ፣ ሰው ሁሉ፣ አገር ያለ ሰው» ...ወዘተ በሚሉት ሐረጎች ውስጥ የሚገኘው «ሰው» የሚል ቃል ደግሞ ብዛትን የሚያመላክት ነው። ስለሆነም ሰው መሠረቱን ፍቅር ላይ አድርጎ የእርሱ ከሆነው ከራሱ ሰውነት ላይ ተነስቶ ሕይወቱን ለማሻሻል ሲሠራ ሰውነትም ሕይወትም የጋራ ስለሆኑ ሰው ለተባለ ፍጡር እየሠራ ነው ማለት ነው። ፍቅርም የጋራ የሰው ሁሉ ናትና ለሁሉም ይሠራል ማለት ነው።

በሌላ አባባል ሰው ራሱን ትቶ ከሌላው ጋር አነጻጽሮ ሲነሳ ግን ምንም እንኳን ራሱን ያነጻጸረው ከሰው ጋር ቢሆንም እንኳን ራሱን ትቶ ከሌላው በመነሳቱ ራሱን ከዷል ማለት ነው። ራሱን ከካደ ደግሞ የሌላውንም ሰው ማንነትም ይክዳል ማለት ነው። ሁለተኛ ነገር ወደሌላው ሰው የተመለከተው ያንን ሰው ለመጥቀም ሳይሆን ከዚያ ሰው አኳያ እርሱ ያለውንና የሆነውን ለመመዘንና በምን ይበልጠኛል፣ እኔስ በምን እበልጠዋለሁ፣ እኔ ከእርሱ በምን አንሳለሁ፣ እርሱስ ከእኔ በምን ያንሳል የሚሉትን በእርሱና በሌሎች መካከል አሉታዊ ክፍፍል የሚፈጥሩ፣ አላስፈላጊ የመበላለጥና የበላይነትና የበታችነት ስሜትን የሚፈጥሩ አፍራሽ ስሜቶችና የጉድለት ስሜትን የሚፈጥሩ ስሜቶችን የሚያመጡና ያን የተዛባ የኃይል ሚዛን ለመመለስ ለማስጠበቅ ወደፉክክርና ሽኩቻ የሚወስዱ የጥፋት መንገድን በማሰብ በመሆኑ ነው።

ስለዚህም ሌላውን መሠረት አድርጎ የሚነሳ ሰው በመጨረሻም በዚህ የተሳሳተ አካሄዱ ሰውን መጉዳቱ አይቀሬ ነው። እናም እንዲህ ዓይነቱ ሰው ራስ ወዳድ ሳይሆን ራስ ጠል ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ራስን ለመመልከትና ከራስ ለመነሳት ራስን መውደድ ያስፈልጋል። ራሱን ተመልክቶ ከራሱ ተነስቶ ቢሆን ኖሮማ ራሱንም ስለሚወድ ሌላውንም ይወዳል። ስለሆነም ሌላውን ሰው የሚጎዱ ሰዎች በተለምዶ እንደሚባለው ራስ ወዳድ ሰዎች ሳይሆኑ ራሳቸውን ክደውና ጠልተው ራሳቸውን ከሌላው አንጻር ለመመልከትና ለመቅረጽና በዚያ መንገድ ለመኖር የሚሠሩ ራስ ጠል ሰዎች ናቸው ማለት ነው። ወይንም እነዚህ ሰዎች ማለትም ከራሳቸው ሳይሆን ራሳቸውን ከሌላው ጋር አነጻጽረው ኑሮን ለመምራት የሚነሱ ሰዎች ራስ ጠል ናቸው ወይንም ራስ ወዳድ ሳይሆኑ ራስን ብቻ ወዳድ በሚል ሊገለጹ ይችላሉ።

ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቶቹ ራስ ጠል ሰዎች ሕይወታቸውን ለመምራት ወደሰው የሚሄዱት ራሳቸውን ስለሚጠሉ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን ብቻ ስለሚወዱም ሊሆን ይችላል። ማለትም ከራሳቸው አብልጠው ወደሰው የሄዱት ራሳቸውን ብቻ ስለሚወዱ በዚያም ሁሌም እነርሱ ብቻ ከሌላው የበላይ ሆነው ለመኖር ከሌላው ሕይወት ላይ ተነስተው ማለትም ሌላው ሰው ባለውና በሌለው፣ በሆነውና ባልሆነው ነገር ላይ ተመሥርተው ሌላው የሌለውን ለእነርሱ ለመፍጠር ሌላው ያልሆነውን እነርሱ ለመሆን የሚያስችላቸውን ራስን ብቻ የማስበለጥ ወይንም የመውደድ ብልጣብልጥ ስሌት ሊሆን ይችላል።

ሆኖም ፍቅር በባህሪው ለብቻ የማይዙት፣ ለራስም ለሌላውም የሚሰጡት፣ ከራስ አፍልቀው ለሌላው የሚሰጡት የሚካፈሉት እንጂ እንደበሽታ ለብቻ የሚሸከሙት ባለመሆኑ «ራስን ብቻ መውደድ» የሚባለው አገላለጽ በራሱ የተሳሳተ አገላለጽ ወይንም ስያሜ ነው። ስለሆነም እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳን ራሳቸውን ብቻ በመውደዳቸው ራስ ብቻ ወዳዶች ተብለው ሊገለጹ የሚችሉ ቢሆንም አንድም ከስያሜ ተገቢነት አኳያ የማያስኬድ በመሆኑ፣ የስያሜው ኢተገቢነት የመነጨው ደግሞ ከጽንሰ ሃሳቡ ስሁትነት በመሆኑ ማለትም ራስን ብቻ እየወደዱ ራስ ወዳድ ወይም ፍቅር የሚያስገኘውን ሰላም እያገኙ መኖር የማይቻል በመሆኑ ራስን ብቻ መውደድ በራሱ ከፍቅር ይልቅ የጥላቻ መገለጫ በመሆኑ ራስ ጠል የሚለው ይበልጥ ይስማማቸዋል።

ራሱን ብቻ የሚወድ ለራስ ብቻ የሚሰጥ ፍቅር ባለመኖሩ ፍቅርም በባህሪው ለራስ ብቻ የማያገለግል በመሆኑ እንዲሁም ራስን ብቻ ወዳድነት አስማሚና አንድነት ፈጣሪ ሳይሆን አግላይና ከፋፋይ በመሆኑ ራስን ብቻ ወዳድነት ራስንም ሌላውንም የሚጎዳ ራስ ጠልነት ነውና! ራሱን ብቻ የሚወድ ሌላውን ይጠላልና፤ ሌላውን የሚጠላ ደግሞ ራሱንም አይወድምና፤ እንዲያውም ራሱን የሚጠላ ነውና! የትሕነግ እውነተኛ ስሪትና ባህሪም እንዲሁ ነው። ለምን?

ምክንያቱም አሸባሪው ትሕነግ ገና ሲወለድ የራሱን ማለትም ኢትዮጵያዊ ማንነቱን ክዶ ነው የተወለደው። ማንነቱን ክዶ የተወለደው «የትግራይ ሕዝብ» ነፃ አውጪ ግንባር (ትሕነግ) በአጥንትና በደም ተሳስረውና ተዋህደው ፍጹማዊ በሆነ ፍቅርና መቻቻል የማያልቅ ሕብረትና አንድነት ፈጥረው ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ ዥንጉርጉር መልካቸውን ይዘው፣ ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን ጠብቀው፣ የተከበረና አኩሪ ታሪክ ያላት ታላቅ አገር መስርተው የኖሩ ኢትዮጵያውያንን አባቶቹንና እናቶቹን ማንነት ክዶ ነው የተወለደው። ራስን መካድ ደግሞ ራስን መጥላት ነው። ከዚህ በተጨማሪም በኢምፔሪያሊዝም የዘር ሾተላይ የእርግዝና ዘመኑን ሳይጨርስ የሰውነት ደረጃ ላይ ሳይደርስ ከኢትዮጵያ ምድር የተወለደው ጭንጋፉ ትሕነግ ከምን ጊዜውም በላይ የሰው ልጆች ወደ አንድነትና ትብብር እየመጡ ባሉበት በሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ሰዎችን፣ ያውም የአንድ አገር ዜጎችን የሚለያይ የአጥንትና የመንጋ ፖለቲካ ይዞ ነው የተወለደው።

የራሱንና የአገሩን የኢትዮጵያን ተፈጥሯዊ ማንነት አውልቆ ጥሎ ለኢትዮጵያውያንና ለራሱ ሌላ አዲስ የሃሰት ማንነት ለመፍጠር ነበር ትሕነግ በጫካ የተወለደው። በመጨረሻም «ኢትዮጵያ የአማራ ገዥዎች ሌላውን ብሔርና ብሔረሰብ በኃይል አስገድደው የፈጠሯት አገር ናት፤ ትግራይም የኢትዮጵያ አካል ሳትሆን ራሷን የቻለች አገር ናት፣ እናም ትግራይም ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችም ማንነታቸውን ለማስከበርና ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር በጨቋኙ የአማራ ብሔር ላይ በጋራ መነሳትና መታገል አለባቸው» የሚል የጥላቻና የሃሰት ትርክት አዘጋጅቶ የጥፋት መርዙን ቋጥሮ ነበር ከጫካ የወጣው። እናም ትሕነግ ራስ ጠል ነው።

በዚህ መንገድ ለብሔር ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት የተቆረቆረ መስሎ ግን ደግሞ ማንነታቸውንና የአገር ባለቤትነት መብታቸውን ነጥቆ ኢትዮጵያን ለአንድ ብሔር ብቻ ጠቅልሎ የሚሰጥ በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ዥንጉርጉርነት ተፈጥሯዊ ማንነትን ክዶ የሚያስክድ እጅግ አደገኛ የክህደት፣ የውሸትና የጥፋት አጀንዳን ያለእረፍት እየፈጸመና እያስፈጸመ ግማሽ ክፍለ ዘመናትን በሕይወት ቆይቷል። ራስ ጠል በመሆኑ በክህደት ተወልዶ በውሸት ያደገው አሸባሪው ትሕነግ ዛሬም በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ከስህተቱ የማይማር፣ ከጥፋቱ የማይመለስ፣ በእርኩሰቱ የሚደሰት፣ እየተገረፈ የሚስቅ፣ ለቅሶ ተቀምጦ ከበሮ የሚደልቅ፣ መቃብር ውስጥም ሆኖ የሚፎክር ሳጥናኤልን የሚያስንቅ ከንቱ የእብሪተኛ ቡድን በመሆኑ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለሰው ዘር በሙሉ ኃፍረትም ነው። እናም እንዲህ ዓይነት ራስ ጠል ታህተ ሰብእች ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለሰው ዘር ሁሉ ጸሮች ናቸውና ከምድረ ሰው እንዲወገዱ ዓለም ሁሉ ሊተባበር ይገባል የሚለው የአጥኚው ምክረ ሃሳብ ነው።

# ተናጋሪው ዶሴ

# ‹‹ ቡና ቶሎ አልሰጠሽኝም! ››

## ያመጣው ጣጣ እስከ ህይወት ፍፃሜ

**አስመረት ብስራት**

የሰው ልጅ ለመኖር በርካታ ጥረቶችን ያደርጋል። ለመኖር ብሎም ጥሪት ለማፍራት ጥሮ ግሮ ገንዘብ የሚያገኝበትን መንገድ ይፈልጋል። አንዳንዱ ተምሮ ስራ ሲይዝ የመማር እድል ያላገኘው ደግሞ በትንንሽ ስራዎች ላይ ይሰማራል፤ በንግድና በግብርናው አለሁ ብሎ ወደ ስራ ይገባል። በዛም አነሰ ሁሉም ኑሮውን ለማሸነፍ ይታትራል። ተምሮ ስራ ያገኘውም ሆነ በተለያየ ስራ የተሰማራው ለነገ ለውጥ ለማየት ተስፋ አድርጎ ይሮጣል።

በአብዛኛው ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ የተወለዱ ወጣቶችም የተሻለ የስራ እድል ለማግኘት ሲሉ የትውልድ ቀያቸውን ለቀው ወደ የሀገሪቱ መዲና አዲስ አበባ በመምጣት ስራ መፈለጋቸው የተለመደ ነው። በተለይም ከደቡቡ የሀገሪቱ አካባቢ የሚመጡ ልጆች ከህፃንነታቸው ጀምሮ በተለያዩ የስራ ዘርፎች ተሰማርተው ይታያሉ። በመንገድ ዳር አነስተኛ ሚዛን አስቀምጠው "ተመዘን"‹‹ተመዘኚ›› የሚል ጣፋጭ ቃል ከሚያወጡት ህፃናት አንስቶ በጉልበት ስራ ላይ የተሰማሩት ወጣቶችም በብዛት ከዛው አካባቢ ነው የመጡት። ከይርጋለም አካባቢ ወደ አዲስ አበባ ለስራ በሚል ምክንያት ከሚመጡት ወጣቶች መካከልም ወጣት ወሰን ለማ አንዷ ናት።

**ታታሪዋ ወጣት**

ወጣት ወሰን አዲስ አበባ በመጣችበት ጊዜ የመጀመሪያ ስራዋ በሰው ቤት ሰራተኝነት ተቀጥራ መስራት ነበር። ለተወሰኑ አመታት በዚሁ ስራ ላይ ተሰማርታ ስትሰራ ከቆየች በኋላ ትንሽ ሳንቲም ሲጠራቀምላት የእራሴን ስራ መጀመር አለብኝ ብላ ትወስናለች። እቅዷን በፍጥነት ወደ ተግባር የቀየረችው ወጣት በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ሸለሞ ግቢ እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ የጀበና ቡና ለመሸጥ ቦታውን ተከራይታ የሚያስፈልጋትን ግብአት አሟልታ ስራዋን ትጀምራለች። ቀን ቀንን እየወለደ በቡና ጠጡ የተጀመረው ስራ ቁርስም፤ የተቀቀለ ድንችም ሌሎችንም ፈጣን ምግቦች እያስከተለ ስራዋ እየሰፋላት ሄደ። ተወዳጅም ሆነና ደንበሾች እሷን ብለው መምጣት አበዙ።

ከእለት ጉርስና ከቤት ኪራይ የተረፋትን እቁብ እየጣለች አነስተኛ ሽሮ ቤት ለመክፈት ያቀደችው ይች ወጣት በጠዋት ተነስታ ሻይ፤ ቡናና ቁርስ ለማዘጋጀት ትጣደፋለች። ደንበኞቿ የሚረኩበት ጣእም ለማምጣት ተፍ ተፍ ስትል ነው የምታረፍደው። የቁርስ መስተንግዶ እንዳበቃ ምሳቸውን በልተው ቡና ለመጠጣት የሚመጡ ደንበኞቿ ቡና አጥተው እንዳይመለሱ እሱን በማዘጋጀት ስራ ላይ ትጠመዳለች። የምሳ ሰአቱ ግርግርና መስተንግዶ ከበቃ በኋላ ደግሞ ማምሻቸውን ትኩስ ድንች በሚጥሚጣ ለሚመገቡ ደንበኞቿ ድንች ጥዳ መምጣታቸውን በጉጉት ትጠባበቃለች።

በስራዋ ቀልድ የማታውቀው ወጣት ከፊቷ የማይጠፋ ፈገግታዋን ይዛ ሙሉ ቀን ስትደክም ትውላለች። በዚህ መካከል ነው እንግዲህ ህይወቷን ያስከፈላት አጋጣሚ የተፈጠረው።

**የድካሟ ማረፊያ ክፉ ገጠመኝ**

ሰኔ 3 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 7፡00 ሰዓት አካባቢ ነበር። የምሳ ሰአት የቡና ደንበኞቿን ሸኝታ አረፍ ወደ ማለቱ ነበረች። ቀኑን ሙሉ ሲለፉ የዋለ ጎኗ ረሃብ ስለተሰማው የሚበላ ነገር ለመቅመስ ዞሪያ ገባዋን ብታይ ከተጣደው ድንች በስተቀር ምንም መመልከት አልቻለችም ነበር። የዛሬ ገበያ ጥሩ ነበር፤ አንድም የሰራችው ምግብ አልተረፈም።



ተጥዶ በመንተክተክ ላይ ካለው ድስት ውስጥ አንድ ትኩስ ድንች ከድስቱ አውጥታ እንዲቀዘቅዝ ሰሀን ላይ አድርጋው ቀና ስትል አንድ ሰው ወደ ምትሰራበት በመሄድ "ቡና ስጭኝ" በማለት ተቀመጠ። እጅግ በጣም የተጣደፈ ይመስላል። "እሽ ቆይ ላሙቅልህ" በማለት ቡናውን በተያያዘ ከሰል የተሞላው ማንደጃ ላይ ጥዳ የራበውን ሆዷን ለማስታገስ ድንች ወደመላጡ ተመለሰች። ድንች እየላጠች ሳለ "ለምን ቡናውን ቶሎ አትሰጭኝም" ብሎ ስድብ ጀመረ። " አንዴ ይሙቅ አልኩህ" አለችው ትእግስት ማጣቱ እያበሳጫት። በመጮህና በመሳደብ ከተቀመጠበት ተነስቶ ድንች እየላጠችበት የነበረውን ቢላዋ እጇን ጠምዝዞ በመያዝ እና ጣቷን በመንከስ አስለቀቃት።

ቢላውን ከእጇ ላይ ካስለቀቃት በኋላ ቢላውን ጨብጦ በመያዝ ደረቷ ላይ ለመውጋት ይሞክራል፤ ወሰንም የስውየው ንዴት አስደንግጧት ዞራ ለማምለጥ ስትሮጥ ተከትሏት ከጀርባዋ ሲሰነዝር ላለመወጋት የአቅሟን ያህል ትታገላለች። ምን ብትውተረተር ረሀብና ስራ ያደከመው ሰውነቷን ግን በቀትር ከመጠባት ውርጅብኝ ማዳን አልቻለችም። ብዙ ታግላ የወደቀችውን የሃያ ስድስት አመት ወጣት ወሰን በወደቀችበት በተደጋጋሚ በሰነዘረው ቢላ የእግር ታፋዋ ላይ ወግቶ ለማምለጥ ሲሞክር በአካባቢው በነበሩ ሰዎች ተይዟል። ወሰንም በግርግር መካከል ወደ ህክምና መስጫ ቦታ በፍጥነት መድረስ አልቻለችም ነበር። ፖሊስ በአካባቢው ደርሶ ወጣቷ ወደ ህክምና ቦታ ስትደርስ በደረሰባት ጉዳት ምክንያት ብዙ ደም ስለፈሰሳት ህይወቷን ማትረፍ ሳይቻል ቀረ።

አሰራለሁ እለወጣለሁ ብላ ከቤቷ የወጣችው ወጣት የስራ ቦታዋ መጥፊያዋ ሆነ። የእራሷንም ሆነ የቤተሰቧን ህይወት ለማሻሻል ስትታገል የነበረችው የጀበና ቡና የምትሰራው ወጣት ከህልሟ ሳትደርስ በአጭር ተቀጨች። ዛሬን እንደምንም ኖራ ነገን የተሻለ ለማድረግ ያቀደችው ዕቅድ በማይረባ ምክንያት በተራ ግለፍተኛ የተነሳ ለማንም ሳትተርፍ ቀረች። ምኞቷና ተስፋዋ ሁሉ እንደ ህምሌ ደመና በኖ ቀረ።

**ቡና ያሰከረው ነፍሰ ገዳይ**

በመካከለኛ እድሜ ያለ ሰው ነው አቶ ገንዘብ ታምሩ። በኮንስትራክሽን የስራ ዘርፍ ተሰማርቶ ግንበኝነቱንም፤ ቀለም ቀቢነቱንም ሁሉንም ስራ የሚሞካክር ሁለገብ ባለሙያ ነው። ለወትሮው ማለዳ ተነስቶ ቡናውን ጠጥቶ ነበር ወደ ስራው የሚሄደው። ሰሞኑን ግን ስራ ጠፍቶ ቤት ከዋለ ሰነባብቷል። ጠዋት መነሳቱ ቀርቶ አልጋ ላይ ማርፈድን ልማድ እያደረገው ነው። ያች የቡና ሱሱ ብቻ ስትቀሰቅሰው ከመኝታው ተነስቶና ቡና ጠጣጥቶ ስራም ጠያይቆ ተመልሶ አልጋ ውስጥ ይገባል።

እጁ ላይ ያለው ገንዘብ እያለቀ ስራም ከጠፋ መሰነባበቱ እያበሳጨው ባለበት ወቅት ነበር ቡና በአይኑ ላይ ውል ያለው። ከአልጋው ብድግ ብሎ ወደ ቡና ደንበኛው ጋር ሄደ። የሃሳቡ መብዛት ይሁን ሱሱ ጥድፍድፍ ቸኩልኩል ብሏል። ሰሞኑን ያለ አመሉም መበሰጫጨትን እያበዛም ነበር። ልክ ቡናው ስኒ ጋር እንደደረሰ ወዲያው እጁ ላይ ሲኒ እንዲቀመጥለት የተመኘው ሰው ቡና የምታፈላውን ሴት በትእግስት ማጣት ያጣድፋት ጀመር። ቡናውን አሙቃ እስክትሰጠው ትእግስት ያጣው ገንዘብ ምሳዋን ልትበላው ድንች እየላጠችበት የነበረችበትን ቢላዋ ተቀብሎ ነፍስ ሊያጠፋ በቃ።

ሰው አጠፋለሁ ብሎ ባላሰበበት በአጋጣሚ የደቂቃዎች ትእግስት ማጣት የተነሳ የአንዲት ምስኪን ነፍስ በእጁ አለፈ ። አስቦትም ይሁን ሳያስብ የአንዲት ተስፈኛ ወጣት ህይወት በእጁ በማለፉ የተነሳ ህግ ፊት መቅረብ ግድ ነው።

**የፖሊስ ምርመራ**

ተከሳሽ አቶ ገንዘብ ታምሩ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ሸለሞ ግቢ እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ የጀበና ቡና በመሸጥ ነበር የምትተዳደርን የ26 ዓመት ወጣት ወሰን ለማ ‹‹ቡና ቶሎ አልሰጠሽኝም›› በሚል ምክንያት ታፋዋ ላይ በመውጋት ጉዳት ማድረሱንና በዚህም ጉዳት መነሻነት ህይወቷ ሊያልፍ መቻሉን በሰነድ ማስረጃና ከአይን ምስክሮች ያገኘው ማስረጃ አጥናክሮ ለአቃቤ ህግ በመላክ ክስ እንዲመሰረት አድርጓል።

የዐቃቤ ሕግ ክስ እንደሚያስረዳው ከሆነ ገንዘብ ታምሩ የተባለው ተከሳሽ ሰኔ 3 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 7፡00 ሰዓት ሲሆን ሟች ወደ ምትሰራበት በመሄድ "ቡና ስጭኝ" በማለት ሲቀመጥ "እሽ ቆይ ላሙቅልህ በማለት" ቡናውን ማንደጃ ላይ ጥዳ ድንች እየላጠች ሳለ "ለምን ቡናውን ቶሎ አትሰጭኝም" ብሎ ስድብ በመሳደብ ተነሰቶ ድንች እየላጠችበት የነበረውን ቢላ እጇን ጠምዝዞ በመያዝ እና ጣቷን በመንከስ ካስለቀቃት በኋላ በቢላዋ ደረቷ ላይ ለመውጋት ይሞክራል፤ ሟች ዞራ ለማምለጥ ስትሮጥ ተከትሏት ከጀርባዋ ሲሰነዝር ሟችም ላለመወጋት ትታገላለች ፤ በዚህን ጊዜ በተደጋጋሚ በተሰነዘረው ቢላዋ የሟችን የእግር ታፋዋ ላይ ወግቶ ለማምለጥ ሲሞክር በአካባቢው በነበሩ ሰዎች ተይዟል። ሟችም ህክምና መስጫ ቦታ ስትደርስ በደረሰባት ጉዳት ምክንያት ብዙ ደም ስለፈሰሳት ህይወቷ ሊያልፍ ችሏል። ዐቃቤ ህግ ከፖሊስ ጋር በመሆን ተገቢውን የወንጀል ምርመራ ካከናወነ በኋላ ተከሳሽ ላይ የሰው መግደል ወንጀል ክስ መስርቶበታል።

## ውሳኔ

ተከሳሹም ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ "ድርጊቱን ፈፅሜአለሁ ነገር ግን እራሴን ለመከላከል ነው" በማለት የተከራከረ ሲሆን ዐቃቤ ህግ ደግሞ ያሰባሰባቸውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን በማቅረብ ተከራክሯል። ፍርድ ቤቱ መረጃዎችን ሲመረምር ቆይቶ በተከሳሹ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ለማሳለፍ በቀነ ቀጠሮ ተገኝቷል። ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል ተከሳሹ በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጦ የክስ መከላከያውን እንዲያቀርብ ዕድል ሰጥቷል ። ድርጊቱን መፈፀሙን አምኖ እራሴን ለመከላከል ስል ነው ከማለት ያለፈ ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን አላስተባበለም።

ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ግድያ እና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎትም ተከሳሹ በተከሰሰበት አንቀፅ ጥፋተኛ ነው በማለት በዋለው ችሎት ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት አንደኛ ተከሳሽ አቶ ገንዘብ ታምሩ እጁ ከተያዘበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር በአስራ ሶስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል። ይግባኝ መብት ሆኖ መዝገቡም ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ የሚል ውሳኔ በመስጠት የተሰየመው ችሎት ተበትኗል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## እኛው ያጠገብናቸው የመዲናችን አይነኬ ‹‹ባለሥልጣናት››

ደበል ካሳ

ገና ወደ ግዛታቸው ስትገባ «ሕግ ያለው ፍርድ ቤት ብቻ ነው» የሚል በትልቁ የተጻፈ የራሳቸው ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፊት ለፊት ተጽፎ ታነባለህ። እናም የፈለገ ነገር ቢያደርጉህ እነኝህን ባለሥልጣናት መናገር አትችልም። መብቴ ተጣሰ ብለህ መብትህን ለማስከበር መከራከር ትርፉ ጆሮ የሚሰቀጥጥ ስድብ መስማት ነው። ያውም አንተን ብቻ ከሆነ የሚሰድቡህ። ዘጠኝ ወር አርግዛ፤ ጡቶቿን አጥብታ፣ በጉያዋ አቅፋ፣ በጀርባዋ አዝላ ከእርሷ በቀር ማንም ሊያደርገው የማይችለውን ተፈጥሯዊ ጣፋጭ ፍቅሯንም መግባ ያሳደገችህን በምንም በማንም የማትለውጣትን ውዷን እናትህንም ይጠሯታል፤ ጠርተው ይሰድቧታል።

ታዲያ «አሁንስ ይበቃል በእናቴ እንኳን አልችልም ብለህ» አጸፋ ብትመልስላቸው ባለሥልጣናቱ ጭፍሮቻቸውን ጠርተው ሊደበድቡህና ሊያስደበድቡህ ይችላሉ። ስለዚህ ግፋቸውን ቢያበዙብህ፣ ያሻቸውን ቢያደርጉብህ ምንም ማድረግ አትችልም። ያው እንደለመደብህ ቻል አድርገህ ዝም ከማለት በስተቀር። ምክንያቱም ባለሥልጣናቱ አይነኬ ናቸዋ! «በሕግ አምላክ» ብትል የሚሰማህ ያለ እንዳይመስልህ። የሕግ ነገርማ እነሱ ጋር በሕግ የተከለከለ እኮ ነው። መብትን መጠየቅስ? መብትን መጠየቅም ያው ነው፤ መጠየቅ አይቻልም ምክንያቱም ያሰድባል ባስ ሲልም በተለይ ደግሞ ምሽት ላይ ከሆነ ያስደበድባል። እነዚህ ፈላጭ ቆራጭ ፈርዖናውያን አይነኬ ባለሥልጣናት ደግሞ እነማን ናቸው ብላችሁ አትጠይቁኝም። በየቀኑ «የምንገለገልባቸው» የከተማችን ታክሲዎች አሽከርካሪዎችና አጋፋሪዎቻቸው ረዳቶች ናቸው።

እነዚህ ባለሥልጣናት የብር ከሃምሳ ሳንቲሙን መንገድ አምስት ብር ቢያስከፍሉህ፣ ሦስት እጥፍ አስከፍለውህም በወንበር ሦስት ወይም አራት እያደረጉ እንደጀሪካን አሰቃቅለው ቢጭኑህም፣ «በአቋራጭ» በሚለው አስገዳጅ የኮማንድ ፖስት ሕጋቸው መውረጃ ቦታህን አሳልፈው ተመልሰህ ወደነበርክበት ታክሲ እንድትይዝ ቢያስገድዱህም ምንም ማድረግ አትችልም። ምንም ማድረግ አይቻልም አለ ዲጄው። ምንም ልታደርጋቸው አትችልም። አይነኬ ናቸዋ። ግን እኮ አይደለምና ከታሪፍ በላይ ያለ አግባብ በምትከፍለው ክፍያ በሕግና በአግባቡ የመስተናገድ መብት አለህ። «በሕግና በአግባቡ» አልኩ እንዴ? ለካ ሕግ ያለው ፍርድ ቤት ነው ይቅርታ። ፊርማታህን ተገደህ ያለማለፍ፣ በአንድ ወንበር ሦስትና ከዚያ በላይ ሆኖ ያለመሳፈር፣ ለሦስት እንኳን የምትቀመጥበት ወንበር አጥተህ አግዳሚ ላይ ተደርድረህ ያለመሄድ መብት እኮ አለህ።

ወይ የኔ ጅልነት በሕጉ ተስፋ ብቆርጥ ደግሞ ስለ መብት ማውራት ጀመርኩ። ታክሲ ውስጥ መብት? እንደዚያ ብሶት እንዳጃጃለው የኔ ብጤ በጠራራ ፀሐይ ላምባዲና አብርተህ ብትፈልገውም ታክሲ ውስጥ መብተህን አታገኘውም። እናም እንደፈለጉ ቢጫወቱብህ መብትህን መጠየቅ አትችልም። አይነኬዎቹ የታክሲ ሹፌሮችና ረዳቶቻቸው እኮ ናቸው። ምንም ማድረግ አትችልም እንደለመደብህ ዝም ብለህ አቤት ወዴት ብለህ ታክሲህ ውስጥ ተሳፍረህ ከመነዳት በስተቀር! ውይ! ውይ! እንዲያውስ ከታክሲው ስወርድ ረስቼው ነው እንጂ ዝም ብዬ ይህን ሁሉ ስማቸውን የማጠፋው እነሱማ አይነኬዎቹ ቄሳራውን መች የዋዛ ናቸው። ስለ መብት የሚጠቅስ አንቀጽስ በሕገ መንግሥታቸው አስቀምጠው የለ። አዎ...አስታወስኩ...መብትን በተመለከተ በታክሲ ሹፌሮችና ረዳቶች ሕገ መንግሥት የተቀመጠው አንቀጽ እንዲህ ይላል፤ «መብትዎ ትዝ የሚልዎት ታክሲ ውስጥ አይሁን»

ሌላው ስለ ታክሲዎቻችንና ስለ አይነኬዎቹ ቄሳራውያን ሳስብ ግርም የሚያደርገኝ ነገር ቢያንስ እንኳን ለእንጀራቸው ሲሉ ተሳፋሪዎቻቸውን፤ ደንበኞቻቸውን አክብረው የማይሠሩት ለምንድነው የሚለው ነው። ደግሞ እውነቴን ነው። የታክሲ ሾፌሮችም ሆኑ ረዳቶቻቸው እኮ ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበትና ኑሯቸውን የሚመሩበት የገቢ ምንጭ የሚያገኙት ለኅብረተሰቡ በሚሰጡት የትራንስፖርት አገልግሎት ነው። ስለዚህ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚፈልግ ኅብረተሰብ ከሌለ አገልግሎቱን የሚሰጠው አካልም አይኖርም ማለት ነው። የታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኛ ወይም ተሳፋሪ ከሌለ ታክሲውም ሾፌሩም አይኖሩም። እና ታዲያ ሾፌሮቹና ረዳቶች ተሳፋሪው ላይ ይህን ሁሉ ግፍ የሚፈፅሙት ተሳፋሪ ደንበኞቻቸውን ካጡ ሥራቸውንና ራሳቸውንም አብረው እንደሚያጡ ጠፍቷቸው ነው ወይስ የግል መኪና መግዛት ያልቻለው ብዙሃኑ ድሃ እስካለ ድረስ ታክሲ ተሳፋሪ አይታጣም ብለው ነው? መልሱን ለአንባቢ ልተወው።

ለነገሩ ብዙ ጊዜ የሚያደርሱብንን ስቃይ እያብሰለሰልን የሚፈፅሙብን ስቃይ ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው መሆኑን እየረሳን ነው እንጂ ቄሳራውያኑ ደንበኛን ላለማክበርም ሕግ አላቸው። የዚህ አንቀጽም እንዲህ ይላል፤ «ደንበኛ ካልቀበጠ ንጉሥ ነው»። አይነኬዎቹ ቄሳራውያን የታክሲ ሹፌሮችና ረዳቶቻቸው እንግዲህ ይህን ያህል የተራቀቁ ናቸው። በማንኛውም የሥራ መስክ ደንበኛ ንጉሥ መሆኑን ያውቃሉ። ነገር ግን ሕጎች ሁሉ እንደየ መብቀያቸው ነባራዊ ሁኔታ ይለያሉና በእነሱ «ሕገ መንግሥት» ደንበኛ ንጉሥ የሚሆንበት አግባብ ይለያል።

የሕጋቸው ማብራሪያ እንዲህ ይላል፤ «ሌላ ትርጉሜ ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ ሕግ ውስጥ «ንጉሥ ደንበኛ» ማለት «ያልቀበጠ ደንበኛ» ማለት ነው። መቅበጥ ሲሉ ገብቷችኋል አይደል? ያልቀበጠ ደንበኛ ማለት ከታሪፍ በላይ ሂሳብ ሲያስከፍሉት ዝም የሚል፣ በአንድ ወንበር ላይ ለሦስት እንዲቀመጥ ሲታዘዝ «ከፍዬ እኮ ነው የምሄደው እንዲህ ሆኜ አልሄድም» የማይል፣ በአቋራጭ ለመሄድ ያለ ሰፈሩ ጥለውት ሲሄዱ ለምን ብሎ የማይጨቃጨቅ፣ ሲሰድቡት፣ ሲደበድቡት፣ ሲዘርፉት «ቀብጦ መልስ የማይሰጥ» ደንበኛ ማለት ነው።

ታዲያ እነ አብየ የታክሲ ሾፌርና ረዳት ሕግ ባለበት አገር የራሳቸውን ሕግ አውጥተው መተዳደሪያ እንጀራቸው መሆኑን እያወቁት በተገልጋይ ደንበኞቻቸው ላይ ይህን ያህል ግፍና በደል ሲያደርሱ የማይጠየቁ አይነኬ ባሥልጣን እንዲሆኑ ያደረጋቸው ማን ነው? እውነት እውነት እልሃለሁ! እስከ መጨረሻው ድረስ ሄደህ መብትህን መጠየቅና ራስህን በማስከበር ሰው ሰውነቱን ሲያስከበር ሕግ የትም ሊኖር እንደሚችል እንዲያውቁት ማድረግ ሲገባህ «ሕግ ያለው ፍርድ ቤት ብቻ ነው» እያሉ ሲቀልዱብህ ዝም ያልከው፣ ታክሲ ውስጥ መብትን መጠየቅ አይቻልም እያሉ ሲዝቱብህ፣ መብትህን ስትጠይቅ ደግሞ «ቅብጢ» እያሉ ሲሰድቡህና ሲያዋርዱህ...ልክ እንደ ግዑዙ ታክሲያቸው ወደ ፈለጉት ሲነዱህ ዝም ያልከው አንተው ራስህ ተሳፋሪያቸው ነህ። እንደፈለጉ ሲያደርጉህ አሜን ብለህ የተቀበልከው በዝምታ መርቀህ፣ በስንፍና ቀብተህ በገዛእጅህ ያነገስካቸው ፈላጭ ቆራጭ አይነኬ ቄሳር ፈርኦን ያደረግካቸው አንተው ንግሥናህን ያላወቅከው «ንጉሡ» ደንበኛቸው ነህ። አንተም ግን አይፈረድብህም፣ አማራጭ ብታጣ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## ፕሬዚዳንት ፑቲን «ዓለምን በበላይነት ለመቆጣጠር የሚደረገውን ሙከራ» እንደማይቀበሉ ገለጹ

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን «ዓለምን በበላይነት ለመቆጣጠር የሚደረገው ሙከራ» እንደማይቀበሉ ለቻይናው አቻቸው ፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ ገለጹ። የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን እና የቻይና አቻቸው ዢ ጂንፒንግ የዩክሬን-ሩሲያ ጦርነት ከተጀመረ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ በኡዝቤኪስታን መዲና ሳማርካንድ ተገናኝተዋል።

ሁለቱ መሪዎች የሻንጋይ የትብብር ድርጅት የመሪዎች ጉባኤ ላይ የጎንዮሽ ውይይት ያደረጉ ሲሆን፣ ፑቲን «አንድ የማይታወቅ ዓለም ለመፍጠር የተደረጉ ሙከራዎች በቅርብ ጊዜ በጣም አስቀያሚ ቅርጽ እየያዙ ነው፤ እናም ፈጽሞ ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው» ሲሉ ለቻይናው አቻቸው መናገራቸውን ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

የፑቲንን ሃሳብ የሚጋሩትና «የቀድሞ ጓደኛዬን» በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ ያሉት ፕሬዚዳንት ዢ በበኩላቸው ቻይና ከሩሲያ ጋር ለመሥራት እንደምትፈልግ ለፑቲን አረጋግጠውላቸዋል።

አክለውም ቻይና «በተመሰቃቀለ ዓለም ውስጥ መረጋጋት እና አዎንታዊ ጉልበት ለማስፋፋት ትፈልጋለች» ብለዋል።



በሌላ በኩል መሪዎቹ የዩክሬን አሁናዊ ሁኔታን አንስተው የተወያዩ ሲሆን፣ የቻይናው ፕሬዚዳንት የዩክሬን ጉዳይ እንደሚያሳስባቸው ለፑቲን መናገራቸውን ዘገባው አመላክቷል።

ዢ በዩክሬን ጉዳይ የተለያዩ ስጋቶችና ጥያቄዎች እንደነበራቸው እረዳለሁ ያሉት ፑቲን የቻይናው መሪ በዩክሬን ጉዳይ ያንጸባረቁትን «ሚዛናዊ አቋም» እንደሚያደንቁ ገልጸውላቸዋል።

«ከዩክሬን ቀውስ ጋር በተያያዘ የቻይና ወዳጆቻችንን ላሳዩት ሚዛናዊ አቋም ትልቅ ክብር አለን» ሲሉም ነው ፑቲን ለዢ የገለጹላቸው።

መልካም የሚባል ግንኙነት እንዳላቸው የሚነገርላቸው መሪዎቹ በኡዝቤኪስታን ፊት ለፊት ሲገናኙ ሩሲያ በዩክሬን ላይ ወታደራዊ ዘመቻ ከጀመረች ወዲህ የመጀመሪያ ነው ተብሏል፡፡

በተለይም በኮሮና ምክንያት ኩፉኛ የተፈተነችው አገር መሪ ለሆኑት ለቻይናው ፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ የመጀመሪያ የባህር ማዶ ጉዞ መሆኑን አልዓይን ዘግቧል።

የመሪዎቹ መገናኘት በዩክሬን ጦርነት ምክንያት ዓለም ፊቱን ላዞረባት ሞስኮ ትልቅ ፋይዳ እንዳለውም እየተገለጸ ነው።

ሞስኮ እና ቤጂንግ በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ባላቸው ግንኙነት የቅርብ አጋሮች ሆነው ብቅ ያሉበት አጋጣሚ ተፈጥሯል።

## አሜሪካ ለዩክሬን የረጅም ርቀት ሚሳኤል ከሰጠች ሩሲያ ራሷን ለመከላከል የትኛውንም አማራጭ እንደምትጠቀም አስታወቀች

አሜሪካ ለዩክሬን የረጅም ርቀት ሚሳኤል ድጋፍ የምታደርግ ከሆነ ሩሲያ ራሷን ለመከላከል የትኛውንም አማራጭ እጠቀማለሁ ስትል አስጠነቀቀች፡፡ የሩሲያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ማርያ ዛካሪቫስ እንደገለጹት፣ አሜሪካ ከዓለም አቀፍ ሕግ ውጪ ለዩክሬን መጠነ ሰፊ የጦር መሣሪያ በማቅረብ የጦር ወንጀል እየፈጸመች ነው፡፡

ዋሺንግተን በዚህ ድርጊቷ ገፍታ ለኪዬቭ የረጅም ርቀት ሚሳኤል የምታቀርብ ከሆነም ቀይ መስመር እንዳለፈች እና በግጭቱ በቀጥታ እንደተሳተፈች እንቆጥረዋልን ማለታቸውን ኤፍቢሲ ዘግቧል። ሞስኮ ራሷን ለመከላከል እና ሉዓላዊነቷን ለማስከበርም የትኛውንም አማራጭ ለመጠቀም የምትገደድ መሆኗን ነው ቃል አቀባዩ ያሳወቁት፡፡

ምዕራባውያን እስካሁን የተለያዩ ጦር መሣሪያዎችን ለዩክሬን አቅርበዋል። ይሁን እንጂ ዩክሬን የምትሻውን ዓይነት ከባድ ጦር መሣሪያዎችን በቀላሉ ማግኘት አልተቻላትም። በጦርነቱ ግንባሮች ላይም ዩክሬናውያን የከፍተኛ ጦር መሣሪያ ብልጫ ተወስዶባቸው እንደነበር ይታወሳል።

አሜሪካ ለዩክሬን ሡራዊት የጦር መሣሪያዎችን በማቅረብ ከየትኛው አገር በላይ ከፍ ያለ ወጪ እያደረገች ነው። ዋይት ሐውስ እንደሚለው፤ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ሥልጣን ከያዙ በኋላ ዋሽንግተን የኪዬቭን ደኅንነት ለማጠናከር 6.3 ቢሊዮን ዶላር ሰጥታለች።



ከአሜሪካ በመቀጠል ደግሞ ዩናይትድ ኪንግደም እና ፖላንድ በቢሊዮን የሚያስወጡ በርካታ የጦር መሣሪያ ድጋፍን አቅርበዋል። ዩናይትድ ኪንግደም በበኩሏ ከጦርነቱ ለዩክሬን የሰጠች ሲሆን፤ አሁን ደግሞ ጅማሬ አንስቶ እስካሁን 1.6 ቢሊዮን ዶላር ወታደራዊ ድጋፍ ተጨማሪ 1.2 ቢሊዮን ዶላር ለመስጠት ማቀዷን ማስታወቋ የሚታወስ መሆኑን ይታወቃል።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# የአደይ ዝማሬ!

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

አደይን የማያውቃት ማን ይኖር ይሆን? አደይ ወቅትን ጠብቃ አዲስ አመትን ልታበስረን በወርሃ መስከረም ብቅ ብላ የምታደምቀን አበባ ነች፤ አደይ አበባ። አደይ ወቅትን ጠብቃ መጥታ ወቅትን ጠብቃ ትሄዳለች፤ እንደ ህይወት። የእያንዳንዳችን ህይወትም በሆነ ወቅት የተገኘ የሆነ ጊዜ ደግሞ ምድርን የሚለቅ ነው። መነሻውም ሆነ መድረሻዋ በወቅት የሚገለጽ። አደይ በወቅት ውስጥ ትርጉም ያላት፤ በወቅት ውስጥ የምትኖር። በወቅቷ መጥታት የወቅቷን መልእክት አስተላልፋ የምትሄድ፤ የወቅት መልእክትኛ። የዘንድሮዋ አደይ ግጥም ገጥማ ግጥሟንም በዜማ አዋዝታበአደባባይ ላይ ወጥታ እየዘመረች ነው። ዝማሬውን የሰሙ ዝማሬ ይሆን እንጉርጉሮ እየተምታታባቸው ቢሆንም። በአደባባይ የተገኘ ሰው አደይን ለመስማት ግር ብሎ ወጥቶ የተገኘ ነው። በመገረም ለመመልከት፤ በመገረም ዝማሬን ለመስማት የሆነ ግር ማለት። የዝማሬዋ አዝማች እንዲህ ይላል፤

*ዘመን ሄደ ዘመን መጣ፤*
*ሰው ተዘርቶ አፈር ወጣ፤*
*ሰው ከአፈር መሆኑ ቀርቶ፤*
*አፈር ተመዘነ ከሰው ቀሎ፤*

ዝማሬ ወይንስ እንጉርጉሮ ብያኔው ለእያንዳንዱ አድማጭ የተለያየ ሊሆን ይችላል፤ በአደባባይ የሚሰማው ግን በቃ ይኸው ነበር። የአደይ ዜማ በአንድነት የሰበሰባቸው የወቅቱን መልእክት ለመስማት የተሰበሰቡት ወደ መጡበት ሲመለሱ ግን በሃዘን ውስጥ ሆነው ነበር።

ሚዲያ ላይ ስለ ወቅቱ የአደይ ዝማሬ አስተያየታቸውን የሚሰጡም ብዙ ነበሩ። "ጥበብ አቅሟ የሚታወቀው እንዲህ ባለ ወቅት ነው" በማለት የሥነ-ጽሑፍ አስተማሪው የአደይ ዝማሬን ተከትሎ በአንዱ ሚዲያ ቀርበው እየተነተኑ ነው። የአፈር አጥኚ ባለሙያ ደግሞ "አደይ በአፈር ውስጥ ስላለው እውነት በዜማዋ እንዴት እንደገለጠች የሚያስገርም ነው። አፈር ለሰው ልጅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የሚያስረዳ ዝማሬ ነው። አፈርና የሰው ልጅ ፈጽሞውኑ ሊነጣጠሉ እንደማይችሉ አደይ እያስተማረችን" ሲሉ ድምጻቸውን አሰሙ። የፖለቲካ አጥኚ ግለሰብ ደግሞ በሌላ ሚዲያ ላይ ቀርበው "የአደይ ዜማ ስለ ወቅቱ የሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ብዙ የሚለው አለ። በጦርነት ሰው እረግፎ አፈር እየሆነ፤ ከአፈር የመጣው ሰው ወደ አፈር እንዲህ እየተመለሰ፤ መንገዳችን ማስተዋል የጠፋው ሲመስል ነው አደይ ለዜማ መውጣቷ" አሉ። የሃይማኖት አስተማሪው እንዲሁ በአንድ ሃይማኖታዊ ሚዲያ ላይ ቀርበው ስለ ዘመን አቆጣጠር እና በዘመናት ውስጥ የሰው ልጅ አፈር እየገፋ እንዴት ህይወትን ቅርጽ እንደሰጡ፤ይህም የሰው ልብ በላቡ ወንዝ እንጀራን እንዲበላ ከተጣለበት ኃጢአትን ተከትሎ ስለመጣው ትእዛዝ እንደሆነ እየተረኩ ነው። ነጋዴው በበኩሉ የሚዛን ጉዳይ አሁንም ቦታ ሊሰጠው የተገባ እንደሆነ ነጋዴው ከጊዜያዊ ጥቅሙ ባሻገር ስለ ህዝብ ማሰብ እንዳለበት የሚገባ መሆኑን አደይ በዜማዋ መልእክት እያስተላለፈች እንደሆነ ተረድቶ ማብራሪያ ሰጥቷል።

የአደይ ዝማሬ አይሉት እንጉርጉሮ ብዙ መነጋገሪያ ሆኖ ቀጠለ። አደይ በተገኘችባቸው አደባባዮች ግን የወቅቱን መልእክቷን እያሰማች ጉዞዋን ቀጥላለች። አደይ የዘንድሮው ወቅቱ የሰጣትን ጊዜ ስትጨርስ ትሰወርና ቀጥሎ ባለው አዲስ ዓመት ደግሞ ትመጣለች። የሰው ልጅ ግን ከትላንት ታሪኩ ሳይማር ትላንትን ዳግም እየደገመ ከአንድ ችግር ወደ ሌላ ችግር እየተሸጋገረ በሰላም መኖር እየቻለ በጸብ ውስጥ ዘመኑን ይጨርሳል።

አደይ የሰው ልጅ በምድር ላይ የሚያደርገውን ድርጊት በሙሉ ስትታዘብ ትቆይና የኢትዮጵያውያን የዘመን መለወጫን መነሻ አድርጋ መልእክት ይዛ ትመጣለች። መልእክቷ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከበደ የመጣ መልእክት ነው። የሰው ልጅ የምድር ላይ ክፋት ከቀን ወደ ቀን እንዴት እየጨመረ መሆኑን ተረድታ አመቱን ሙሉ ስትቆዝም ቆይታ በአጭር ጊዜ መገለጧ እውነቷን ተናግራ መልሳ የምትደበቅበት የወቅት ድምጽ የመሆን ልማድ።

የአደይን ጥበባዊ ምልከታ ተመልክተው አካሄዳቸውን ስንቶቹ ማስተካከል እንደቻሉ አደይ እርግጠኛ አይደለችም። ጥበብ ግን ሁሌም ትናገራለች። አስተዋይ ሰው ጥበብን ገንዘቡ ያደርጋል። በጥበብ ውስጥ የትላንት ውድቀት የዛሬን ቤት መስሪያ ትልቅ ግብዓት መኖሩን አስተዋይ ብቻ ይረዳል። አመቱን ወደ ኋላ በጥበብ መነጽር ውስጥ መመልከት የቻለ የአደይን ጥሪ በተረዳ ነበር። አደይ ልትል የፈለገቻውን ለራስ በሚመች መንገድ ተርጉሞ መነሳት ይቻላል። እውነታውን ፊትለፊት እንጋፈጥ ከተባለ ግን ወደ ኃላም ሆነ ወደጎን ሳይባል በእውነት መቆም ይቻላል። ጥበብ የምትነግረን እውነት ከአፈሩ በላይ የከበረው የሰው ልጅ አጠገባችን ያለ መሆኑን ነው።

አጠገባችን ያለው የሰው ልጅ እንደ አደይ ወቅትን ጠብቆ ብቅ ብሎ የሚጠፋ መልሶ የሚመጣም አይደለም፤ ሁሌም አብሮን ያለ እንጂ። ዛሬ ታክሲ ላይ ይሆን የዳቦ ሰልፍ ላይ፤ ስብሰባ ላይ ይሁን የምንኖርበት ጊቢ ውስጥ፤ በግራም ይሁን በቀኝ በራሳቸው ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ተሰልፈዋል። አደይ የሰው ልጆች በአጠቃላይ እየኖሩት ያለውን ኑሮ ተመልክታ ያዜመችው ዜማ ውስጥ እኛ ከአጠገባችን ካለው ሰው ጋር ያለን መስተጋብርም አካል ነው።

ከአደይ የወቅቱ መልእክት ውስጥ ሁለት ነጥቦችን አውጥተን 2015ን አብረን እንቀበል። አፈር እና ሰው።

**አፈር**

"አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ" የሚለው የፈጣሪ ቃል ደጋግሞ ሲነገር ሰምተናል፤ እውነቱም እንዲያ ሆኖ የትላንት ትውልድ አፈር ሆኖ እነሆ አፈር ከሰፈራችን አለ። ከመነሻው አፈር የሆነው አፈር እና ከአፈር የሆነው የሰው ልጅ ወደ አፈር እየተመለሰ የሆነው አፈር ተደባልቀው እነሆ አሉ። አፈሩም ለግብርናም ሆነ ለአምራቹ ዘርፍ ግብዓት ሆኖ የሰውን ልጅ እያገለገለ ነው። አፈሩ ታርሶ ምርትም እየሆነ ነው።

የዘንድሮ የጳጉሜ ቀናት መካከል አንዱ የሆነው ጳጉሜ ሁለት የአምራችነት ቀን ተብሎ ተሰይሞ ስለ አምራችነት መልእክቶች ሲተላለፉ ሰምተናል። የእርዳታ ጥገኛ የሆነች ሀገር ውስጥ ስንኖር የአምራችነት ቀን ተደጋግሞ የሚነሳ ቀን ሊሆን እንደሚገባው እያሰብንም ቀኑን አሳልፈነዋል። አምራችነት ከአፈር ጋር የተሳሰረ ሆነና አፈራችንን በመጠበቅ ውጤታማ አምራቾች ለመሆን በአፍር ጥበቃው ብዙ ለመስራትም እንደከማለን። አፈርን ከአደጋ ለመጠበቅ የሚመለከተው መንግሥታዊ አካልም ጥንቃቄ እንዲደረግ ሲሰራም ይታያል። ባእድ ነገሮች ወደ ሀገር ገብተው አፈራችን እንዳይበከል ለማድረግ የሚሰራው ስራም እንዲሁ የሚጠቀስ ነው። አፈር ውስጥ የተቀመጡት ማእድናት በወቅቱ ወጥተው ለሀገራችን ጥቅም የሚሰጡ እንዲሆኑ እንዲሁ የሚሰራው ስራም ከዜና ገጾች ላይ ይነበባል። ዛፍ የመትከል ልማድም እያደገ እንዲመጣ የሚሰራው ስራ ከአፈር ጥበቃ ጋር ያለው ግንኙነት ቀጥተኛ ነውና ሊነሳ ይችላል። ስለ አፈር የዘርፉ ባለሙያዎች የሚሉት ዝርዝር ነገርን ለባለሙያዎች ሰጥተን ስለ አፈር ከትላንት ዛሬ እየተሻገረ የመጣው የፍትሕ አሰጣጥ መንገዳችንን ግን እንመልከት። ስለ አንድ ስንዝር መሬት የሚከፈለው ዋጋ፤ ስለ እፍኝ አፈር የሚፈሰው ደም። አንድ ዝንዝር መሬትን አሳልፎ ላለመስጠት ህይወትን በመገበር ጭምር የሚደረገው ኢትዮጵያዊ ባህላችን ስለ ሀገራችን ቁራሽ መንገድ ያለንን ቀናኢነት በሰፊው የሚያሳይ ነው። የኢትዮጵያን አፈር በጠላትነት የረገጡ ወራሪዎች ከባድ ዋጋ እንዲከፍሉ ያደረገ የታሪክ ገጾችን ጥቂት አይደለም። የሌሎችን ያለመፈለግ የራስንም አሳልፎ ላለመስጠት የተደረጉት ተጋድሎዎች በኢትዮጵያ አፈር ዙሪያ ሃሳብን ማዋጫ ጉዳይ ሊሆንም ይችላል። ከሌሎች ጋር ስለ አፈራችን የገባነው ፍልሚያ እንዳለ ሆኖ እርስበእርሳችን ያደረግነውም የታሪካችን አንድ አካል ሆኖ ግን ድምር ውጤታችን ኪሳራ ውስጥ እንዲገኝ አድርጎታል። የአፈር ወረት ከማህበራዊ ወረታችን በላይ ሆኖ በግትርነት ያጠፋነው ጥፋት።

ጥበብ ስራዋን ስትሰራ በታሪካችን ውስጥ እድገት ያለውን ቦታ ታሳየናለች። ትላንት እና ዛሬን በማነጻጸር እድገታችንን እንድንፈትሽ የሚያደርግ። ግለሰባዊም ሆነ ማህበረሰባዊ እድገት ላይ ጥናት የሚያደርጉ ተመራማሪዎች የትላንት ጉዞ በዛሬው ላይ ያለውን ተጽእኖ በስፋት ያነሳሉ። ኢትዮጵያውን ስለ ማንኛውም ጉዳይ ከእዚህ ቀደም የሄዱበት መንገድ ለዛሬውም የመምጣቱ እድል ሰፊ ነው። በትላንት ችግር አፈታት ውስጥ ፍጹም ሰላማዊ የሆኑ መንገዶች እንዳሉ ሁሉ ጦርኝነትም የሚይዘው ስፍራ ብዙ ነው።

በአፈራችን ላይ የፈሰሰው ደም፤ ከአፈር ጋር ተደባልቆ አፈር የሆነው ኢትዮጵያዊ የጦር ሜዳ ውሎ የታሪካችንን ገጾች የተቆጣጠረ ነው። የሰላም መንገድ የተናቀና መናኛ መንገድ ሆኖ ነገሮችን በብረት ለመፍታት የመሄድ መንገድ አፈርን አብዝቶ ይሆናል እንጂ ሰውን ሊያባዛው አልቻለም። የበዛው አፈርስ እንደ ብዛቱ ፍሬን መስጠት ስለመቻሉ ከእውነት ጋር ሆኖ የሚጠይቅ ሰው የማያሻማ መልስ ያገኛል። ከደም የተነሳ ምድር ፍሬዋን እንደምትከለክል የቃየልና አቤል ታሪክ አስተማሪ ሆኖ እናገኘዋለን። ቃየን በቅናት ተነሳስቶ የሄደበት መንገድ ለጊዜው አቤልን በማጥፋት አሸናፊ የሆነ ቢመስልም አቤል ወደ አፈርነት በመቀየሩ ምድር ፍሬዋን እንዳትሰጥ ተከለከለች። በምድርም ላይ ተንከራታችና ተቅበዝባዥ መሆን ቀጠለ። የሰው ደም አፈሩ ምርታማ እንዳይሆን የሚያደርግ ነዋሪውም ተቅበዝባዥ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። ከፈረንጆቹ ሚሊኒየም በኋላ የተጠኑ ጥናቶች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የመንቀሳቀስ ወይንም የስደት ኑሮ ከግማሽ በላይ የጨመረ መሆኑን ያሳያል። ስደት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የቅርብ ጊዜ ታሪክ እንደሆነ ቢነገርለትም ከፍተኛ የሰው ደም መፍሰስ ባስከተሉ የለውጥ ወቅቶች የነበሩ ስደቶች ከፍተኛ ደረጃውን ይዘው በእያንዳንዱ ቤት ጓዳ ውስጥ ስደትን የተከተለ የሃዘን መዝገብ እንዲከፈት ምክንያት ሆኗል።

ዛሬ በኢትዮጵያ አፈር ላይ የምንኖር ፈጽሞውኑ ከትላንት መንገድ በመመለስ ልዩነቶቻችንን በሰላም የመፍታትን ልምምድ ማድረግ እንዳለብን የግድ ይላል። ስለ ሰላም የሚኬደው የትኛውም እርቀት አሸናፊ የሚያደርገው ሁሉንም ነው። የዘንድሮዋ አደይ እንጉርጉሮ በሚቀጥለው ወደ ሙሉ ደስታ ይቀየር ዘንድ የኢትዮጵያ ልጆች አብረን አፈሩ ላይ ቁጭ እንበል። አብረንም በፍቅር በመተማመን እንቀመጥ። አንዳችን በአንዳችን ቁስል ላይ እንጨት ከመስደድ ተጨማሪ ቁስል ውስጥ ላለመግባት ሰላማችንን ለመፍጠር እንሰማራ። ስለ ሰላም ጎዳና መሰየሙ ደስ ያሰኛል፤ ለእውነተኛ ሰላም ቁጭ ብሎ አብሮ መጨነቅ መቻል ደግሞ የበለጠ ደስ ያሰኛል። ከአፈሩ በላይ የሆነ ስላለ፤ ሰው።

**ሰው**

ሰው ማለት በቃ ሰው ነው፤ በውስንነት የሚኖር የፍጥረት ሁሉ ቁንጮ ፍጥረት። ሰው ከተገኘበት ከምድር አልፎ ወደ ሌሎች ዓለም በመሄድ ሌሎች ፍጥረቶችን ለማጥናት አመታትን የሰጠ ሃብቱንም እያፈሰሰ ያለ በእውቀት እረክቶ የማይቀመጥ እጅግ አስደናቂ ፍጥረት። በሰው አካላዊ ውቅር ላይ ጥናት የሚያደርጉ ተመራማሪዎች አካላትን የበለጠ ለማወቅ ጥናት በተደረገ ቁጥር የሚደረስበት መደምደሚያ ሰውን አጥንቶ መጨረስ የማይቻል መሆኑን አመላካች ነው። ሰው እንኳን በሰው፤ በፈጣሪውም የጸጸት ምክንያት እንደሆነ የተጻፈለት ነው፤ የቆንጆዎች መጽሐፍ ደራሲ "አስቀድሞ ነው እንጂ መጥኖ መደቆስ" ብሎ የተሳለቀበት የመጽሐፉ ክፍል። ፈጣሪ በስራው የማይሳሳት ቢሆንም ከፍጥረቱ ሁሉ ግን በሰው የተቸገረ መሆኑን የሃይማኖት አስተማሪዎች ደጋግመው የሚያነሱት ነው፤ ሁላችን ደግሞ በኑሯችን የምንረዳው።



ሰውን መርምሮ አለማወቅ አንድ ጉዳይ ሆኖ እያለ እያንዳንዱ ሰው ስለ ሰው የሚኖረው አተያይ ግን ሊኖር ግድ ነው። ሰውን በሙሉ ክፋት ወይንም ሰውን በፍጹምነት የማየት የሁለት ጥግ አስተሳሰብ ትክክለኛ አይደለም። ሰው ሁሉ ክፉ፤ ሰው ሁሉ ደግ አይደለም። ከሰው ውስጥ በመልካምነት የምንገልጻቸው ሰዎች አሉ፤ ከሰው ውስጥ በክፋት የምንገልጻቸውም እንዲሁ።

በአደይ ዝማሬ ውስጥ ሰው አደይ ሚዛኑ የቀለለ እንደሆነ እና ከሰውነት ይልቅ ግዑዝን መከተል የቀደመ መሆኑን ትናገራለች። የዓለማችን የሃይል አሰላለፍ እንካ በእንካ ሆኖ እውነትና መርህ ሳይሆን ይዞ መገኘት የትክክለኛነት ማሳያ እየሆነ እንዳለ እናያለን። ሰዎችን በሰውነታቸው የመመልከትና አጠገባችን ያለ ማናቸውም ሰው ከሰውነቱ የሚመነጨው ታላቅነቱን የመረዳት ስራ መሰራት አለበት።

ሰዎች ከአጠገባቸው ሰው የሆነ ሰው ባጡ ቁጥር ወደ መገለልና ራሳቸውን ወደ መጉዳት ይገባሉ። ያለፉት ሃያ አመታት ውስጥ የታየው እውነት በየአመቱ ራሳቸውን የሚያጠፉ ሰዎች ቁጥር ከ30% በላይ የጨመረ መሆኑን ነው። ሰዎች ትኩረትን የሚፈልጉ ፍጥረቶች ናቸው። ፍጥረትም በሙሉ ስለ እነርሱ የሆነላቸው ልዩ ፍጥረቶች።

ሰዎች ትኩረት እንድንሰጣቸው የሚያደርገን የመጀመሪያው ምክንያት ሰው መሆናቸው ነው፤ ቀጥሎ አሁንም ሰው መሆናቸው ነው፤ ሲሰልስም ሰው መሆናቸው ነው። ከመልካምነታቸው ይሁን ከክፋታቸው ባሻገር እንዲሁ ሰው በመሆናቸው ልዩ ፍጥረት ናቸው፤ ልዩ ትኩረት፤ ልዩ ቦታ፤ ልዩ እይታ የሚገባቸው። የሰዎችን ሙብት ከማክበር አልፈው ስለ እንስሳት ሙብት ለመሞገት የሚደራጁ፤ ሚሊዮኖችን የሚበጅቱ፤ ቢሮ የሚከራዩ፤ ሙሉ ጊዜ ሰራተኛን የሚቀጥሩ ወዘተ ስንመለከት ከፍጥረታት ሁሉ የገዘፈው ፍጥረት እንዴት የከበረው ነገር እንዲገባው እናስተውላለን። ከፍጥረታት ሁሉ የተሻለውን ሊያገኝ የሚገባው ፍጥረት። ከሰዎች ጋር ስለሚኖር ግንኙነት ልንኖራቸው ስለሚገቡ መርሆች የተለያዩ ጸሃፍት የየራሳቸውን ብዙ ብለዋል። እማሆይ ትሬዛ ቀላል ህይወትን እያንዳንዱ ሰው ቢኖር ሌላው ሰው ህይወትን በቀላሉ መኖር የሚችልበትን እድል እንደሚያገኝ መናገራቸው ይጠቀስላቸዋል። ከእርስ በእርስ ህይወት ውስጥ በስፋት ተቀባይነትን ያገኘው አስተሳሰብ አንድ ሰው ለእራሱ እንዲደረግለት የሚፈልገውን ለሌሎች እንዲያደርግ የሚያስተምረው የክርስቶስ ትምህርት ነው።

**ውድ ወገኖቼ፤**

የአደይ ዝማሬን አድምጠን ሚዛናችንን በማስተካከል ለሁላችንም መልካሙን የምንመኝበት ደግሞም የምናደርግበት ዘመን ከፊታችን እንዲሆን እሻለሁ። መልካሙን!

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የከተማ ግብርና ስኬታማነት ማሳያው ዶክተር ጋሻው

ኃይሉ ሣህለድንግል

የአፈር ሳይንስና ጂኦግራፊክ ኢንፎርሜሽን ሲስተም ባለሙያና የሀወሳ ዩኒቨርስቲ መምህር ናቸው ። የዛሬ የስኬት አምድ እንግዳችን። ለስኬት አምድ ስናስባቸው የዩኒቨርስቲ መምህርነት ወይም አካዳሚክ ህይወታቸው አይደለም የሰባን። በሀዋሳ ከተማ በመኖሪያ ቤታቸው ግቢ በሚያካሂዱት የከተማ ግብርና ተጠቃሽ መሆን መቻላቸው ነው። የከተማዋን የአረንጓዴ ልማትንም ያማክራሉ፤ ዶክተር ጋሻው ምትኬ።

በቅርቡ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በ2015 በጀት አመት በሚያከናውናቸው እቅዶች ላይ ከመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ጋር ለመስራት እንዲያስችለው ካዘጋጀው መድረክ ጎን ለጎን የሀዋሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ፕሮጀክቶችን አስጎብኝቶ ነበር። ከፒያሳ ወደ ሴንትራል ሆቴል እና አሞራ ገደል የሚወስደውን ውብ መንገድ ይዘናል። አሞራ ገደል ልንደርስ ጥቂት ሲቀረን ዋናውን መንገድ ወደ ቀኝ ትተን ወደ ግራ ታጠፍን። መኖሪያ ቤታቸው አካባቢ ደርሰን፤ ዶክተር ጋሻው ከውጭ ተቀብለውን ወደ ግቢያቸው ይዘውን ዘለቁ። ዶክተር ጋሻው ምትኬን ያገኘናቸውም፣ የማዘጋጃ ቤቱ ምክትል ሃላፊ አቶ ታሪኩ ታመነ የእኚህን ሰው የከተማ ግብርና ስራ እንድንጎበኝ ባመቻቹት መሰረት ነው።

ግቢው በእጅጉ ይማርካል፤ የጓሮ አትክልቶቹ፣ የፍራፍሬ ተክሎቹ፣ ቡናው፣ አበቦቹ፣ ሳሩ ግቢውን በእጅጉ አስውበታውታል። መሬቱን ብቻ አይደለም ያለሙት፤ በሽቅብ ግብርናም/ ቨርቲካል ፋርሚንግ/ አጥሩንም፣ ግድግዳውንም አትክልት በአትክልት አድርገውታል። ሳሩ ተከርክሞ ሲታይ ከመጥበቡ በስተቀር ስታዲየም ይመስላል። ችግኝ የሚያፈሉበት ስፍራም አላቸው።

ዶክተር ጋሻው፣ የተወለዱት በጅግጅጋ ከተማ ነው። የወታደር ልጅ ነኝ ይላሉ። አሁን ወደ ጡረታው እያልኩ ነኝ የሚሉት ዶክተር ጋሻው፣ ረጅም፣ ገዘፍም ያሉ ናቸው። በእዚህ እድሜያቸውና ቁመናቸው ያን ልማት ጎንበስ ቀና እያሉ ይሰሩታል ተብሎ አይታሰብም። እሳቸው ግን የግቢያቸውን አትክልቶች ብቻ ሳይሆን ከግቢያቸው ውጪም ተሻግረው ይሰራሉ።


የከተማ ግብርናውን ከጀመሩ ሁለት አመታት ተቆጥረዋል፤ ዶክተር ጋሻው በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥም በዩኒቨርሲቲው ግብርና ኮሌጅ ግቢም በአረንጓዴ ስፍራ ልማት ሰርተዋል፤ ሀዋሳ አሁን ለያዛችው ገጽታ ታስክ ፎረስ በመምራትና በፈቃደኝነት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ይናገራሉ። አሁን ወደሚኖሩበት አካባቢ ሲመጡም የነዚያ አካባቢዎች ተሞክሮ ማስፋታቸውን ይገልጻሉ።

በየቀኑ ማለዳ 11፡30 ተነስተው የአካባቢውን አረንጓዴ ስፍራ በሙሉ በረጅም ቱቦ ውሃ ያጠጣሉ። በዚህም እናቶች ይመርቋዋል፤ ወደ ግቢያቸው ተመልሰውም ተመሳሳይ ስራ ይሰራሉ። የውጪውን ቢያንስ በሳምንት ሁለት ሶስት ቀን ፣ የግቢያቸውን ግን በየቀኑ ውሃ ያጠጣሉ። በእሳቸው አቅም ያልሆነውን ደግሞ ሌሎች ያግዟቸዋል።

እሳቸው እንደተናገሩት፤ የከተማ ግብርናውን የሚያካሂዱት ከ600 እስከ 700 በሚሆን ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ነው። በዚህ የአትክልት ስፍራ ሶስት አይነት ስራዎች /ኮምቢኔሽን/ ይታያሉ። መሀል ላይ የፍራፍሬ ተክሎች፣ /አቦካዶ፣ ፓፓዬ፣ ማንጎና ሮማን እና ቡና/ አላቸው። እንደምታዩት ደግሞ አበቦች አሉ የሚሉት ዶክተር ጋሻው፣ የአትክልትና የመሳሰሉትን ችግኞች ያፈላሉ፤ ችግኞቹም የአትክልት ምርቶቹም ከእሳቸው ፍጆታ በላይ ናቸው። ‹‹ቆስጣ በጣም ጥሩ ተከል ነው። አራት አምስት ጊዜ ምርት ይሰጣል ሲሉ ገልጸው፣ እሳቸው ለገበያ እያመረቱ አይደለም፤ ከፍጆታ ውጪ ያለውን ምርት ገጠር አካባቢ እንደሚደረገው ለማህበረሰቡ ይሰጣሉ።

ለአትክልት መትከያ እቃ ፍለጋ ሲሉ አንዳንዴ እቃዎችን በቆራሌ መልክ እንደሚሰበስቡም ነው የሚናገሩት። ለአትክልት መትከያ የሰበሰቧቸውን የዘይት እቃና የመሳሰሉትን ቁሳቁስን አሳዩን። ጣሳው ተበስቶ አፈር ተሞልቶ ጊዜውን ጠብቆ ችግኙ ይተከላል፤ የሚፈላም ከሆነ ዘሩ ይዘራል።

ለከተማ ግብርናው ላንድስኬፕ ሌላው ኮምፓነንት ነው የሚሉት ዶክተር ጋሻው፣ የአትክልት የአበባ የሳር አይነቶችን ይሰበስባሉ፤ ሳሩ እንደመጣ አይተከልም፤ እየተበተነ ነው በመስመር የሚተከለው፤ ፍግ ያደርግበታል፤ ውሃ በአግባቡ እንዲጣጣ እየተደረገም ነው ውብ ሊሆን የቻለው። በእዚህ ላይ ችግኞች ያዘጋጃሉ።



ዶክተር ጋሻው ምትኬ

ዶክተር ጋሻው፣ የተሻሻለ የፓፓያ ዝርያ ከደቡብ ክልል የአትክልት ባለሙያዎች ወስደው ለመትከልም አቅደዋል፤ በጣም በአጭር ጊዜ የሚደርስ ሬዲሜድ የሚባል ዝርያ ነው፤ አይታችሁት ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወላይታ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት የጎበኙት የፓፓያ ዝርያ ነው፤ በጣም ጣፋጭ አጭርና በትንሹ 60 እና 70 ፓፓያ የሚይዝ ነው ። እሱን በብዛት መትከል እፈልጋለሁ ሲሉ ገለጹልን።

የአርሶ አደር ልጅ አይደሉም፤ የወታደር ልጅ ናቸው፤ ታዲያ ትምህርታቸው ወይስ ያደጉበት አካባቢ ነው ወደ ከተማ ግብርና እንዲያዘነብሉ ያደረጋቸው? ከተባለም፤ ሁሉንም አይደሉም። እርግጥ ነው ዶክተር ጋሻው ፕሮፌሽናሊ ለግብርና የተጠጉ ናቸው። በከተማ ግብርናው ላይ ይህን ያህል እንዲያተኩሩ ያደረጋቸው ግን ይህ ምክንያትም አይደለም። ባደጉበት አካባቢ ስለባቄላ፣ጤፍና ሌሎች የሰብል አይነቶች አያውቁም፤ ከጅግጅጋ ወደ ዩኒቨርስቲ ሲገቡ ነው የእነዚህን ሰብሎች ልማት የተመለከቱት ፤ ቢሾፍቱ። ‹‹የሆነ ነገር ተተክሎ ሲያድግ የማየት ፓሽን አለኝ፤ ከልጅነቴ አንስቶ ውስጤ ያለ ነገር ስለሆነ እንጂ ከትምህርትም ከአስተዳደግም ጋር የተያያዘ አይደለም ሲሉ ያብራራሉ።

በከተማ ግብርናው ተከታዮችን ማፍራት ችለዋል። በዚህም በእጅጉ ተደስተዋል፤ ተከታይ ማፍራታቸውን በስራው ስኬታማ ለመሆናቸው ሌላ ማረጋገጫ አርገውም ይወስዱታል። የአካባቢው ነዋሪዎች እሳቸውን ተከትለው የጓሮ አትክልት ማልማት ጀምረው ተጠቃሚ እየሆኑ ናቸው። እሳቸውም እነሱን ያሰልጥናሉ፤ ይከታተላሉ/ ኮች ያደርጋሉ/።

በአቅራቢያችን አንዲት አካል ጉዳተኛ በእኔ ኮቺንግ አትክልት ማምረት ጀምራ በአሁኑ ወቅት ከራሷም አልፋ ለሰዎች እየሰጠች ነው ሲሉ የሚጠቅሱት ዶክተር ጋሻው፣ ውሃ ልማት በሚባለው በሚኖሩበት አካባቢ የሴቶች እና የወጣቶች አደረጃጀቶች በክፍለ ከተማው ያለውን ሰፊ ክፍት ቦታ ተደራጅተው በማልማት አትክልት በብዛት እያመረቱ ናቸው። የእናቶች የልማት ቦታና ምርቶች በማህበራዊ ሚዲያዎች ፓስት እየተደረጉ መሆናቸውን ዶክተር ጋሻው ይገልጻሉ። በተለይ ቆስጣ ደስ የሚል ነገር አለው፤ ምርቱን ይዞ ቤት ሲኬድ በጣም ያረካል፤ ይህም በዚህ በተወደደ ኑሮ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ያሳርፋል ይላሉ።

እሳቸው መናኸሪያ አካባቢ ካለ ምግብ ቤት ጋር በፈጠሩት ትስስር አምራቾቹ አንድ ጊዜ ከአምስት ሺ ብር በላይ ሌላ ጊዜ ከስድስት ሺ በላይ ብር አግኝተዋል። በተለይ ሰላጣ በደንብ ሸጠዋል፤ ባለሆቴሏ በተለይ ሴቶችን ማበረታታት የምትፈልግ በመሆኗ በቀጣይም ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

ልጆች ላይ ሰርተዋል፤ ሆነ ብለው ሰብስበው ግን አይደለም፤ እኔን ሲያገኙ ዶክተር ስለሚሉኝና ውሃ እንዲያጠጡ እድሉን ስለምሰጧቸው ይደሰታሉ፤ የቀለም ጣሳ በሚገባ በስተው አዘጋጅተው ይሰጧቸዋል፤ እነሱም የተከሉትን አምጥተው ያሳዩዋቸዋል። ይሄ ለእሳቸው ትልቅ እርካታ ሰጥቷቸዋል። በእዚህ ሁሉ በጣም ተሳክቶልኛል።

በሰዎች በእናቶች አእምሮ አድርያለሁ፤ በዚህ በኩል ብዙ ሰዎች ወደ መዳህኒአለም ቤተክርስቲያን ይሄዳሉ፤ የእነሱን የየቀኑ ምረቃ ደግሞ ልዩ ነው ፤ መልካም ምኞታቸውን ሁሌም እንደገለጹልኝ ናቸው። እኔን እንደ ማመሳከሪያ /ሪፈረንስ/ ይመለከቱኛል ይላሉ።

የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ፣ የፌዴራል መንግስት ሃላፊዎችን ጨምሮ የተለያዩ ሰዎች የአትክልት ስፍራቸውን በተደጋጋሚ መጎብኘታቸውን ይናገራሉ ። በከተማና መሰረተ ልማት ሃላፊዎች በፓርላማ አባላት ጭምር ስራቸው ተጎብኝቷል። ሰዎች ስራቸውን ሊጎበኙ ወደ ግቢያቸው ሲመጡ ደስተኛ ሆነው ያስተናግዳሉ።

ምቹ ሁኔታ ባገኝ በቀጣይም ስራውን ባሰፋ እወዳለሁ የሚሉት ዶክተር ጋሻው፣ በዚህ ስራ በምኖርበት ቀበሌ፤ ክፍለ ከተማና ከተማዋ ላይ ያስገኘነው ጥሩ ውጤት አለ ሲሉ ገልጸው፣ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለጉብኝት የሚመጡ ሁሉ ይህን ለማስፋት ምን ሀሳብ አለዎት የሚል ጥያቄ እንዳቀረቡላቸውም ይናገራሉ። ምቹ ሁኔታ ከተፈጠረ ለማስፋት ደስተኛ መሆናቸውን እንደነገሯቸው ይጠቅሳሉ።

የቤተሰብና የስራ ባልደረቦቻቸው ድጋፍ አላቸው። ባለቤታቸው በክልሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶች በተፈጥሮ ሀብት ላይ ይሰራሉ። የግብርና ግንዛቤው ስላላቸው በዲዛይንና በመሳሰሉት ለዶክተር ጋሻው ድጋፍ ያደርጉላቸዋል። ከእሳቸው ሙያ ውጪ በሆኑት ደግሞ በዲዛይን የሚያግዝ የስራ ባልደረባ አላቸው፤ ከተባይና ከበሽታ ጋር ያሉትን ችግሮች በመፍታት በኩል የማያወቋቸውን የተባይ መከላከያ ባለሙያዎችን ያማክራሉ።

ሀዋሳ ከመጣሁ በሁለት አመት ውስጥ ለከተማዋ የበኩሌን ብዙ አስተዋጽኦ በፍላጎቴ አድርጌያለሁ የሚሉት ዶክተር ጋሻው፣ በእዚህም ሰርተፍኬቶች እና የተለያዩ ሽልማቶች አግኝተዋል፤ የሚኖሩበት ክፍለ ከተማ በከተማ ግብርናው አንደኛ ወጥቶ ሰሞኑን መኪና ተሸልሟል። ለእሳቸው ደግሞ የምስክር ወረቅትና የአራት ሺ ብር ሽልማት ተበርክቶላቸዋል ። ከሳምንት በፊትም በክፍለ ከተማ ደረጃ ዋንጫና ሰርተፍኬት ተሰጥቷቸዋል። ሁሉም የበለጠ እንድሰራ የሚያበረታቱ ሆነው አግኝቼያቸዋለሁ ይላሉ።

እኔ የፓለቲካ ሰው አይደለሁም የሚሉት ዶክተር ጋሻው፣ የከተማ ግብርናው ዋና አቀንቃኝ ግን ነኝ ሲሉ አጽንኦት ሰጥተው ይናገራሉ። ለእዚህ ተሰልፈው እስከ መጨረሻው ለመስራት ዝግጁም ናቸው።

የከተማ ግብርና ስራውን የሚያካሂዱት በፓለቲካ ግፊት እንዳልሆነም ይገልጻሉ። በኛ ደረጃ የተማሩ ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ጭምር እንዲህ አይነቱን ነገር ከፓለቲካ ጋር ያይዙታል፤ የግርግር የፓሮፓጋንዳ ስራ አርገው ይመለከቱታል ሲሉ ዶክተር ጋሻው ጠቅሰው፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የከተማ ግብርና ስራም የሚያሾፉ አንዳንድ የፌስ ቡክ ቀበኞች እንዳሉም ይጠቅሳሉ።

ይሄ በምንም አይነት መልኩ የፓለቲካ ስራ አይደለም፤ አሁን በየቦታው ሰዎች በክፍት ቦታዎች፣ በተለያዩ ቁሳቁስ አትክልት እያመረቱ ናቸው። እነዚህን ምርቶች ፍለጋ ወደ ገበያ አይሄዱም፤ ንጹህ ምርት ያገኛሉ፤ ልማቱ ለምግብ ዋስትና ፋይዳ አለው፤ ግብርናው በእርግጠኝነት የሰዎችን ሕይወት ይቀይራል፤ ገቢን ይጨምራል፤ እናቶች እየተጠቀሙ ናቸው ሲሉ ስለከተማ ግብርናው ፋይዳና ስለደረሰበት ደረጃ ያብራራሉ።

እኛ ባለሙያዎችና አመራሮች የምንሰራውን ማህበረሰቡ ይወስዳል ። ህዝቡ ጥሩ ነገር ካሳየነው ለሀገር ይሰለፋል የሚሉት ዶክተር ጋሻው፣ ህዝቡ ለመከላከያ ሲባል እንዴት ሆኖ እንደተነሳ ታይቷል። በመሀል ውዥንብር የሚፈጥሩ ቢኖሩም ለሀገሩ ሉአላዊነት የሚሰራም አለ። የተነሳው ለልማት ከሆነ የአመራሩ ቁርጠኝነት ወሳኝ ነው። ብዙ አስቸጋሪ ነገር አለ ፤ በምንችለው ግን ያንን ለማሸነፍ ጥረት ማድረግ አለብን ሲሉ ያስገነዝባሉ።

ማህበረሰቡ ለምሁራን የሚሰጠው ትልቅ ቦታ አለ። በእኔ በኩል እድሜዬና ዶክተርነት አለ፤ ይሄ አሁን ብዙ አስፈላጊ ባይሆንም አሁን በከተማ ግብርናው እየሰራሁ ያለሁት ስራ በማህበረሰቡ ዘንድ ያድራል፤ ሰዎች በእዚህ ነገር በጣም ይሳባሉ፤ እኔ ሰዎች አፍርቻለሁ፤ ምርቱን መስጠቱ ብቻ ሳይሆን፣ ይህን ነገር እንደ ልማድ /ሆቢ/ እንዲይዙት አምርቶ መብላት፤ ንጹህ ነገር ማግኘትና ኑሮን መደጎም እንደሚቻል ማሳየት የቻልኩ ይመስለኛል ሲሉ ያብራራሉ።

ዶክተር ጋሻው ኢትዮጵያዊነት ላይም ጠንካራ አመለካከት አላቸው። ‹‹ለአባቴ እግዚአብሄር ይሰጠውና ኢትዮጵያዊነት ውስጤ አለ። ›› ሲሉ ይናገራሉ። በእዚህ በጣም ይኮራሉ፤ በወታደር ልጅ ዲስፕሊን ነው ያደጉት ይላሉ። አባታቸው በኦጋዴን፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ብዙ ተሰልፈው አገልግለዋል፤ አሁን በጡረታ ላይ ናቸው። የእሱን እድሜ በእኔ መገመት ይቻላል የሚሉት ዶክተር ጋሻው፣ ቤታቸው ውስጥ ከፍተኛ የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዳለም ነው የሚናገሩት፤ ኢትዮጵያዊ ነኝ ካልኩኝ ለኢትዮጵያ እኔስ ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ ብዬ መስራት አለብኝ? ሲሉ ራሳቸውን ይጠይቃሉ ።

ብቻውን ዶክተር ነኝ ብትል ብዙም ዋጋ የለውም፤ ለራስህ ፐብሊሽ ልታደርግ ትችላለህ፡ ከዚያ ያለፈ ለማህበረሰቡ ምን አደረግሁ ማለት ያስፈልጋል፤ ይህን ሁሉ አትክልትና የአረንጓዴ ስፍራ ውሃ ስታጠጣ ሰዎች ላይ የማሳደረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም የሚሉት ዶክተር ጋሻው፣ ይህም ለእኔ ስኬት ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

ራሴን ከፍከፍ ማድረግ አልፈልግም፤ ይሄ የወረደ ስራ አይደለም፤ በሰራሁት ወደ ማህበረሰቡ ውስጥ መግባቴ በጣም ያስደስተኛል ሲሉ ገልጸው፣ ሁሉም ይህን ማድረግ እንደሚችል መክረዋል፤ በከንቱ ጣት መቀሰር እንደማይጠቅም፣ የጠፋ ነገር ካለ ጠጋ ብሎ መምከር እንደሚገባና ሀገር በፌስ ቡክ ዘመቻ እንደማይገነባም ያስገነዝባሉ።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ባለብዙ አንድምታው የመኖሪያ ቤቶች እድሳትና ግንባታ

መላኩ ኤሮሴ



በአቧሬ አካባቢ ለአቅመ ደካሞችና በአነስተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ የአካባቢው ነዋሪዎች የተገነባውና በርከታ መኖሪያ ቤቶችን ያካተተው ህንጻ

የመኖሪያ ቤት ችግር በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ትልቁ ፈተና መሆኑን ቀጥሏል። በርካታ የከተማዋ ነዋሪ በክራይ ቤት እና በደባልነት ነው የሚኖረው። በከተማው ባለው የኪራይ ቤት እጥረት ምክንያት ተከራይ የሚፈልገውን አይነት የኪራይ ቤት ማግኘት ይከብዳል። በዚህ ላይ የኪራዩ ዋጋ አይቀመስም።

በዚህ ላይ ያረጀውን መኖሪያ ቤት ማደስም ሆነ አዲስ ቤት መገንባት ባለመቻላቸው የተነሳ ሊወድቁ በተቃረቡ እና ለኑሮ በማይመቹ ቤቶች የሚኖሩ የከተማዋ ነዋሪዎችም በርካታ ናቸው።

የከተማዋን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት መንግስት የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም መፍትሄ ለመስጠት ርብርብ ሲያደርግ ቆይቷል። በአሁኑ ወቅትም የተለያዩ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን አስቀምጦ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ሆኖም የከተማው የቤት ችግር የነዋሪዎችን አቅም መፈታተኑን ተያይዞታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ደግሞ ከከተማዋ መኖሪያ ቤቶች ጥቂት የማይባሉት በእርጅና በመሳሰለው ሳቢያ የሚያኖሩ አይነት አይደሉም፤ ነዋሪዎቹ በእቅመ ደካማነትና በመሳሰሉት ሳቢያ ቤቶቹን መልሶ መገንባት የሚችሉ ባለመኖናቸው የተነሳ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለመኖር ተገደው ቆይተዋል።

መንግስት ይህን ችግር ህብረተሰቡን በማስተባበር ለመፍታት በቤቶች እድሳት ላይ በትኩረት እየሰራ ይገኛል። በእዚህ በኩል እያደረገ ካለው ጥረት መካከል በህብረተሰብ ተሳትፎ እና በበጎ ፈቃድ አገልግሎት እየተገነቡ እና እየታደሱ ያሉ የአቅመ ደካማ ቤቶች ይጠቀሳሉ። በበጎ ፈቃድ እና በህብረተሰብ ተሳትፎ ቤቶችን ማደስ እና አዳዲስ ቤቶችን ገንብቶ አቅም ለሌላቸው ማቅረብ በተለይም ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ እየተለመደ መጥቷል። በዚህም በተለይም የአቅም ደካሞች ህይወት እየተቀየረ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ዳዊት ከበደ እንደተናገሩት፤ በተጠናቀቀው 2014 አም የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት እና ግንባታ ስራዎች ተከናውነዋል።

በ2014 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ስምንት ሺህ አካባቢ ቤቶች ባሉበት በከፊል እና ሙሉ በሙሉ ታድሰው ለህብረተሰቡ ተላልፈዋል። ከዚህ ውስጥ 3ሺህ 645 ቤቶች ደግሞ ከግንቦት እስከ መስከረም ባሉት የክረምት ወራት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የተገነቡና የታደሱ ናቸው።

በተለይም ከግንቦት እስከ መስከረም ወር ባሉት አምስት ወራት አመርቂ ስራዎች መሰራታቸውን አቶ ዳዊት ይጠቅሳሉ። ''በጎነት ለዘላቂ አብሮነት'' በሚል መርሃ ግብር ከግንቦት አንድ 2014 ዓ.ም እስከ መስከረም 2015 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ ለአምስት ወራት የዘለቁ ሰባት መርሃ ግብሮች ተቀርጸው ርብርብ መደረጉን ጠቅሰው፣ ከነዚህ መርሃ ግብሮች አንደኛው የሰብዓዊና ማህበራዊ አገልግሎት መርሃ ግብር መሆኑን ይጠቁማሉ። በሰብዓዊና ማህበራዊ መርሃ ግብር ውስጥ ከሚካተቱ ተግባራት መካከል የአቅመ ደካማ እና የሀገር ባለውለታ የሆኑ ዜጎች የቤት እድሳት አንዱ እንደነበር ነው ያነሱት።

በነዚህ አምስት ወራት ውስጥ 3 ሺህ 400 ቤቶች ለማደስ ታቅዶ እንደነበር የጠቆሙት አቶ ዳዊት፤ ባለሃብቶችን ጨምሮ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተሳተፉበት የቤት እድሳት ከእቅድ በላይ ማሳካት መቻሉን ጠቁመዋል። 3 ሺህ 645 አዳዲስ ቤቶችን መገንባት እና ማደስ ተችሏል። ከነዚህ ውስጥ 1 ሺህ 300 የሚሆኑት ሙሉ በሙሉ ፈርሰው እንደገና የተገነቡ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ባሉበት ቦታ ግድግዳቸው ወይም ጣሪያቸው ፈርሶ የታደሰ መሆኑን ተናግረዋል።

እነዚህ ቤቶች ጳጉሜ 1 በጎ ፈቃድ ቀን ተብሎ በተሰየመው መሰረት ለነዋሪዎቹ ተላልፈዋል። በአማካይ በነዚህ ቤቶች ውስጥ እስከ አምስት ሰው የሚኖርባቸው መሆናቸውን አቶ ዳዊት ጠቅሰው፣ የታደሱት እና እድሳት የተደረገላቸው 3 ሺህ 645 ቤቶች ውስጥ 18 ሺህ 222 የሚጠጉ ነዋሪዎች የሚኖሩባቸው መሆናቸውን ነው ያብራሩት።

እንደ አቶ ዳዊት ማብራሪያ፤ በህብረተሰብ ተሳትፎ እና በጎ ፈቃድ እድሳት ከተደረገላቸው እና እንደ አዲስ ከተገነቡ ቤቶች በተጨማሪም ዘጠና በስልሳ በተሰኘ ሰው ተኮር ፕሮጀክት በከተማ አስተዳደሩ አነሳሽነት 747 ቤቶችን በአዲስ መልክ በመገንባት ለነዋሪዎች ማስተላለፍ ተችሏል። ይህም በርካታ ማህበራዊ ችግሮችን መቅረፍ ያስቻለ ነው።

እድሳትና ግንባታው ቅድሚያ ተሰጥቷቸው መታደስ ያለባቸው እና እንደ አዲስ መገንባት ያለባቸው ቤቶችን በመለየት ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ እንደሚከናወን የተናገሩት አቶ ዳዊት፤ በልየታ ሂደት ውስጥ የተለያዩ አካላት የድርሻቸውን እንደሚወጡም ጠቁመዋል። ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን ግንባታ እና እድሳት የሚያስፈልጋቸው ቤቶች ልየታ የሚያካሂድ ኮሚቴ በወረዳዎች እንዳለም ተናግረው፣ የድሃ ድሃ እነማን ናቸው የሚለው በጥንቃቄ እንደሚለይም ነው ያመለከቱት።

መገንባት ወይም መታደስ ያለባቸው የነማን ቤቶች ናቸው፤ በአካባቢው ከሚገኙ የግለሰብ ቤቶች እና የቀበሌ ቤቶች ውስጥ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቤቶች የእነማን ናቸው በሚል ቤቶች መስፈርት ወጥቶላቸው እንደሚታደሱና እንደሚገነቡ ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ አቅማ ደካማ የሆኑ፣ አጋዥ የሌላቸው፣ መስራት የማይችሉ በወረዳ ደረጃ ይለያል። በነዚህ ክፍለ ከተሞች እነዚህ እነዚህ ቤቶች ቢታደሱ ተገቢ ነው የሚለውን መረጃ ለሚፈልጉ አካላት ይተላለፋል። ግለሰቦች ባለሃብቶች፣ ተቋማት እና ድርጅቶች ማደስም ሆነ የግንባታ ስራዎችን እንዲሰሩ ይደረጋል።

አንዳንዶቹ ነዋሪዎች ለእድሳት ወይም ለመልሶ ግንባታ በሚወጡበት ወቅት ተመልሰው ወደ ቦታው የሚገቡም አይመስላቸውም ያሉት አቶ ዳዊት፣ ይህም ከዚህ ቀደም በመሃል ከተማ የሚኖሩት በመልሶ ግንባታ ምክንያት ወደ ዳር እየተወሰዱ ስለነበር የተከሰተ መሆኑን ያስታውሳሉ። አሁንም ተመሳሳይ ነገር ይፈጠራል በሚል ስጋት ከቤታቸው ለመውጣት ፍርሃት የነበራቸው እንደነበሩም ይገልጻሉ።

እንደ አቶ ዳዊት ማብራሪያ፤ በህብረተሰብ ተሳትፎ እና በበጎ ፈቃድ እየተሰሩ ባሉ ስራዎች የከተማዋን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ማቃለል እየተቻለ ነው። በርካቶችን ከአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ማላቀቅ ተችሏል። ይህም እውን ሊሆን የቻለው በህብረተሰቡ ተሳትፎ ነው። ባለሃብቱ እና ሌላው በጎ ፈቃደኛ ድጋፉ በትክክል ለሚያስፈልጋቸው አካላት እየደረሰ መሆኑን በአይናቸው በማየታቸው በርካቶች ተመሳሳይ የበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ የመሳተፍ ፍላጎት እያሳዩ ናቸው።

አምራች ያልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን መርዳት ያስፈልጋል የሚለው እሳቤ ተቀባይነት እየጨመረ ነው ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ አምራች ያልሆነውን የህብረተሰብ ክፍል የሚደግፉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሆኑን ይጠቅሳሉ። ቤት ገንብተው እንዲሁም አድሰው ከመስጠት ባሻገር አንዳንዶቹ ሌሎች ወጪዎችንም እየሸፈኑ መሆናቸውንም አመልክተው፣ ሙሉ የቤት ውስጥ እቃ አሟልተው የሚሰጡም መኖራቸውን ነው የጠቆሙት።

እንደ ምክትል ኮሚሽነሩ ማብራሪያ፤ የእነዚህ ቤቶች መገንባት እና እድሳት አንድምታው ብዙ ነው። ባለሃብቱን ጨምሮ ሌሎች ማገዝ የሚችሉ አካላት በበጎ አድራጎት ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ አስችሏል። በርካቶች ድጋፍ የሚፈልጉ ዜጎችን መደገፍ ቢፈልጉም የተደራጀ እና ተቋማዊ አሰራር ባለመኖሩ ለመደገፍ ሲቸገሩ ነበር። ይህ ኮሚሽን ተቋቁሞ የማስተባበር ስራ መጀመሩ መደገፍ የሚፈልጉት ድጋፋቸውን በተደራጀ መልኩ እንዲያቀርቡ አስችሏቸዋል።

አብዛኞቹ የቤት እድሳት የተደረገላቸው እና አዲስ ቤት የተገነባላቸው ነዋሪዎች በአንድ ወቅት ለኢትዮጵያ ትልቅ የዋሉ እና ራሳቸውንና ሀገራቸውን ያገለገሉ፣ በአንድም በሌላም መንገድ ይህችን ሀገር ለዚህ ትውልድ ያስረከቡ ናቸው። እድሜያቸው በመግፋቱና ረጂ በማጣታቸው ለችግር የተጋለጡ ናቸው። እድሳትና ግንባታው እነዚህን ሰዎች ከነበሩበት ሁኔታ መታደግና አለኝታነትን መግለጽ የተቻለበት ነው።

ትናንት ለሀገራቸው የዋሉ ሰዎች በዚህ መልኩ ድጋፍ ማግኘታቸው ዛሬም ለሀገራቸው ጠንክረው ለሚሰሩት መልካም መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው ያሉት አቶ ዳዊት፣ ውለታቸውን ሀገራቸው እንደማትረሳቸው እና በከባድ ሁኔታ ውስጥ ቢወድቁ እንኳ አስተዋሽ እንዳላቸው እንዲያስቡ የሚያደርግ ነው ይላሉ።

በተለይም ውድ ህይወታቸውንና የተለያዩ አካላቸውን ለሀገራቸው ሉአላዊነት ሲዋደቁ ላጡት ጀግኖች እና የጀግኖች ቤተሰቦች የቤት ግንባታ እና እድሳት መከናወኑ አገሪቷም ባላት ሃብት ለነዚህ አካላት ቅድሚያ በመስጠት የምትደግፈውና የምታበረታታው መሆኑን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፤ ኢትዮጵያዊያን ከበፊትም ጀምሮ የመረዳዳት እና የመተጋገዝ ባህል ያላቸው ህዝቦች ናቸው። ለእዚህም እድር እና እቁብ መሰል መረዳጃዎች ማሳያ ናቸው። ደቦን የመሳሰሉ በጋራ የመስራት ባህልም ኢትዮጵያዊያን የቆየ የመረዳዳት ባህል ባለቤቶች መሆናቸውን ያመለክታሉ። አሁን በአዲስ አበባ እና በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስ እና በተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎች እየታየ ያለው መልካም ተግባር የመረዳዳት ባህልን ያነቃቃ ነው። የመተጋገዝ እና የመረዳዳት ባህል እየጨመረ መምጣቱንም አመላካች ነው።

የቤት ግንባታና እድሳቱ አቅም አልባ ዜጎች ዘንድ እፎይታን የፈጠረ ነው። እነዚህ ነዋሪዎች ቤታቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ታድሶላቸው ተመልሰው የሚገቡ አይመስላቸውም ነበር። መንግስት በበጎ ፈቃድ የቤት ግንባታና እድሳት ሰበብ ከመሃል ከተማ ሊያስወጣቸው በማሰብ የሚሰራ ደባ የሚመስላቸውም ነበሩ ሲሉ ያብራሩት አቶ ዳዊት፣ ከዚህም የተነሳ የቤቶች እድሳት እና ወይም ግንባታ ተጠናቆ ተመልሰው ወደ ቤታቸው ሲገቡ ደስታቸው ከፍ ያለ እንደነበር ተናግረዋል።

እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፤ መሰል ጥርጣሬ ሲፈጠርባቸው የነበረው ከለውጡ በፊት በነበሩ ዓመታት በመሃል ከተማ ለዘመናት ይኖሩ ከነበሩበት ቀዬያቸው ለልማት የተነሱ በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎች ወደ ዳር ሄደው እንዲሰፍሩ በመደረጉ ነው። በዚህም ምክንያት የብዙዎች ማህበራዊ ትስስር ተናግቷል። ከለውጡ በፊት የነበረው አካሄድ አሁንም ሊቀጥል ይችላል የሚል ስጋት በብዙዎች ዘንድ ነበር። ቤቶቹ ተገንብቶ አልቀው ከገቡ በኋላ ግን ጥርጣሬያቸው ትክክል እንዳልነበር መረዳት ችለዋል።

አዲስ አበባ ጉራማይሌ ነች። ውብ ሰወፈሮች እና ቦታዎች አሏት። በዚያው ልክ ደግሞ ለመኖር አስቸጋሪ የሆኑ ሊፈርሱ የተቃረቡ እና በሸራ የተወጠሩ ቤቶች የሚገኙባቸው አካባቢዎችም አሏት ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ አብዛኛው የቤቶች ግንባታና እድሳት እየተካሄደባቸው ያሉ አካባቢዎች የአጠቃላይ የመንደሩን ዉበት በመጨመር ገጽታው እየተቀየረ እንዲመጣ እያደረጉ መሆናቸውንም ነው የገለጹት።

እድሳትና ግንባታው ከተማን የማስዋብ እና የመቀየር ሚናም አለው ይላሉ። ሊወድቁ የተቃረቡ እና በሸራ የተሰሩ ቤቶች በህንጻ ሲተኩ በአካባቢው ላይ የሚኖረው ውበት ግልጽ ነው። ይህን በበጎ ፈቃድ እየተገነቡ ያሉ ቤቶች ለከተማዋ ዉበት የራሳቸውን ሚና እየተጨወቱ ስለመሆኑ አመላካች ነው ይላሉ አቶ ዳዊት።

እድሳት እየተደረገላቸው እና እንደ አዲስ እየተገነቡ ባሉ ቤቶች ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ቀደም ባሉ ጊዜያት ይኖሩ የነበረው አኗኗር እና ቤታቸው ከታደሰ እና እንደ አዲስ ከተገነባ በኋላ ያለው የአኗኗር ዘይቤያቸውም እየተቀየረ መሆኑን አቶ ዳዊት ይገልጻሉ። ሁኔታው ማገዶ ከመጠቀም ሌሎች ታዳሽ የሀይል ምንጮችን እንዲጠቀሙ እያደረጋቸው ነው፤፤ ይህም የደን መጨፍጨፍን በመቀነስ እየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ለሚደረገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነው ሲሉ ያብራራሉ።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የአንድ ወቅት ብቻ አገልግሎት አይደለም የሚሉት አቶ ዳዊት፤ በበጋ ወቅትም የቤት እድሳት እና ግንባታን ጨምሮ የተለያዩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለማከናወን ታቅዷል ሲሉ ይጠቁማሉ። የክረምት በጎ ፈቃድ ማጠቃለያ መስከረም 30 እንደሚጠቃለል ጠቅሰው፣ለእዚህም ፕሮግራም ሊደረግ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አቶ ዳዊት ይጠቁማሉ። የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራ ከተጠቃለለ በኋላ የበጋ እንደሚጀመርም አመልክተዋል። በዚህም የቤቶች እድሳት እና ግንባታን ጨምሮ በርካታ የበጎ አድራጎት ስራዎችን ለማከናወን እቅድ መያዙን ነው የተናገሩት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትግራይን ሕዝብ ዋጋ እያስከፈለ ያለው የአሸባሪው ትህነግ ጦረኛ ድርጊት ነው!

አሸባሪው ትህነግ በጦርነት ውስጥ ተወልዶ፣ በጦርነት ውስጥ አድጎና አርጅቶ፣በጦርነት ውስጥ የሚኖርና ከስህተቱ የማይማር አሸባሪ ድርጅት ነው።ይህንን የቀደመ ታሪኩንም ሆነ አሁንም በትግራይ ህጻናት፣ ታዳጊዎች፣ ወጣቶች እና አዛውንቶች ደም እየጻፈ ያለው ጥቁር ታሪክ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

በቀደሙት ዘመናት "በነጻነትና በዲሞክራሲ" ስም ለ17 ዓመታት ባካሄደው የትጥቅ ትግል በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ወጣቶችን ሕይወት ገብሯል፤ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩትን የአካል ጉዳተኞች አድርጓል፤ እንደ ሀገርም ፣ ሀገርና ሕዝብን ብዙ ዋጋ አስከፍሏል። ይሁንና በአመራሩ የግል ፍላጎት የተፈለገውን ግብ ሳያሳካ ቀርቷል።

በትጥቅ ትግሉ ወቅት ሳይቀር የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸውን ታጋዮች ከማሰር እና ከማሳደድ ጀምሮ የመግደልና በሴራ የማስገደል ታሪክ ያለው፣ በየትኛውም ሁኔታ ለውይይትና ለድርድር ብሎም ሰጥቶ ለመቀበል መርህ የማይገዛና ለዚህ የሚሆን ማንነት የሌለው ነው።

የሁሌም መፈክሩ ኃይልና ከኃይል የሚመነጭ እብሪት፣ ውዥንብርና ከውዥንብር የሚመነጭ ግራ ማጋባት ነው። ለሰላምና ሰላም ለሚፈጥረው የማኅበራዊ መረጋጋት ጸር የሆነ፤ ይህንንም ስጋት አድርጎ የሚመለከት ነው።

በህዝቦች መስዋእትነት ወደ ስልጣን ከመጣ ማግስት ጀምሮም የሀገሪቱ ብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች በሰላም ተቻችለውና ተስማምተው እንዳይኖሩ ፣ በመካከላቸው ጥርጣሬና አለመተማመን የሚፈጥር የውሸት ትርክት ተግባራዊ አድርጎ ዜጎችን ለመነጣጠል ዕድሜ ልኩን ሰርቷል።

የሕዝቦችን የቆየ የአብሮ የመኖር እሴቶችን የሚንዱ የጥላቻ ትርክቶችን በመፍጠር እና በተደራጀ መንገድ በማሰራጨት የሀገሪቱ ህዝቦች ማኅበራዊ ሕይወት ለዘለቄታው እንዳይረጋጋ ከማድረግ አንስቶ፤ ግጭቶችን በመፍጠር ዜጎች ለሞትና ለስደት እንዲዳረጉ በስፋት ሰርቷል።

የተለየ የፖለቲካ አስተሳሰብ ያላቸውን ዜጎችን በበረሀ በጀመረው መንገድ በማሰር፣ በማሰቃየት፣ በመግደልና በማሳደድ ብዙዎች "በነጻነትና በዲሞክራሲ" ስም ዋጋ የከፈሉለት ትግል ትርጉም አልባ ፣ በትግሉ የተሰዉ ሰማዕታት ደም ከንቱ እንዲሆን አድርጓል።

ከውልደቱ ጀምሮ በተጠናወተው በዚሁ በሽታው በሕዝባዊ እምቢታና በኢህአዴግ ውስጥ በተደረገ ውስጣዊ ትግል ከማዕከል ከተገፋ ማግስት ጀምሮ በኃይል ወደ ስልጣን እመለሳለሁ በሚል ቀቢጸ ተስፋ በሀገር ላይ ጦርነት በማወጅ የእብደት ጥጉን አሳይቷል።

መንግስት በሚመቹም በማይመቹም ሁኔታዎች የሰጣቸውን የሰላም አማራጮች እንደ ሽንፈት በመቁጠር ለሦስት ጊዜ በሀገር ላይ ጦርነት በማወጅ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይን ህጻናት፣ ታዳጊዎች፣ ወጣቶች እና አዛውንቶች ለእልቂት ዳርጓል፤ እየዳረገም ነው።

ይህ የጥፋት ቡድን ለሦስተኛ ጊዜ በከፈተው ጦርነት ያሰበውና ያለመው ሳይሳካለት ሲቀር አንድም ጦርነቱን የጀመረው መንግስት ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ባለው ጊዜ አልቀበል ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል የነበረበትን የሰላም አማራጭ ተቀብዬአለሁ በሚል እየጮኸ ነው።

ይህ ዓላማውን በኃይል ለመፈጸም የሄደበት መንገድ መምከኑን ተከትሎ የጀመረው ዓለም አቀፉን ህብረተሰብ የማደናገር ጩኸትም ሆነ የሰላም ፈላጊነት ዜማ የቡድኑን የትናንት ሆነ አሁናዊ ሁኔታ ለሚረዳ ብዙም የሚያስገርም አይደለም።

ቡድኑ በራሱ የያዘውን እና ከጋላቢዎቹ የተቀበላቸውን ተልዕኮዎች በኃይል ለማስፈጸም የሚሄድባቸው መንገዶች ሲመክኑበት የራሱን ህልውና ለመታደግ የተለያዩ ትርክቶችን በመፍጠር በተገዥ አክቲቪስቶች፣ ሎቢስቶችና በፕሮፓጋንዳ ማሽነሪዎች በኩል የመጮኹ እውነታ የተለመደና አሰልችም ጭምር ሆኗል።

ለሁለት አስርት ዓመታት የትግራይን ሕዝብ በቀበሮ ጉድጓድ ሆኖ ሲጠብቀው በነበረው የሰሜን እዝ ላይ "መብረቃዊ ጥቃት" በሚል ከኋላ በማጥቃት አሰቃቂ ግፍ በፈጸመ ማግስት፤ያሰበው ያቀደው ሳይሳካ ሲቀር፤ በትግራይ ህዝብ ላይ የዘር ማጥፋት እየተካሄደ ነው በሚል የአዞ እንባ ሲያነባ ታይቷል።

ለሁለተኛ ጊዜም ሂሳብ አወራርዳለሁ በሚል በአማራና በአፋር ክልል ሰፊ ወረራዎችን አድርጎ እስከ መሃል ሀገር የዘለቀበት ክስተት ሲቀለበስም በተመሳሳይ መልኩ፤የድረሱልን ጩኸቱን በተለያዩ የፈጠራ ትርክቶች አስደግፎ አደባባዮችን መሙላቱ ይታወሳል።

ዛሬም ቢሆን ለሦስተኛ ጊዜ የለኮሰውን ጦርነት መንግስት በጠንካራ መከላከል ሲያመክንበት፤አዳዲስ ትርክቶችን በመፍጠር ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብን ለማደናገር በስፋት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በዚህ ሂደት ሁሉ ግን እያለቀ ያለው የትግራይ ህጻናት፣ ታዳጊዎች፣ ወጣቶች እና አዛውንቶች ለሽብር ቡድኑ ምኑም አይደሉም።

ከዚህ ይልቅ ይህን ያህል ገደልኩና ማረኩ በሚሉ ልፈፋዎች የተቀረውን የትግራይ ወጣት ለእልቂት ለመዳረግ የፖለቲካም ሆነ የወታደራዊ አመራሮቹ ባልተለመደ ሁኔታ በየቀኑ እርስ በርሱ በሚጋጭ መግለጫ ሲደሰኩሩ መስማት እየተለመደ ነው።

ይህ የአሸባሪው ትህነግ በጦርነት ውስጥ ተወልዶ ፣ በጦርነት ውስጥ አድጎና አርጅቶ ፣በጦርነት ውስጥ የመገኘቱ እውነታ መላው ሕዝባችንን ብዙ ዋጋ እያስከፈለ ቢሆንም ፤ቡድኑ የትግራይን ሕዝብ ላለፉት አምስት አስርት ዓመታት ያስከፈለውና እያስከፈለ ያለው ዋጋ ግን ከሁሉም የከፋ ነው።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# በአንድ ራስ ሦስት ምላስ

**ዳግም ከበደ**

የጠብ ድግስ በመጥመቅ የሚታወቀው ሽብርተኛው ትህነግ በኢትዮጵያውያን ላይ የሉአላዊ ስጋት ከደቀነ ከሁለት ዓመት በላይ ሊሆነው ነው። ከታሪካዊ የአገራችን ጠላቶች ጋር በመመሳጠርና ቡድናዊ ፍላጎቱን በማስላት ብቻ በኢትዮጵያውያን ላይ ክህደት እየፈፀመ ይገኛል። ይህንን ተፈጥሯዊ የጭካኔ፣ የግፍ፣ የስግብግብነት ግብሩን ለማሳካት ሳር ቅጠሉን እየነጨ፤ ዳገት ቁልቁለቱን እየቧጠጠ ይገኛል።

እየሱስ ክርስቶስን ሦስት ጊዜ እንደከዳው ጴጥሮስ የትግራይ ሕዝብን አግቶ ኢትዮጵያውያንን እናቶች ያጎረሱትን እጅ ነክሶ ባለፉት ሁለት ዓመት ብቻ ተደጋጋሚ ወረራዎቹን አድርጓል። ለውጭ ጠላቶች ጫና አገራችን እንድትጋለጥ፤ የአገር ዳር ድንበር እንዲሳሳ ከማድረግ ባለፈ፤ ኢትዮጵያን የመበታተን ቅዠቱን እውን እንዲሆን እንቅልፍ አጥቶ እየሠራ ይገኛል።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግሥት የትግራይን ሕዝብ ጨምሮ መላው ኢትዮጵያውያን የሰላም አየር እንዲተነፍሱ፣ ሰቅዞ የያዛቸውን ድህነት በጠንካራ ክንዳቸው ታግለው እንዲያሸንፉ ካለው ፍላጎትና ኃላፊነት ጭምር የሽብርተኛውን ቡድን ተደጋጋሚ ትንኮሳ፣ ጭፍጨፋ እንዲሁም ከፍተኛ ወረራ ወደጎን በመተው ለሰላም እጁን በመዘርጋት የተናጠል ተኩስ አቁም ከማድረጉም በላይ በሆደ ሰፊነት ምንም ዓይነት ሕጋዊ ድጋፍ ከሌለው አገር አፍራሽ ቡድን ጋር «ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንደራደር» የሚል ጥሪ አቅርቦ ረጅም እርቀት ተጉዟል።

አሸባሪው ትህነግ ግን ከውልደቱ ጀምሮ የትግል አጋሮቹን በበረሃና በየጢሻው በግፍ እየረሸነ የመጣ አረመኔ ቡድን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ «ተቀምቻለሁ» ብሎ ያሰበውን መንበርና የዝርፊያ ሰንሰለት ዳግም በኢትዮጵያውያን ጫንቃ ላይ ለማስፈን ወረራን፣ የግፍ ጭፍጨፋንና ጠብ አጫሪ መንገድን መርጦ «በአንድ ራስ ሦስት ምላስን» የሚል አውሬያዊ ሕግ እየተከተለ ይገኛል።

ቡድኑ እንደ እስስት የሚቀያየር የሽብር ቡድን ነው። ይህን ለመረዳት የሰሞኑን ድርጊቶቹን ብቻ መቃኘት በቂ ነው። ላለፉት ወራት በኢትዮጵያ መንግሥት ይሁንታ የተደረገውን የተኩስ አቁም ስምምነት እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ የትግራይ ወጣቶችን፣ ሕፃናትንና አዛውንትን በአስገዳጅ ሁኔታ ጦርነት ውስጥ ለመማገድ መጠነ ሰፊ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል።

የአዞ እንባውንም በማፍሰስ እርዳታ እና የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ጥያቄዎችን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እያደረገ በኢትዮጵያ መንግሥት እና ሕዝቦች ላይ ጫና ለመፍጠር ከላይ እታች ሲል ሰንብቷል። በክልሉ ለሰብአዊ ተግባር ይቀርብ የነበረውን እርዳታና ነዳጅ በመዝረፍ እና በግፍ ከንፁሃን አፍ በመንጠቅ ለእኩይ አላማው ማስፈጸሚያ ለጀመረው ጦርነት እያዋለው ይገኛል። ለዚህ ደግሞ ሰሞኑን በተዋጊዎቹ ምሽጎች እየተገኙ ያሉት የእርዳታ አቅርቦቶቹን ማየት በቂ ነው።

ቡድኑ በአንድ በኩል በአገር ውስጥና በዓለምአቀፍ ደረጃ ባሰማራቸው ተከፋይ ሎቢስቶችና ፕሮፓጋንዲስቶች በኩል የቅጥፈት የበሬ ወለደ ወሬዎችን በስፋት በማሰራጨት የዓለምአቀፉን ኅብረተሰብ እያደናገረ በሌላ በኩል ከክልሉ በሚዋሰኑ ሕዝቦች ላይ ወረራ በማካሄድ ዝርፊያ እና የጅምላ ጭፍጨፋ ያካሂዳል።

የቡድኑ ወታደራዊ ሆነ ፖለቲካዊ አመራሮች በበኩላቸው የመንግሥትን ትዕግስትና ሆደ ሰፊነት እንደ ሽንፈት እየወሰዱ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ መፎከርና ማቅራራት ዋነኛ መገለጫውም ከሆነ ውሎ አድሯል። «ጦርነቱ አብቅቷል፣ እጅ ስጡ፤ ይሄን ሺ ሰራዊት ገደልን፤ማረክን » በሚሉ የቅዠት ቃሎች እራሳቸውን ሲያጽናኑም መስማት ተለምዷል።

መንግሥት ትዕግስቱ አልቆ እርምጃ መውሰድ ሲጀምር ደግሞ «ያዙኝ ልቀቁኝ» የሚለው ፉከራቸው ብዙም ሳይቆይ «ተገደልን፣ ተጨፈጨፍን፣ የትግራይ ሕዝብ ከበባ ውስጥ ነው፣ ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ጣልቃ ይግባ፣ የገላጋይ ያለ» የሚል ለቅሶና ዲስኩር በቅጥረኞቻቸው በኩል ያሰማሉ።

«ትህነግ ሦስት ምላስ ነው ያለው» አልን እንጂ የዚህ ሽብር ቡድን ምላስ እጅግ ብዙ ነው። ከሰሞኑ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሲናዘዝ የነበረውን በርካታ የተምታታ ጉዳይ ካስተዋልን እንኳን ብዙ አስቂኝ ነገሮችን እናገኛለን። አንዴ ጀግና አንዴ ደግሞ ቅልስልስ ይሆናል።

የሰሞኑን የቡድኑ መሪ «የአድኑኝ» ጥሪን ስናይ ለውጭ ኃይሎች ፈረስ ሆኖ እንደሚጋለብ በአደባባይ የሚያጋልጥና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ድጋፍ ካላገኘ አንድ እርምጃ እንደማይጓዝ በተጨባጭ ያመላከተ ነው። ይህ ሙከራው አልሳካ ሲልና እንደለመደው ጊዜ ለመግዣ «በአፍሪካ ኅብረት ማዕቀፍ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እደራደራለሁ» የሚል ዲስኩር አሰምቷል።

የትህነግ ተለዋዋጭ ባህሪ እና እስስታዊነት በዚህ የሚያበቃ አይደለም። «ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እደራደራለሁ» ብሎ ይፋ መግለጫ ባወጣ ማግስት የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የተዘናጋ ሲመስለው በሱዳን ድንበር በሁመራ አካባቢና በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ጦርነት በመክፈት አንድ ጊዜ በጦርነት፣ ሌላ ጊዜ በለቅሶ እንዲሁም በገላግሉኝ ተለዋዋጭ ባህሪው ኢትዮጵያውያንን ለማንበርከክና አገራችንን የማፈራረስ ህልሙን ለማሳካት እየተፍጨረጨረ ይገኛል።

ግማሽ ክፍለ ዘመን ለሚሆን ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትህነግን ያውቀዋል። ከዚያም አልፎ ለ27 ዓመታት በጭቆና መንበሩና አገዛዝ ሥርዓቱ አሳልፏል። ቡድኑ አላማውን ለማሳካት «በሬ ወለደ» ብሎ እንደሚያሳምን ጠንቅቀን እናውቃለን። ግቡን የሚያሳካለት ከሆነ የትኛውንም ድንጋይ እንደሚፈነቅል፣ አንዴ አንበሳ አንድ ጊዜ ደግሞ ውሻ እንደሚሆን ሃቅ ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥትም ይህንን መረዳት ይኖርበታል። ማንኛውም ግጭት በድርድርና ጦርነት ቢፈታ መልካም ነው። ከአሸባሪው ትህነግ ባህሪ አንፃር ግን ይህ እንደማይሆን ማወቅ ብዙ የሚቸግር አይደለም። ያለፉትን ነገሮች እረስተን ወደ ፊት እንሂድ ብንል እንኳን የሰሞኑን የትህነግን ተለዋዋጭ ባህሪና እርስ በእርስ የሚጣረስ መዘላበድ እንዴት መዘንጋት እንችላለን።

የቡድኑን የባንዳነት አገር የማፍረስ ተልዕኮ ለማክሰም እና ዘላቂ አገራዊ ሰላም ለማስፈን መንግሥትም ሆነ ጀግናው ሰራዊታችን የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ ከምን ጊዜውም በላይ ዝግጁ ሆነው ሊቆሙ ይገባል። በቡድኑ የከፋ ጭቆና ስር የሚገኘው ኢትዮጵያዊው የትግራይ ሕዝብም ከዚህ አረመኔ ቡድን ነፃ መውጣት እንዳለበት ልናምን ይገባል። በቡድኑ «እደራደራለሁ» የሚል ማዘናጊያ ዲስኩር አምኖ ሕዝቡን ለዳግም ወረራ፣ ጭፍጨፋና ውድመት የሚጋብዝ መንግሥት እንደሌለ ሊታወቅ ይገባል።

መንግሥት ከቡድኑ ደጋፊና ጋላቢ ኃይሎች ሊደርስበት የሚችለውን ጫና የሚቋቋምበት ስልት ደግሞ ደጋግሞ መንደፍ ይገባዋል። የመጀመሪያው ትህነግ በኢትዮጵያ ውስጥ የበቀለ እባጭ እንጂ ሕጋዊ መሠረት ያለው ቡድን አለመሆኑን ደጋግሞ ማስገንዘብ ያስፈልጋል። ዓለምአቀፍ ተቋማትም ሆነ የፀጥታው ምክር ቤት የኢትዮጵያን ሉአላዊነት በማያከብር መልኩ በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገቡ ማስገንዘብም ሆነ ማሳሰብ የዕለት ተዕለት ሥራው መሆን አለበት።

ይህ ተግባር የአሸባሪው ትህነግ የቀብር ሥነሥርዓት እስካልተፈፀመ ድረስ መቆም የለበትም። ለዚህ የሚሆን በሳል የዲፕሎማሲ ሥራ ከተሠራ፣ ወጣቱ መከላከያን ተቀላቅሎ ወረራውን መመከት ከተቻለ፣ የሴራ ፖለቲካ የሚጎነጉኑና የኢትዮጵያን አንድነት የሚፈታተን ተግባር ውስጥ ያሉ የውጭም ሆነ የውስጥ ቡድኖች የረዘመ እጅ ከቆረጥን መላው ኢትዮጵያውያን የሰላም አየር የሚተነፍሱበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም። የሽብር ቡድኑ ትህነግ «በአንድ ራስ ሦስት ምላስ» አካሄድ ማብቂያም እንደዚሁ። ሰላም!!

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# ባሳለፈው ችግር- ነገን ለመሻገር

**መልካምሥራ አፈወርቅ**



መልክና ቁመናዋን ላስተዋለ እንኳን አልቅሳ ተከፍታ የምታውቅ አትመስልም። በአትኩሮት ላያት ግን ጠይሙ ፊቷ ብዙ የሚናገር ይመስላል። ጥቂት ላሰበ በወይዘሮዋ እርጋታ ውስጥ የተደበቀ ማንነት እንዳለ መገመት አይቸግርም። በየአፍታው በዓይኖቿ የሚመነጨው ትኩስ ዕንባ በህይወቷ ብዙ መከራ ማለፉን ያሳብቃል። ወይዘሮ መሰረት አርጋው ውልደትና ዕድገቷ አዲስ አበባ ልዩ ስሙ ተክለሀይማኖት ከሚባል አካባቢ ነው። ኑሮዋን በጎዳና የላስቲክ ጎጆ ከማድርጓ በፊት እሷም እንደሌሎች ግድግዳና የቆርቆሮ ጣራ ከነበረው ቤት ውላ ታድር ነበር። የዛሬን አያድርገውና እንደአሁኑ ጤናዋ ሳይታወክ ህይወቷ በሰላም፣ ፍቷ በፈገግታ የተሞላ ነበር። መሰረት ወላጅ እናቷን በሞት ያጣችው ገና የአንድ ዓመት ህጻን ሳለች ነው። የዛኔ እሷን የማሳደግ ሀላፊነቱ የታጠለው በአክስቷ ትከሻ ሆነ። አክስት የአባቷ ታላቅ እህት ናቸው። የእናቷን መሞት ተከትሎ ከወንድማቸው የተቀበሏትን ህጻን ለማሳደግ በወሰኑ ጊዜ አባት ከስፍራው ርቀው ከዓይን ተሰወሩ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ የመሰረት ወላጅ አባት ልጅ ‹‹አለኝ›› ብለው አልተመለሱም። መሰረት ስለወላጆቿ ስትሰማ ያደገችው አንዳቸው በሞት፣ ሌላቸው በመጥፋት እንደተለይዋት ነው።

አክስቷን እንደእናት አባት ተቀብላ መኖር የጀመረችው ህጻን አንዳች ሳይጎድልባት በፍቅር አደገች። የሙት ልጅ ብትሆንም በቤቱ ያሉ የአክስቷ ልጆች እህት ወንድም ሆኑላት። ልጅነቷን አገባዳ ታዳጊነትን እስከትጀምር ህይወት አልጎረበጣትም፣ ባይተዋርነት፣ ብቸኝነት ይሉት ስሜት አልፈተናትም። የአስራ አራተኛ ዓመት ልደቷን ባከበረች ማግስት የመሰረት ህይወት ከፈተና ሊወድቅ ግድ አለ። በፍቅር ተንከባክበው ከልጆቻቸው ሰይለዩ ያሳደጓት አክስቷ በድንገት አረፉ። ይህኔ ክፉኛ ሆድ ባሳት፣ ሀዘኗ ከፋ፣ እስከዛሬ ውስጧ ያልነበረ ብቸኝነት ከበባት።

አሁን መሰረት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ናት። አክስቷን በሞት ካጣች በኋላ ህይወትን እንደቀደሞ ለመቀጠል ትፍጨረጨር ይዛለች። ውሎ አድሮ በቤቱ የተከሰተው አለመግባባት ግን ሰላም እየነሳት ነው፤ የአክስቷ ልጆች ከእናታቸው ሞት ማግስት እሷን ማየት እንደማይሹ ነግረዋታል። መሰረት ስለምን ብላ መወዛገብ አልፈለገችም። እነሱ ከእሷ የሚጋጩበትን ምክንያት አሳምራ ታውቀዋለች። ሰበብ እየፈለጉ የሚጣሏት በመኖሪያ ቤቱ መነሻ ነው። ቤቱ የቀበሌ ይዞታ መሆኑ ይታወቃል። እንዲያም ቢሆን የእሷን አለመወለድ ምክንያት ሆኖ እንድትልቅ ተገዳለች። የአክስቷ ልጆች ከእሷ በዕድሜ ይበልጣሉ። ታናሽነቷን አይተው ግን ማዘን አልፈለጉም። ከቤት እንድትወጣ ሲወስኑ በአንድ አይነት ቃልና ስሜት ነበር። ደጋግመው ቤቱ ለእነሱ ብቻ እንደሚገባ ነገሯት። መሰረት ምርጫ የላትም። የልባቸውን ሞላች። ያደገችበትን ቤት ላትመለስባት ተሰናብታ ከወዳጅ ዘመድ ተጠጋች። የመሰረት ጅምር ትምህርት እንደቀድሞው አልቀጠለም። በየዘመዱ ቤት ያለው እንክርት ህይወቷን ፈተነው። የዘመድ ቤት ኑሮ እንዳሰበችው አልሆነም። ውላ አድራ ከራሷ መከረች። ያገኘችውን እየሰራች ለእጇ ሳንቲም መያዝ እንዳለባት ወሰነች። ያሰበችው ሆነ። የአቅሟን ቤት ተከራይታ ራሷን መምራት ያዘች።

**የወታደሩ ዓይኖች**

አሁን መሰረት በአካል ጎልብታ በዕድሜ ጨምራለች። ዛሬ ከጎኗ የሚሆን ዕንባዋን የሚያብስ ዘመድ የላትም። የእናት አባቷን ፍቅር ሞልተው እንደ ልጅ ያሳደጓትን አክስቷን ካጣች ወዲህ ህይወት መልኳን ቀይራባታለች። እንደእህት ወንድም የምታያቸው የአክስቷ ልጆች በቤት ንብረት ሰበብ ከደዋታል። ማንም እንደሌላት የምታውቀው ወጣት አጋር እንደሚያሻት ልቧ ሹክ እያላት ነው። መሰረት ድንገት ካወቀችው ወታደር ጋር መግባባት ይዛለች። ወታደሩ አገር ለማስጠበቅ፣ ድንበር ለማስከበር ዝግጁ የሆነ ወጣት ነው። ባገኘችው ቁጥር ጎዶሎዋ የሞላ፣ ቀኗ የፈካ ይመስላታል። ስታየው ውስጧን ደስ ይለዋል። ሲያወራት ታደምጠዋለች። ሲያጫውታት ጊዜ ትሰጠዋለች። ዓይኑን የጣለባት ወታደር በዚህ ብቻ አልበቃውም፤ ልቧን ተረክቦ ልቡን አስረከባት። የሁለቱ ግንኙነት ፍቅር ቢያሸንፋ ቁምነገር አሰቡ። ትዳር ይዘው ጎጆ ቀልሰው መኖር ወደዱ። ጥንዶቹ በትዳር ዘልቀው ቤት ሲያቀኑ መተሳሰባቸው ነገን የሚያሻግር ሆነ። የአብሮነታቸው መስመር ጠንክሮ ዓመታትን በአንድ ኖሩ። ፍቅራቸው በመኖር ብቻ አልተጋመሰም። ሁለቱን በአንድ የሚያጣምር ፤ህይወት ኑሯቸውን የሚያሳምር ፍሬ አገኙ። ትዳራቸው በልጅ በረከት ታደሰ። የመጀመሪያ ልጃቸውን በፍቅር እያዩ አቅፈው ሳሙ። ዳግም ነገ የመኖር ተስፋቸው ለመለመ።

መሰረት ከልጇና ከባለቤቷ ጋር ህይወትን ቀጥላለች። ትናንት የሆነባትን አታስብም። ብቸኛ የሆነችባቸው ዓመታት አሁን በእጥፍ በሆኑ የደስታ ቀናት ተክሰዋል። ዛሬ ልጇና ባለቤቷ ጎዶሎዋን ሞልተው ፤ዓለሟን አሳምረዋል፣ ዕንባዋን አብሰው ፈገግታዋን መልሰዋል።

**ድንገቴው ህመም..**

መሰረት አልፎ አልፎ የሚሰማት ህመም ጤና ይነሳት ይዟል። የሚጠባ ልጇን እንደታቀፈች ስትስል፣ ስታስነጥስ መዋል ልማዷ ነው። ሁሌም የተለየ ድካም ይሰማታል፤ ልቧን እያስጨነቀ መተንፈሻ ያሳጣት ህመም አልጋ አያስያዝ ያስነሳታል። ‹‹ተሸሎኛል››ስትል እያገረሸ በውጋት ያሰቃያታል። መሰረት ህመሟ የሳንባ ቲቢ መሆኑን ካወቀች ሰንብታለች። መድሀኒት ታዞለት ዘወትር እየወሰደች ነው። ያም ሆኖ አልተሻላትም። አንድቀን ህመሙ ባስ ሲል ወደ ሀኪም ቤት አቀናች። ሀኪሞቹ የቀደመ ውጤቷን እያስተዋሉ ተጨማሪ ምርመራ እንድታካሂድ አዘዙ። መሰረት እንደተባለችው ሙሉ ምርመራ አካሄደች፣ ደም ሰጥታ ውጤት ጠበቀች። ጥቂት ቆይቶ ሀኪሙ እጅ የደረሰው የምርመራ ውጤት እንደተገመተው ሆነ። ጥርጣሬው ትክክል ነበር። መሰረት ከሚያሰቃያት የሳንባ ህመም በተጨማሪ በደሟ የኤችአይቪ ቫይረስ ተገኝቷል። ሀኪሞቹ ከውጤቱ በኋላ መሰረትን እያጽናኑ ማድረግ ስለሚገባት ጥንቃቄዎች ምክር ለገሱ። ወይዘሮዋ ሁለት ዓመት ያልሞላውን ህጻን ልጇን እያጠባች ነው። ከዚህ በኋላ ከቀድሞው የበለጠ ጥንቃቄና እንክብካቤ ያሻታል። ቫይረሱ በደሟ እንደተገኘ ሌሎች ጥያቄዎች ሊነሱ ግድ ሆነ። አሁን ህጻኑና ባለቤቷ ተመሳሳይ ምርመራ ማካሄድ አለባቸው። በተለይ ባለቤቷ በፈቃደኝነት የተመሰረተ ይሁንታው ያስፈልጋል።

**የጭንቅ ቀናት ...**

መሰረት ውጤቱን ከሰማች በኋላ በከባድ ድንጋጤ ተዋጠች። ስጋትና ጥርጣሬ እየተመላለሱ አስጨነቋት። ትንሹ ልጇ በእርግዝናዋ ፤ ቆይቶም በማጥባት ጊዜ ከእናቱ ቫይረሱን ሊወስድ ይችላል። ይህን ስታስብ ጸጸቱ ዕንቅልፍ ነሳት። ሆስፒታል በነበረች ጊዜ ከህክምና ባለሙያዎቹ ልጁ አስቸኳይ ምርመራ ማካሄድ እንዳለባት ተነግሯታል። መሰረት የሀኪሞቹን ምክር ተቀብላ ህጻን ልጇን ለማስመርመር ከሆስፒታል ተገኝታለች። ትንሹ ልጅ በእናቱ እቅፍ ሆኖ ትንሽዬ ክንዱን ለምርመራው አዘጋጅቷል። የደም ናሙናው ሂደት ሲጠናቀቅ ለውጤቱ ቀጠሮ ተሰጣት። እናት መሰረት በአይኖቿ ሙሉ እያነባች ፈጣሪዋን ተማጸነች፣‹‹በኔ ይብቃ፣ በልጄ አይለፍ›› ስትልም ምህረት ፤ድህነቱን ተመኘች። የቀጠሮ ቀን

ወይዘሮዋ ዛሬ በቀጠሮዋ መሰረት ከሕክምና ማዕከሉ ተገኝታለች። ጊዜው ደርሶ ስሚ እስኪጠራ ብዙ እያሰበች ነው። ከልጅነቷ ጀምሮ ያሳለፈችው ስቃይ ቀላል የሚባል አይደለም። ያለእናት አባት የኖረችበት ጊዜ ዋጋ አስከፍሏታል። ካደገችበት ቤት በግፍ መባረሯ አሁን ለቆመችበት ህይወትና ለደረሰባት ክፉ አጋጣሚ ምክንያቷ ነው። ያልተመቸ ኑሮዋ ለህመም አጋልጦ ሲያሰቃያት በደሟ የተገኘው የኤችአይቪ ቫይረስ ለአንድ ልጇ ጭምር ስጋት ሆኗል። አሁንም እናት መሰረት ጭንቀት ውስጥ ናት፤ስለራሷ፤ስለባሏ በተለይ ስለትንሹ ልጇ እያሰበች የዓይኖቿን ዕንባ ታብሳለች። በድንገት ስሟ ሲጠራ ከዕንቅልፏ የባነነች ያህል ፈጥና ነቃች። ከአንድ ክፍል ገብታ እንደተቀመጠች ሀኪሙ በእጁ የያዘውን ካርድ እያገላበጠ እውነቱን ሊያሳውቃት ተዘጋጀ። መሰረት ሀኪሙ ተናግሮ እስኪጨረስ አፏ እየደረቀ አዳመጠችው። የተባለችውን ሰምታ የሀኪሙን ምክር አድምጣ ከክፍሉ ስትወጣ እናት መሰረት ፊቷ በፈገግታ በርቶ፣ እርምጃዋ ከወትሮው ጨምሮ ነበር። አሁን ልጇ በደሙ የኤችአይቪ ቫይረስ እንደሌለበት ተረጋግጧል። መሰረት ይህን ስትሰማ በደስታ አነባች፣ የራሷን ህመም ረሳች፣ ፈጣሪዋን አመሰገነች።

**ህይወት በሌላ መልክ...**

መሰረት የልጇን ውጤት ካወቀች ወዲህ ጡት ማጥባት እንደሌለባት ተነግሯታል። አሁን ትልቁ ሸክም ከትከሻዋ ወርዷል። እንዲያም ሆኖ ሌላ ችግር አልቀረላትም። ባለቤቷ ተመርምሮ ኤችአይቪ እንዳለበት ካወቀ ወዲህ በእጅጉ ተስፋ ቆርጧል። በየቀኑ በመጠጥ ሱስ መናወዙም ህይወት ኑሯቸውን አመሳቅሏል፡ ፡መሰረት ከምትወስደው የቲቢ መድሀኒት ባለፈ በጀመረችው ተጨማሪ ህክምና ልዩ ትኩረት የሚያሻት ሆናለች። ከምንም በላይ ግን የባለቤቷ ሁኔታ ሰላም ነስቷታል። ስራውን ትቶ በየቦታው መታየቱ፣ ራሱን ጥሎ በተስፋ ማጣት መሰንከሉ ተስፋዋን አጨልሞባታል። መሰረት በዚህ ፈታኝ ህይወት ላይ ሆና ሁለተኛዋን ልጅ ወለደች። እንዲህ መሆኑ ከባሏ ስራ መፍታት፣ ከእሷ በህመም መጎዳት ጋር ተጣምሮ ኑሮን አስቸጋሪ አደረገው። መልካም ከሆኑ ሰዎች ግቢ ማድቤቱን ቤት አድርጋ ኑሮን ቀጠለች። ያለችበት ቤት በልማት ምክንያት ሲፈርስ ከስፍራው ልትወጣ ግድ ሆነ። እያደር እጅ ሲያጥር፣ ቤት ሲጎድል አማራጮች ጠበቡ። ለቤት ኪራይ የሚከፈል፣ ለዕለቱ የሚላስ የሚቀመስ ጠፋ። መሰረት ውሎ አድሮ ከነቤተሰቧ ከጎዳና ወደቀች። ላስቲክ ወጥራ፣ ከመንገዱ ደርቻ፣ ከአስፓልቱ ጥግ ኑሮ መሰረተች። አሁን ባለቤቷ ከእሷ አይደለም። በመሀላቸው በተፈጠረው ችግር ተለያይተዋል። ከጎኗ ረዳትና አጋዥ የለም፣ ልጆቿን ለማሳደግ፣ አስተምሮ ወግ ለማድረስ ቀን ከሌት መስራት ግድ ይላታል። ለዚህ ብርታቱን የሰጣት ወይዘሮ ስለ ልጆቿ የማትሆነው የለም። በየቀኑ የሾፌሮችና የረዳቶችን ልብስ ታጥባለች፤ለትንሽ ትልቁ ትታዘዛለች፣ ከምታገኘው ገቢ ለልጆቿ ደጉሟ ለላስቲክ ጎጇዋ ትደርሳለች።

**ሌላው ፈተና..**

መሰረት ችግርን ከጽኑ በሽታ ይዛ አመታትን በችግር በገፋችበት የላስቲክ ቤት ህይወት በልጆቿ ተስፋ ታደርጋለች። የጎዳና ህይወቷ ክረምት ከበጋ ከፈተና አይወጣም። ጎርፍና ዝናብ ያስጨንቃታል። ብርድና ውርጩ ያስቸግራታል።

የልጇቿ አባት ከእሷ ባይሆንም ይጠያየቃሉ። እሱን ስታይ ይከፋታል። የትናንትናው መልኩ ዛሬ አብሮት የለም። በህመምና ችግር አካሉ ከስቶ ፊቱ ገርጥቷል። ልብሱ ቆሽሾ ራሱን ጥሏል። ገለልተኛ ሆኖ ከሰዎች ርቋል። እናም መሰረት እሱን ስታይ ይከፋታል ፤ ከልቧ ታዝናለች። ወይዘሮዋ ኤይችኤቪ ቫይረስ በደሟ መኖሩን ካወቀች ወዲህ ራሷን አሳምና መኖርን ለምዳለች። ከዓመታት ወዲህ የሚሰማት ሌላ ህመም ግን ሰላም እየሰጣት አይደለም። ሰውነቷን ክፉኛ ያሳክካታል። መላ አካሏን ላስተዋለ እሳት የበላው ይመስላል። የህመሙ መመላለስ ያስጨነቃት መሰረት ከቀናት በአንዱ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተገኝታ ሙሉ ምርመራ አካሄደች። በወቅቱ የተገኘው ውጤት አስደንጋጭ ነበር። ወይዘሮዋ በካንሰር በሽታ ተጠቂ ሆናለች።

‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› እንዲሉ የመሰረት ጤንነት በሌላ ህመም መፈተኑ ለሚያውቋት ሁሉ አስደንጋጭ ሆነ። በምልልስ የኬሞቴራፒ ህክምናን የጀመረችው ሴት ህመሙ ከምትገኝበት፣ ካሳለፈችው ህይወት ተዳምሮ ኑሮዋን አስቸጋሪ አድርጎታል። የቀደመ ታሪኳን የሚያውቁና ችግሯን የተረዱ አንዳንዶች በማጽናናትና በምክር ቆመ እንድትሄድ አግዘዋታል። በተለይ በሆስፒታሉ ህክምናዋን የያዘው ዶክተር ዳኛቸው እሷንና ልጇቿን ከግል ኪሱ እየደጎመ ነገን አሻግረው እንዲያዩ ረድቷቸዋል። መሰረትም ለዚህ ሰው ያላት አክብሮትና ምስጋና ከሌሎች ሁሉ ይለያል። ዛሬም መሰረት የዘንድሮን ክረምት በጎዳናው ቤቷ አሳልፋለች። ህመም ከኑሮ ድካም ያንገላታት ወይዘሮ በእግሯ ላይ የሚሰማት ብርቱ ህመምና በሰውነቷ ላይ የሚስተዋለው ለውጥ ሲያውካት ይውላል። በውጭ አካሏ ላይ በግልጽ የሚስተዋለው የጓጓለ አይነት ምልክት ሁሌም እረፍት እንደነሳት ነው። ልብስ አጥባ ስትገባ እጇን ክፉኛ ያሳክካታል፣ ያቃጥላታል። አንዳንዴ የሚመላለስባት ቁርጥማት በእጅጉ ከባድ ነው። መሰረትን ሳገኛት ገጽታዋ የሕመምተኛ አይመስልም። መልኳ የተረጋጋ ፈገግታዋ የተመጠነ ፤የፊት ቀለሟ የሚያምር እንደሆነ አስተውያለሁ። ከእሷ ጥቂት ማውጋት እንደጀመርን ልብሷን አውልቃ መላ ሰውነቷን አሳየችኝ። መልከ ብዙ በሚባል አይነት ገጽታ ተዥጎርጉሯል። እግሯ፣ ባቷ፤ጀርባዋና ሆዷ ሳይቀር የተለየ መልክ አለው። ውስጤ አዘነ፣ መንፈሴ ተረበሸ፣ ዕንባዋን ተከትዬ ላለማልቀስ ከራሴ ታገልኩ ፡ለጊዜው ተሳካልኝ።

**ዛሬም እንደትናንቱ..**

መሰረት ዛሬም ከህመም እየታገለች ለልጆቿ መኖር ይዛለች። ኑሮዋ አሁንም ከጎዳና አልወጣም። ማንነቷን የተረዱ የወረዳ አካላት ቤት እንደምታገኝ ተስፋ ሰጥተዋታል። በተሰጣት ተስፋ ነገን ለማየት ዛሬን በችግር ልታልፍ ግድ ብሏታል።

የመሰረትን ልጆች ላየ ድህነት ያለባቸው አይመስሉም። ኑሯቸው ጎዳና ቢሆንም ንጹህ ሆነው ይውላሉ። ታሪኳን የሚያውቁ አንዳንዶች ልብስ ያመጡላታል፣ ከቤታቸው ጓዳ ቆርሰው፤ቆንጥረው ያጎርሷታል።

የመሰረት ሁለተኛዋ ልጅ ከአጠቃላይ ተማሪዎች አንደኛ በመውጣት እንዳኮራቻት ነው። ዛሬ አስራሰባት ዓመት የሞላው ወንዱ ልጇ፡ ትምህርቱን አቋርጦ ፤የእሷን ድካም ለመካፈል ሲበረታ ይውላል። በተደራራቢ የጤና ችግር ስትፈተን የምትውለው መሰረት ዛሬ በልደታ ክፍለከተማ በተገነባው የምገባ ማዕከል በቀን አንዴ እንድትመገብ ዕድል አግኝታለች። ሁሌም ከሚሰጣት ቋጥራ ለልጆቿ ታጎርሳለች። ልጆችዋ ለእሷ የጨለማዋ ብርሀን ናቸው። ነገን አሻግራ ታይባቸዋለች፡ ዛሬን በተስፋ ታድርባቸዋለች። ክንደ ብርቱዋ፤መንፈሰ ጠንካራዋ ወይዘሮ።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ቅዳሜ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ፈረሰኞቹ በቻምፒዮንስ ሊጉ የመልስ ጨዋታ ትልቅ ፈተና ይጠብቃቸዋል

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግ የ15 ጊዜ ቻምፒዮኑ ክለብ ቅዱስ ጊዮርጊስ (ፈረሰኞቹ) ከአራት ዓመት በኋላ ወደ አፍሪካ ቻምፒዮንስሊግ መድረክ ተመልሰው ኢትዮጵያን እንደሚወክሉ ይታወቃል። በዚህ የአህጉሪቱ ትልቅ የእግር ኳስ መድረክ የሚያደርጉትን ጉዞም ባለፈው መስከረም 01/2015 በድል ጀምረዋል። ፈረሰኞቹ የመጀመሪያውን የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታ ባህርዳር ስቴድየም ላይ አድርገው የሱዳኑን ኃያል ክለብ አል ሂላልን በቸርነት ጉግሳ ሁለት ግቦች ታግዘው 2ለ1 ማሸነፋቸው አይዘነጋም።

ፈረሰኞቹ ነገ ከአል-ሂላል ጋር ላለባቸው የመልስ ጨዋታ ወደ ሱዳን መጓዝ ያለባቸው ቢሆንም ከቀናት በፊት አስቀድመው ለካፍ ደብዳቤ ማስገባታቸው ታውቋል። ፈረሰኞቹ የመልስ ጨዋታቸውን ካርቱም ላይ እንዲያደርጉ ቀጠሮ መያዙ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከጨዋታው አስቀድሞ በኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን በኩል ለካፍ ደብዳቤ ልከዋል። በደብዳቤው መሠረትም ሱዳን አሁን ካለችበት ወቅታዊ የፀጥታ አለመረጋጋት በመነሳት በአገሪቱ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጁን ተከትሎ ጨዋታውን ሱዳን ላይ ማድረግ ከደህንነት አንፃር ስጋት በመሆኑ ካፍ ጨዋታውን በገለልተኛ ሜዳ እንዲያካሂድ ፈረሰኞቹ ጥያቄ አቅርበዋል።

አል ሂላሎች በተመሳሳይ ባህርዳር ላይ የመጀመሪያውን ጨዋታ ከማድረጋቸው በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ ያለውን ጦርነት ምክንያት በማድረግ ካፍ ጨዋታውን ወደ ገለልተኛ ሜዳ እንዲወስደው ጥያቄ አቅርበው ነበር። ይሁን እንጂ ጥያቄያቸው በካፍ ተቀባይነት አላገኘም።



ፈረሰኞቹ በይድነቃቸው ተሰማ አካዳሚ ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተዋል፣

ፈረሰኞቹ ትናንት ረፋድ ላይ ወደ ካርቱም እንደሚያቀኑ የተጠቆመ ሲሆን፣ የሚጓዙትን የ20 ተጫዋቾች ዝርዝርም ይፋ አድርገዋል። በዚህም ግብጠባቂ ቻርልስ ሉክዋጎ፣ ባህሩ ነጋሽ፣ ተከላካይ ምኞት ደበበ፣ ኤድዊን ፊሪምፖንግ፣ ሄኖክ አዱኛ፣ አማኑኤል ተርፋ፣ ረመዳን የሱፍ፣ ደስታ ደሙ፣ ሱሌማን ሐምዲ ናቸው። አማካይ ተጫዋቾች ናትናኤል ዘለቀ፣ ጋቶች ፓኖም፣ በረከት ወልዴ፣ ሀይደር ሸረፋ፣ ዳዊት ተፈራ፣ ቢንያም በላይ፣ ቸርነት ጉግሳ፣ ዳግማዊ አርአያ፣ አብርሀም ጌታቸው ሲሆኑ አጥቂዎች ኢስማኤል ኦሮ አጎሮ፣ ተገኑ ተሾመ መሆናቸው ታውቋል።

ከስብስቡ ጋር ልምምድ ሲሠሩ የሰነበቱት የተቀሩት አምስት ተጫዋቾች ደግሞ ከሌሎች የዕድሜ ዕርከን ከተውጣጡ ተጫዋቾች ጋር በመጪው ቅዳሜ በሚጀምረው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ቡድኑን ወክለው የሚሳተፉ ይሆናል።

የሁለቱን ክለቦች የመልስ ጨዋታ ሱማሌያውያን ዳኞች እንደሚመሩት ከቀናት በፊት ይፋ ያደረገው ካፍ ለፈረሰኞቹ ጥያቄም እስከ ትናንት መልስ አለመስጠቱ የፈረሰኞቹን ጥያቄ እንዳልተቀበለ ማረጋገጫ ሆኗል። የአል ሂላል ደጋፊዎች ክለባቸው በባህርዳሩ ጨዋታ መሸነፉን ተከትሎ የተለያዩ ሰበቦችን በመፍጠር ቅሬታዎችን በማህበራዊ ሚዲያዎች ሲያሰራጩና ሲዝቱ ታይተዋል። ይህም የመልሱን ጨዋታ ለፈረሰኞቹ በሁለት መንገዶች ፈተና ሊሆን እንደሚችል ስጋት ፈጥሯል። አል ሂላል በባህርዳሩ ጨዋታ ቢሸነፍም ፈረሰኞቹ ላይ አንድ ግብ ማስቆጠሩ በመልሱ ጨዋታ ውጤቱን ቀልብሶ ወደ ቀጣይ ዙር የማለፍ ተስፋ አለው። ለዚህም በሜዳውና በደጋፊው ፊት ፈረሰኞቹ ላይ እግር ኳሳዊ ያልሆነ ተፅዕኖ ማሳደሩ እንደማይቀር ስጋት ሆኗል። ፈረሰኞቹ የሚኖረውን ጫና ተቋቁመው በድምር ውጤት ማሸነፍ ከቻሉም ደጋፊዎች ያልተገባ ሁከት ሊፈጥሩ የሚችሉበት ዕድል ጠባብ አይደለም። ይህ ደግሞ ሱዳን አሁን ካለችበት የፀጥታ ሁኔታ አንፃር ለፈረሰኞቹ ስጋት ሊሆን ይችላል።

የፈረሰኞቹ አሠልጣኝ ዘሪሁን ሸንገታ ከባርዳሩ ድል በኋላ «በመጀመሪያው አጋማሽ ላይ ጥሩ ነበርን፤ ሁለተኛው አጋማሽ ላይ ቀላል ስህተት ሠርተን ሁለት ለአንድ አሸንፈናል። ከሞላ ጎደል በጣም ጥሩ ነው ተጫዋቾቼ የሠሩት።» በማለት ለሶከር ኢትዮጵያ አስተያየት ሰጥተዋል።

ፈረሰኞቹ በመጨረሻ ሰዓት ግብ ማስተናገዳቸው በመልሱ ጨዋታ ጫና ውስጥ እንዳይገቡ ስጋት ቢፈጥርም ወደ ቀጣዩ ዙር ለማለፍ ከተጋጣሚያቸው የተሻለ ዕድል አላቸው። አሰልጣኝ ዘሪሁን ወደ ጨዋታው ሲገቡ ቡድናቸው ግብ እንዳያስተናግድ አስበው እንደነበር ተናግረዋል። ነገር ግን ባለቀ ሰዓት ላይ በትንሽ የመከላከል ቅንጅት በሠሩት ስህተት ግብ አስተናግደዋል። ይህም በመልሱ ጨዋታ ዋጋ ሊያስከፍላቸው እንደሚችል አስተያየት ሰጥተዋል። ይሁን እንጂ ይህን ስጋት ለማስቀረት ፈረሰኞቹ ከባህርዳሩ ጨዋታ የተሻለ ነገር ሠርተው በድምር ውጤት ለማሸነፍ እንደሚዘጋጁ አስረድተዋል። ቅዱስ ጊዮርጊስ ተጋጣሚውን በደርሶ መልስ ውጤት ካሸነፈም በቀጣዩ ዙር ከታንዛንያው ያንግ አፍሪካንስና ከደቡብ ሱዳኑ ዛላን ኤፍሲ ሩምቤክ አሸናፊ ጋር ይጫወታል።

ውድድሩ ሱዳን ላይ መደረግ አለመደረጉ ዛሬ የሚታወቅ ቢሆንም ካፍ ይህን ተጠባቂ ጨዋታ እንዲመሩ አራት የሶማሊያዊ ዳኞች መመደቡም ይታወቃል። ይህን ጨዋታ በመሀል ዳኝነት እንዲመሩ የ29 ዓመቱ ዑማር አብዱልቃድር አርታን የተመረጡ ሲሆን፣ በረዳትነት ዳኝነት ሀምዛ ሀጂ እና ዓሊ መሐመድ በአራተኛ ዳኝነት ደግሞ ሀሰን መሐመድ መመደባቸው ታውቋል። የሊቢያ ዜግነት ያላቸው ጋማል ሳሊ በበኩላቸው የጨዋታው ታዛቢ እንደሚሆኑ ካፍ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

# ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

## ጋር በመተባበር በየሣምንቱ የሚታተም

## አስተዳደራዊ በደሎችን በጥናት የመከላከል ውጤታማነት በተግባር ሲፈተሽ

**ዳንኤል ዘነበ**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ተሻሽሎ በፀደቀው አዋጅ ቁጥር 1142/2011 ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት መካከል የአስተዳደር በደል መንስኤዎችንና መፍትሔዎቻቸውን የሚያስቀምጡ የጥናቶች ሥራዎችን ማከናወን ይገኝበታል። በዚህ መሠረት ተቋሙ በ2014 ዓ.ም በፌዴራል፣ በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋ፣ ኦሮሚያ፣ ሐዋሳ፣ ባህር ዳር እና አሶሳ በመንግሥት አስፈፃሚ ተቋማት ሠራተኞች አገልግሎት አሰጣጥ ተግዳሮቶች ላይ ያተኮረ ነበር። እኛም በዛሬው ጽሑፋችን በ2014 ዓ.ም በተቋሙ በተደረገው ሀገራዊ ጥናቱ ላይ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶችን የምናቀርብላችሁ ይሆናል።

የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ወጥቶ ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ በተቋማቱ ስታንዳርድ ቢወጣም ተግባራዊ አይደለም። ይህ በመሆኑ በበላይ አካል ተከታታይ ድጋፍ ተደርጎላቸው እንዲጠናከሩ እየተደረገ እንዳልሆነ፤ በአዳዲስ ህጎችና ሀሳቦች ከመስራት ይልቅ በነበረው ልምድ ብቻ የሚሠራ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል። በተጨማሪ የአገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቢኖርም የግብዓት አቅርቦት ችግር ወይም ፋሲሊቲ አለመሟላት፤ በስታንዳርዱ መሠረት ተግባራዊ አለመሆኑ ተገቢውን አገልግሎት ባለመስጠጥ ተገልጋዮች መጉላላት፤ ተገልጋዮችና አገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች ጋር ጥሩ ያልሆነ የቃላት መወራወርና (ግንኙነት አለመኖር) በቅንነት አለማገልገል እንዲፈጠር መንገድ መክፈቱም ተጠቅሷል።

ኃላፊነትን ከመወጣት አንፃር የተመቻቸ የሥራ አካባቢን በሚመለከት የመሥሪያ ቤቶች የቢሮ ጠባብነት፤ በአግባቡ በሥራ ሰዓት ላይ ለመገኘት በአንዳንድ መስሪያ ቤቶች ለትራንስፖርት ምቹ አለመሆን፣ አንዳንድ መስሪያ ቤቶች የአካባቢ የንጽህና ጉድለት፣ መጸዳጃ ቤቶች ችግር እና ለሥራ የሚሆኑ ቁሳቁሶች በቂ አለመሆን በአብዛኞዎቹ ተቋማት የሚታይ ችግር እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል። በአንዳንድ መስሪያ ቤቶች ደግሞ ከሰው ኃይል አኳያ ብቁ እና በቂ ባለሙያ አለመኖር እንዲሁም የደሞዝ እና ጥቅማጥቅም ማስተካከያ በሚመለከት ትኩረት ያለመስጠት እንደ ክፍተት ተመላክቷል። በሌላ በኩል በአብዛኞዎቹ ተቋማት የሕፃናት ማቆያ ክፍል አለመኖር፣ በአብዛኞዎቹ ተቋማት ለሠራተኞቹ የተመቻቸ የቁጠባ አገልግሎት፣ የብድር አገልግሎት ያለመኖር፣ በተቋማት ለሠራተኞቹ በበቂ ሁኔታ የአቅም ግንባታ እና የትውውቅ ስልጠና አለመኖር ለሥራ ተነሳሽነት እንቅፋት መሆናቸው በዋናነት በጥናቱ ውጤት ተመላክተዋል።

ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች በህግ የተሰጣቸወቸን መብት እንዲከበር ከማድረግ አኳያ በአካል ድጋፍ ለሚንቀሳቀሱ ባለጉዳዮችና ሠራተኞች አብዛኞቹ መስሪያ ቤቶች ምቹ አይደሉም። ከዚህ በተጨማሪ ለአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መወጣጫ ራምፕና ሊፍት የሌላቸው መሆኑ፣ መስማት ለተሳናቸው ሠራተኞችና ባለጉዳዮች ጋር በቀላሉ መግባባት እንዲቻል የምልክት ቋንቋ ተናጋሪ አለመኖርና ከዚህ ጋር ተያይዞ የወጣ ሕግ አለመኖር፣ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ አካል ጉዳተኛ ተገልጋዮች ወደ መስሪያ ቤቶች አገልግሎት ፈልገው በሚመጡበት ጊዜ በቋሚነት አስተርጓሚ አለመኖር ከዚህ ጋር ተያይዞ የወጣ ሕግ አለመኖር ይጠቀሳል። በአንዳንድ አገልግሎት ሰጪ መሥሪያቤቶች ደግሞ ለአካል ጉዳተኛ ባለጉዳይ ማስተናገጃ በቂ የማቆያ ቦታ አለመኖርና በእቅድ ላይ አውሎ ወደ ተግባር ከመሥራት አኳያ ችግሮች መኖራቸውን በጥናቱ ተረጋግጧል። ለልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሚፈለገው ደረጃ አገልግሎት መስጠት ያለመቻል ከላይ የተገለፁት ተግዳሮቶች መኖራቸው ለማረጋገጥ ተችሏል።

በሠራተኛው የሚሰጠው አገልግሎት በቀልጣፋነት፤ ፈጣን ምላሽ ሰጪነት እና በጥራት ከመስጠት አንጻር የሥራ ኃላፊም ሆነ ባለሙያው ስለሚመሩት ተቋምና የተመደቡበት ሥራ ጋር ያላቸው ግንዛቤ በሚፈለገው ደረጃ የተሟላ አለመሆን፣ አንዳንድ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በቂ ግንዛቤና ዕውቀት የሌላቸውን በተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች አቅማቸው ባለመጎልበቱ በሚሠሩ ሥራዎች ላይ በዕውቀትም ሆነ በክህሎት እንዲሁም የባህሪ ችግርና ሕጎችን ጠንቅቆ ባለማወቅ አፈጻጸም ላይ ክፍተቶች መስተዋላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። በተጨማሪም ተገቢውን አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ከመስጠት አኳያ በቂ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ተጨባጭ ያልሆነ ምክንያት በመደርደር ወይም ግልጽ ባልሆነና ተገማች በማይሆን መንገድ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በሙሉ አቅሙ እየተወጡ አለመሆኑ፣ ግልጽ የአሠራር ሥርዓቶች አለመኖርና የተጠያቂነት አሠራር ጠንካራ አለመሆን እና የአመራር መቀያየር በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ችግር መፍጠር አገልግሎት አሰጣጡኝ ቀልጣፋ፣ ፈጣን፣ በአፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት እና በጥራት ለመስጠት ያለመቻል ከመደምደሚያ ተደርሷል፡፡

ሠራተኞች ሥነምግባርን ተላብሰው ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት ወጥተው አገልግሎት ከመስጠት አኳያ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ ተረጋግጧል። ለችግሩ መንስኤዎቹም አገልግሎት ፍለጋ የሚመጣን ባለ ጉዳይ ገንዘብ የመጠየቅ፣ ባለ ጉዳይ የማመላለስ፣ ባለጉዳዩን መሳደብ ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት ለጉዳያቸው ጥሩ ምላሽ አለመስጠት፣ አድሎአዊ አሠራር መኖሩ፣ ሥራን ባህል አድርጎ ያለመስራት፣ ትውውቅን መሠረት አድርገው የሚሠሩ ሥራዎች መበራከት፣ ጠንካራ የማበረታቻ ሥርዓት ያለመኖርና ከአመራር ስህተት የተነሳ ሠራተኞች ሥነምግባርን በተላበሰ መልኩ ለተገልጋይ አገልግሎት እየሰጡ አለመሆናቸውን በምክንያትነት የተስተዋሉ መንስኤዎች መሆናቸው ከመደምደሚያ ተደርሷል፡፡

የአመራር ክትትልና ድጋፍ በተመለከተ አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት አመራሩ ለሠራተኛው የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ ቢሆንም ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ተሳታፊዎች ደግሞ አመራሩ ለሠራተኛው የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ታውቋል። ለዚህ በምክንያትነት የተቀመጡ ነጥቦች መካከል የተቀናጀ ክትትልና ድጋፍ አለመኖር፣ የሥራ ኃላፊም ስለሚመሩት ተቋምና የተመደቡበት ሥራ ጋር ያላቸው ግንዛቤ በሚፈለገው ደረጃ የተሟላ አለመሆን እና አመራሩ በአመራርነት የበሰለ ያለመሆንና ልምድ ያለመኖር እና ሥራን መዝኖ ግብረ መልስ መስጠት ያለመቻል መሆናቸው ነው፡፡

እርካታ ያልተሰማው ተገልጋይ ቅሬታውን የሚያቀርብበት አካል ስለመኖሩ እና የሚሰጡ ውሳኔዎቻቸውን በተመለከተ በሠራተኛው በሚሰጥ አገልግሎት እርካታ ያልተሰማው ተገልጋይ ቅሬታውን የሚያቀርብበት አካል መኖሩን የሚሰጧቸው ውሳኔዎችም በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል። ነገር ግን ቁጥሩ ቀላል የማይባል ተሳታፊዎች፤ ደግሞ ጉዳዩ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱን ሲገልፁ ይህም የሆነበት ምክንያት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ለቅሬታዎች በአፋጣኝ ምላሽ ያለመስጠት እና አድሏዊ አሠራሮች መታየታቸው በዋናነት የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ